# ማጠቃለያ ምዕራፍ

## ኢትዮጵያ፡ ስለባህሏ ጥበቃ፡ የዛሬውን ትውልድ ስትፋረድ!

ለሃምሳ ዓመታት ያህል የቆየው፡ ያ፡ የአጼ ኃይለ ሥላሴ፡ ሰፊ የእርሻ መስክ፥ የዘር ማሳና የመከር አውድማ፡ እስካሁን ከዘረዘርናቸው በቀር፡ ምን ዓይነት ፍሬን እንዳስገኘ፥ ምን ዓይነት ጠንቅንም ትቶ እንዳለፈ፡ እስቲ፡ በዚህ ምዕራፍ አማካይነት፡ የምንባባችንን ጉዞ፡ ዛሬ፡ ጎልተው በሚታዩ፡ ጥቃቅን ልምዶች፥ በቃል ተነግረው በሚሰሙ፡ የዘወትር ዘዬዎችና በሚፈጸሙ፡ ተራ ድርጊቶች ጀምረን፡ ጠለቅ ወዳሉት መልካካም ይትባሃሎቻችንና ሕያዋን ቅርሶቻችን በመድረስ እንጨርስ!

### "የጨው ክምር ሲናድ፡ ሞኝ ይስቃል! ብልህ ያለቅሳል!"

ይህን ማጠቃለያ ምዕራፍ፡ በዚህና "ሳይቃጠል በቅጠል!" በሚለው የአበው ምሳሌ፡ መክፈት የፈለግሁት፡ ያለምክንያት አይደለም:: ዛሬ ከምንገኝበት፡ የአገር ውድቀትና የሕዝብ ውርደት አሠር የተደረሰው፡ ከእግዚአብሔር ቃላት ጋር፡ እነዚህን የመሰሉትን፡ የአባቶችንና የእናቶችን፡ የቁም ነገር መፈክሮች ባለማጤን መኾኑን በማስገንዘብ፡ በሕይወተ ሥጋ ወደኋላ ለቀረውና አዲስ ለተፈጠረው ትውልድ ለማስታወስ ነው::

አዎን! "ማንነት" የሚታወቅበትና የሚጠበቅበት፡ የአንድ አገር ሃይማኖት፡ ለሕዝቡ ህልውናና ለአገሩ ነጻነት፡ መሠረታዊ አቋም መኾኑ፥ እርሱም፡ ጸንቶ የቆመው፡ በእኒያ፡ ጥቃቅንና ተራ መስለው በሚታዩ፡ የዘወትር ዘዬዎች፥ ልምዶችና ድርጊቶች ሳይ መኾኑ ሊዘነጋ አይገባም:: እነዚህ፡ የአቋሙ አውታሮች፡ ሳይታወቅ፡ ወይም ቀላል መስሎ፥ በረቂቅ ብልሃት፡ ሠርጎ በሚገባውና ባዕድ በኾነው፡ በማናቸውም ኃይል፡ እነርሱን ለማጥቃት፥ ከዚያም አልፎ ለማጥፋት፡ የሚደረገውን ሙከራ ኹሉ፡ በማስተዋልና በጥንቃቄ ነቅቶ መጠበቅና ባግባቡ መከላከል፡ ለዚያ አገር እውነተኞች ዜጎች፡ አስፈላጊያቸው ብቻ ሳይኾን፡ ግዴታቸውም ነው::

ይህን ግዳጁን፡ በንቀት፥ በንዝንላልነት እና/ወይም በቸልተኛነት ሳይፈጽም የቀረ ሕዝብ ኹሉ፡ ማንነቱ ጠፍቶ፡ ህልውናው በመደምሰስ ይፈጸማል፤ ይህን ግዳጁን ተገንዝቦ የሚፈጽም ሕዝብ ግን፡ በማንነቱ እውቅናና በነጻነት ህልውናው፡ በበለጠ ተጠናክሮና ተደላድሎ ይቀጥላል፤ ይህ ብቻ ሳይኾን፡ በሥልጣኔ እርምጃውና በልማት ዕድገቱም፡ በሚያስተማምን ጽናት ተጉዞ፡ ካቀደው ደረጃ ይደርሳል::

### የመጀመሪያዎቹ ሰዎችና የአባቢቱ ጭውውት::

ለዚህ እውነታ፡ ሌላም ምሳሌ አያስፈልግም፤ የመጀመሪያዎቹ ሰዎች፡ አዳምና ሔዋን ይበቃሉ:: ዲያብሎስ፡ እነርሱን፡ ያን ከመሰለ የልዕልና ሕይወት እንሥቶ፡ በአንድ ጊዜ፡ ያን ከመሰለ የውርደት ሞት ወርውሮ የጣላቸው፡ እንዴትና በምን እንደነበረ ማስታወሱ ይጠቅማል::

አዎን! በትጥቅ የደረጀ፡ የጦር ሠራዊቱን አስከትቶ በማሰለፍ፡ ተዋግቷቸው አልነበረም። በአንዲት የተናቀች እንስሳ አማካይነት ቀስ ብሎና ዘበት አስመስሎ፡ በተለዋወጡት ጭውውት፡ አንዲት የዛፍ ፍሬን እንዲበሉ በማድረግ እንደነበረ፡ ለአንዲት አፍታ እንኳ መዘንጋት፡ በተለይ ለኢትዮጵያዊ፡ ከባድ ሞኝነት ይኾናል። አንድን ሕዝብ ለመበታተን፥ አንድን አገር ለማፈራረስም፡ ባዕዱ ጠላት የሚጠቀመው፡ በዚሁ ዘዴ መኾኑን፡ አበክሮ ማወቅ ይገባል።

ዲያብሎስ፡ እንዲያ፡ በመጀመሪያዎቹ አዳምና ሔዋን ሰውነት የተገለጸችውን፡ የሰዎችን መልካም ሕይወት ለማጥፋት፥ የጋብቻን ሥርዓት ለማፍረስና የእግዚአብሔርን መንግሥት፡ ከምድር ለማስወገድ፡ በኢትዮጵያ የወጠነውን፡ ያንኑ፡ ረቂቅና ግዙፍ ሙከራውን፡ ዛሬም፡ በዚህ ትውልድ መሣሪያነት፡ በኢትዮጵያ ለመፈጸም፡ ይኸው፡ ከጥቃቅኑና ከተራው ነገር ተነሥቶ፡ በሙሉ ኃይሉና ጥበቡ እየታገለ መኾኑን እንመለከታለን፤ ነገር ግን፡ ማሸነፍ አይችልም! የመጨረሻዎቹ አዳምና ሔዋን፡ ኢየሱስ ክርስቶስና ድንግል ማርያም፡ ያን የሰዎች ሕይወት፥ ያን የጋብቻ ሥርዓትና ያችን የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ኹሉንም፡ በሥጋቸውና በደማቸው አለምልመው አጽንተዋቸዋልና!

## በቆራጥ ሕዝብ ዘንድ፡ መልካሙ ኹሉ ይቻላል!

አንድ ቆራጥ ሕዝብ፡ ከፈለገ፡ ኹሉን ማድረግ የሚቻለው መኾኑን ለማመልከት፡ ባመኑበት እምነታቸውና በፈለጉት ሥርዓታቸው፡ ማንታቸውን አኩርተው፥ መሪዎቻቸውንም አቅፈው፡ የኃያላን ተቃዋሚዎቻቸውን ጥቃት ተቋቁመው፥ በውጭ ተፅዕኖም ሳይበገሩ፡ ይህን እውነታ፡ በግብር ያረጋገጡ ሕዝቦችን፡ በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል።

## ስለሃይማኖታዊው ሥነ ምግባር፡ የሕዝቦች፡ የተለያየ ግምት።

በመካከለኛው ምሥራቅ፡ ኢራቅ፡ ኩዌይትን በወረረች ጊዜ፡ አሜሪካውያንና ምዕራባውያን አገሮች፡ በነዳጅ በኩል ያላቸውን ጥቅም ለመጠበቅ ሲሉ፡ የቃል ኪዳን ጦር አደራጅተው፡ ኩዌይትን በመርዳት፡ ጎረቤቲቱን፡ ሳዑዲ ዓረቢያን ጭምር፡ ከወረራው ማትረፋቸው ይታወሳል። ይህን በመሰለው እርዳታቸው፡ ሊዋጉላቸው፡ ወደእነዚሁ የእስልምና አገሮች የሄዱትን፡ አሜሪካንና የጦር ጓደኞቿን፡ ሳዑዲ ዓረቢያ፡ በቅድሚያ ካስገባቻቸው ግዴታዎች መካከል፡ ሃይማኖታውያን የኾኑ፡ የጸሎትም ኾነ የሰንደቅ ዓላማ፥ ወይም የበዓል ሥርዓቶቻቸውን፡ በምንም መንገድ በምድሩዋ ላይ ላይፈጽሙ ነበር። ይህም ማለት፡ "እናንተ ክርስቲያኖች፡ የክርስትና ሥርዓታችሁን፡ በእስልምና ምድራችን ላይ ከምትፈጽሙ ይልቅ፡ እስላሙ ጠላታችን ኢራቅ ወርራን፡ አገራችንን ብትይዝ ይሻለናል!" በማለት፥ ቅድሚያውን፡ ለሃይማኖታቸው መስጠታቸው ነው። በተቃራኒው ደግሞ፡ አሜሪካና ምዕራባውያን ተባባሪዎቿ፡ "እናንተን ሳንረዳ፡ ሃይማኖታችንን ከምናስከብር ይልቅ፡ ለገንዘብ ጥቅማችን ስንል፡ ሃይማኖታችን ቀርቶ፡ እናንተን ብንረዳ ይሻለናል!" ማለታቸው ነው።

ምሥራቃውያንና ምዕራባውያን፡ ስለሃይማኖት ያላቸው አስተሳሰብና ግምት፡ እንግዲህ፡ በዚህ ተለይቶ ይታወቃል:: በአሜሪካና በቀሩት የምዕራባውያን ግፊት፡ "በኢትዮጵያ፡ የሕዝባዊ አገዛዝ ሥርዓት (democracy ዲሞክራሲ) መስፈን አለበት!" ተብሎ፡ ለዚህ ትውልድ፡ ይህን ያህል፡ ነጋሪት የሚደለቅለት፡ ለምን እንደኾነ፡ በቀላሉ መመልከት ነው::

የሳዑዲ ዓረቢያ ሕዝብ፡ ከአሜሪካውያንና በጠቅላላ ከምዕራባውያን ጋር ያለው ግንኙነት፡ ያው፡ በገንዘብ ላይ የተመሠረተ ኾኖ፡ የቱን ያህል፡ የጸና እንደኾነ፡ በይፋ ይታወቃል:: ይኹን እንጂ፡ ግንኙነቱ፡ እንዲህ፡ እጅግ የተቀራረበ እንደመኾኑ፥ አገሩም፡ በፈረንጆቹ የሥልጣኔ ምርት እንደመጥለቅለቁ መጠን፡ ሕዝቡ፡ በሃይማኖቱ ላይ የተመሠረተውን፡ ሥነ ምግባሩን፥ ቋንቋውንና ፊደሉን፥ አለባበሱንና ሌላውን ባህሉን፡ በይበልጥ አጠናከረ እንጂ፡ በምንም መንገድ አልለወጠም::

ኢትዮጵያም እኮ፡ እስከዚህ፡ እስከዛሬው ትውልድ ድረስ፡ እንደዚህ ነበረች:: ያውም፡ በሺሆች ዓመታት ለሚቆጠር ዘመን:: ዛሬ ግን፡ ይህ ትውልድ፡ ከላይ የተጠቀሱትን፡ የአባቶች፡ ምሳሌያዊ ቃላት፡ ባለማጤንና ባለማስተዋል፡ ወይም፡ ቸል በማለት፡ ወይም በመናቅ፡ እንኳንስ፡ ዓበይት የኾኑትን የተከበሩ ውርሶቹን ሊያንከባክብ ይቅርና፡ ጥቃቅንና ተራ የኾኑትን እንኳ መጠበቅ አቅቶት፡ ይኸው፡ ጨርሶ ለመውደቅ፡ ሲፍገመገም ይታያል:: ጥቃቅንና ተራ መስለው ከሚታዩት፡ ከእነዚህ፡ ውርሶች መካከል፡ ጥቂቶቹን፡ ከዚህ በታች፡ እንመለከታቸዋለን::

## ኢትዮጵያ፡ ስለመከባበር ባህሏ፡ ትውልዷን ስትፋረድ!

የኢትዮጵያውያን፡ አንዱ መልካም መታወቂያቸው፡ ከ"አንተ!" እና "አንቺ!" ይልቅ፡ ወደ "አንቱታ" ደረጃ ከፍ ይል የነበረው፡ የመከባበር ባህላቸው "ነበር"፤ (ወይስ፡ ባህሉ፡ ገና ሕያው ከኾነ፡ "ነው" እንበል:: እየኾነ በሚታየው ከኾነ፡ "ነበር" ከማለት የተደረሰ ይመስላል፤ ወይስ፡ ጥቂት የቀረ፡ "ገና" ይኖር ይኾን?) ዛሬስ፡ ይህ ባህል፡ በምን ኹኔታ ላይ ይገኛል?

በዕድሜ፡ ታላቅ ወይም አረጋዊ የኾነ ሰው ሲመጣ፡ "ነወር!" (በግእዝ፡ 'ንበር!'፥ ሲተረጐም፡ 'ተቀመጥ!') በማለት፡ ከተቀመጡበት ብድግ ብሎ፡ አክብሮትን የመግለጽ ሥርዓት ባሁኑ ጊዜ ይታያል ወይ? ከመነኮሳትና ከሚጠመጥሙ ካህናት ወይም አረጋውያን በቀር፡ ለወንድ፡ በራስ ላይ ቆብ፡ ኮፊያ ወይም ባርኔጣ ደፍቶ፡ ወይም ተከናንቦ ወደመኖርያ ቤት ወይም ወደመሥሪያ ቤት መግባት፥ በስብሰባ ወይም በሸንጎ ላይ መቀመጥ፥ ያንንም፡ ከራስ ላይ ሳያወልቁ ሰላምታ መስጣጣት፡ ከባህላችን ውጭ ነው፤ በባህላችን፡ ይህ እንደነውር ይቆጠራል::

እንደነውር፡ ወይም እንደብልግና ስለሚቆጠሩ፡ በይፋ የማይነገሩ ቃላት ነበሩ:: ዛሬስ እንደተጠበቁ ናቸው? ወይስ እንደፈረንጆቹ፡ "ነውር!" ወይም "ብልግና!" የሚባል ነገር ቀርቷል?

## ኢትዮጵያ፡

የሥጋ ወላጆችን፥ ወንድሞችንና እህቶችን ብቻ ሳይኾን፡ አዛውንቶችን ወንዶች፡ "አባባ" ወይም ታላላቆችን፡ "ጋሼ"፥ አዛውንቶችን ሴቶች ደግሞ፡ "እማማ" ወይም ታላላቆችን፡ "እትዬ" ብሎ የመጥራቱ መልካም ባህላችን፡ ደብዛው ሳይቀር፡ እየጠፋ መኼዱን፡ ይኸው፡ እየተመለከትን አይደለምን? ነገር ግን፡ በዚህ ፋንታ፡ በባዕዳን ቋንቋ፡ Father! (ፋዘር!)፥ Mother! (ማዘር!)፥ Brother! (ብራዘር!) Sister (ሲስተር!) እያሉ መጥራት፡ በኅብረተሰቡ መካከል፡ የቱን ያህል ተስፋፍቶና ሰፍኖ እንደሚገኝ፥ ይህም፡ በኅብረተሰቡ ዘንድ፡ ሙሉ ተቀባይነትን አግኝቶ፡ ተጠሪዎቹም፡ በደስታ፡ ወንዶቹ፡_"ወይ!" ወይም "አቤት! አብ የት? ማለትም፡ (አብ፡ [አባቴ] የት?)"፥ ሴቶቹ፡ "ወይ!" ወይም "እመት! እም የት? ማለትም፡ (እም፡ [እናቴ] የት?" እያሉ፡ ፈጥነው መልስ በመስጠት ተባባሪነታቸውን ሲያረጋግጡ ይታያል።

ደግሞስ፡ ለየራሳቸው፡ ትክክለኛ ትርጉም ያላቸው፡ ቃላቶቻችን፡ ተዘውትረው፡ አለቦታቸው እየገቡ ሲሠራባቸው የሚደመጡ አይደለምን? ለዚህም፡ "ቆንጆ" ወይም "ቆንዦ" የሚለውን፡ አንድ ቃል ብቻ እንኳ፡ ለምሳሌ ያህል ብንወስድ፡ ይህ ቃል፡ ለመልክ፥ ያውም፡ ለሴት፥ ያውም፥ ለልጃገረድ ብቻ የሚውል ሲኾን፡ ባሁኑ ጊዜ፡ ግን፡ ወሰን ሳይኖረው፡ ለኹሉም ነገር፥ ባልተማረውም፡ በተማረውም፥ በወጣቱም፡ በአዛውንቱም እንደበት ሲነገር ይሰማል። ይልቁንም፡ ይህን የመሰለው አነጋገር፥ አጻጻፍና ድርጊት፡ ለመልካሙ ባህላችን፡ ባለአደራ ጠባቂ ናት ተብሎ በሚታመንባት፡ በቤተ ክህነቱ ሰዎች አካባቢ ሳይቀር መሰማቱ፡ የእውነተኞች ኢትዮጵያውያንን ልብ፡ የቱን ያህል፡ በኀዘን እንደሚሰብር መግለጡ ያዳግታል።

## ኢትዮጵያ፡
## ስለሰላምታ አሰጣጧ ሥርዓት፡
## ትውልዷን ስትፋረድ!

ለሰላምታ፡ በትሕትና የሚደረገው፡ "እጅ መንሣት"፡ የሚገኝበት ኹኔታ፡ እንዴት ነው? አዎን! ባሁኑ ጊዜ፡ በተለይ፡ ይህን ጉዳይ ማውሳቱ፡ የኾነውን ኹሉ እንደማያውቀውና እንደአልሰሚው እንግዳ ብቻ ሳይኾን፡ እንደቂል የሚያስቆጥር መኾኑን፡ ሳላውቅ ቀርቼ አይደለም፡ ይህን ሐተታ፡ እዚህ ላይ ያቀረብሁት። አውቄ ነው! የበኩሌን ግዳጅ በመወጣት፡ ይህ፡ የእጅ መንሣት አርእስተ ጉዳይ፡ ሊታሰብበት የሚገባ፡ ቁም ነገር ስለኾነ፡ በመጠኑም ቢኾን እንነጋገርበት ብዬ ነው።

## የእጅ መንሣት ሥርዓት፡
## ትርጓሜና ሐተታ።

የኢትዮጵያውያን የሰላምታ አሰጣጥ፡ ስያሜው፡ "እጅ መንሣት"፥ ሥርዓቱም፡ ራስን፡ ከአንገት፡ ወደፊት ከመቀለስ ጀምሮ፡ በደረጃ፡ እስከወገብ ዝቅ እስከማድረግ በሚደርስ እንቅስቃሴ የሚፈጸመው፡ ለምን እንደኾነ፡ በቅድሚያ፡ ባጭሩ ማብራራት ያስፈልጋል። ይህን በመሰለው ሥርዓት፡ እኛን የሚመስሉት፡ በባህላዊው ሥነ ምግባራቸው ጥበቃ፡ በዓለም ሕዝቦች ዘንድ ታውቀው የሚደነቁት፡ ጃፓኖች ናቸው።

የ"እጅ መጨባበጥ" ሰላምታ: ወደአገራችን ገብቶ: በባለቤቱ: በእጅ መንሣት ሥርዓት ላይ: መሠልጠን የጀመረው: በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመን: በተለይም: ከፋሺስት ጣልያን ወረራ በኋላ መኾኑ: ግልጽ ነው:: ይህ: የእጅ መጨባበጥ ልማድ: የእኛ ሳይኾን: የባዕዳኑ: የምዕራባውያን መኾኑ: በኹሉ ዘንድ ይታወቃል:: ጥንት: ሮማውያንና ሌሎቹ: በአረማዊነት የነበሩት: የአውሮጳ አሕዛብ: ሰላምታ ይለዋወጡበት የነበረ ልማድ እንደኾነ ይነገራል:: የዛሬው የኢትዮጵያም ትውልድ: በአሁኑ ጊዜ እንደሚያደርገው: እንደሌላው ኹሉ: ይህንንም: ለሰላምታ: በእጅ የመጨባበጡን ልማድ የቀዳው: ከእነርሱ ነው::

በዓለም ላይ የነበሩ የአሕዛብ መንግሥታት: በትረ ሥልጣን ይይዙ፥ የበላይነታቸውን ያጠናክሩና ግዛታቸውን ያስፋፉ የነበሩት: በአካለ ሥጋ ጉልበት፥ በሠራዊት ብዛትና በመሣሪያ ጥራት: በጠቅላላ: በጦር ኃይል ትጥቅ: በተሟላ ድርጅት ስለነበረ: ያን ትምክህታቸውን: በግልም ኾነ: በአገር ደረጃ የሚያሳዩት: በክንዳቸው ጥንካሬ ነበረ፤ እንዲያ በመኾኑ: ወዳጃቸውን: "ወዳጅነትህን ብታጸና: በዚህ ኃይል እጠብቅሃለሁ!"፥ ጠላታቸውንም: "ጠላትነትህን ብትቀጥል: በዚህ ኃይል አጠፋሃለሁ!" ለማለት: ወዳጃቸውንም፥ ጠላታቸውንም ሲገናኙ: እጁን ይጨብጡታል:: አረማውያን: የጠላታቸውን ወይም የራሳቸውን መሸነፍ፥ መማረክ ወይም መገዛት የሚያሳዩትና የሚያረጋግጡት: ጠላታቸው: "እጁን ሲሰጣቸው" ወይም እነርሱ "እጃቸውን ሲሰጡት" እና እነርሱም: "እጁን ሲቀበሉት" ወይም እርሱ: "እጃቸውን ሲቀበላቸው" እንደነበረ ይነገራል::

ደግሞም: አንድ ሰው: የሌላን ሰው እጅ በመጨበጥ: በራሱ ላይ ሊያስከትል የሚችለው ጣጣ እጅግ ብዙ ሊኾን ይችላል:: ምክንያቱም: በዚያ እጅ: ምን እንደተሠራበትና እንደሚሠራበት፥ ምን እንደተያዘበትና እንደሚያዝበት ስለማይታወቅ ነው:: ያ እጅ: ለክፉ ወይስ ለበጎ፥ ለርኵሰት ወይስ ለበረከት፥ ለሞት ወይስ ለሕይወት፥ ለዲያብሎስ ወይስ ለክርስቶስ አገልግሎት ውሏል? ማንም አያውቅም:: የራስን እጅ: ለዚያ: ለሌላው ሰው እጅ አሳልፎ መስጠት እኮ: "እኔም: በዚያ እጅ ሥራ ተባብሬአለሁ!" ማለት መኾኑን: አደራረጉ ራሱ ይመሰክራል::

ከኹሉም ይልቅ: ሊታወቅ የሚገባው: በኢትዮጵያውያን ዘንድ: "እጅ መስጠት" ማለት: "መሸነፍ፥ መማረክ" መኾኑ ነው! በሰልፍ ላይ ያለ ጠላት ድል መኾኑ የሚረጋገጠው: "እጅህን ስጥ!" ሲሉት: "እሺ!" ብሎና መሣሪያውን ጥሎ: እጁን ሲሰጥ ብቻ ነው:: ማናቸውም ሰው: ተማርኮ: እጁን የሚሰጠው ደግሞ: ለ"ጠላት" ነው:: ለእውነተኛ ኢትዮጵያዊ "እጁን ስጠ!" መባል: የመጨረሻው ውርደት ብቻ ሳይኾን: የሞት ሞትም ነው:: በምንም መልኩ አያደርገውም::

"መሸነፍና መማረክ"ም: በጦር ሜዳ ላይ ብቻ አይደለም:: በሰላሙ ጊዜ: ጠላት የሚዋጋበት መሣሪያ: እንደዛሬው ኹሉ: ሃይማኖት ከኾነ: ሃይማኖቱን: እስከሞቱ ድረስ አይለውጥም፤ ገንዘብ ከኾነ: በዚያ ገንዘብ አይደለልም፤ ወይም በእውቀት፥ በጥበብና በሥልጣኔ ከኾነ: በዚያም ውበት፥ ተድላና ደስታ ተታልሎ አይጠመድም:: አይሸነፍም፤ አይማረክም:: ማለትም: *"እጁን አይሰጥም!"*

ታዲያ! ዛሬ: እንዲህ ያለ: እውነተኛ ኢትዮጵያዊ አለን? ኢትዮጵያዊትስ አለችን? እስቲ: እያንዳንዱ: በእግዚአብሔር እውነት መንፈሳዊ መነጽርነት: እየራሱን ይመርምር!

ስለዚህ: የቀደሙት ኢትዮጵያውያን: በልዩ ልዩ ምክንያት: ሰላማውያን መስለው: ወደአገራችን እየመጡ፥ ለእነርሱም እጃቸውን: በሰላምታ መልክ እየሰጡ የተቀበሏቸውና በመልካም ያስተናገዷቸው ባዕዳን: የኋላኋላ ተለውጠው: አደገኞች ጠላቶቻቸው እየኾኑ ስላገኟቸው: "እንግዴህ ወዲህ: እጅህን ለጠላትህ አትስጥ!" ለማለት: ለሰላምታቸው: "እጅ መንሣት!" የሚለውን ስያሜ መስጠታቸው: ግልጽ ነው:: ይኸው ስያሜ ጸድቆ: እነሆ: ከዛሬው ዘመን ደርሷል::

ከላይ ለተጠቀሰው: የደረሰ ድርጊት: ምሳሌ ይኾን ዘንድ: የሚከተለው: የዜና መዋዕል ቅንጫቢ ቀርቧል፥ ይኸውም: የእስላሙን: የግራኝ አሕመድ: የወረራ ጦርነት ለመቋቋም ይረዱ ዘንድ: ተጋብዘው: ወደኢትዮጵያ የገቡት: ፖርቱጊዞች: ተልእኳቸውን ቀይረው: "የካቶሊክን ሃይማኖት ካልተቀበላችሁ" ብለው: ኢትዮጵያውያንን ለማስገደድ በመሞከራቸው: የእርስ በርስ ጦርነት ተነሥቶ: ደም እስከመፋሰስ ደርሶ እንደነበረ የሚያዘክረው: የቅርቡ ትዝታ ነው::

ኢትዮጵያውያን: ለሌላው ሰው: ሰላምታቸውን ሲያቀርቡ: "እጅ የሚነሡት": እንደሌሎቹ የባህል ሥርዓቶቻቸው ኹሉ: ከፈጣሪያቸው የተቀበሉትን መመሪያ ተከትለው: ስለትሕትና እንጂ: ራስን በማዋረድ: የዝቅተኛነት፥ የአገልጋይነት: ወይም የተገዢነት ምልክት አድርገውት አይደለም:: ይህም መመሪያ: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ: ስለትሕትና: በቃል ወይም በሰላምታ አሰጣጥ ብቻ ሳይኾን: በግብርም ፈጽሞ: ለደቀ መዛሙርቱ ያስተምራቸው ዘንድ: ከእነርሱ በሚለይባት: በመጨረሻዪቱ ምሽት: እግሮቻቸውን ካጠበ በኋላ: *"እኔ ለእናንተ እንዳደረግሁ: እናንተ ደግሞ ታደርጉ ዘንድ: ምሳሌ ሰጥቻችዋለሁና!"* ሲል በተናገረው ቃሉ ላይ [፲፱] የተመሠረተው ሥርዓት ነው::

ሰላምታውም: ለእኩያ: አንገትን ቀለስ በማድረግ ብቻ: በዕድሜ: በአገልግሎትና በማዕርግ ለሚበልጡ ታላላቆች ግን: ከአንገት ብቻ ሳይኾን: በደረጃ: ከወገብም ጭምር: ራስን በማስጐንበስ የሚደረግ: የትሕትና መግለጫ ነው:: በመንፈሳዊ ኾነ በሥጋዊ ፍቅር የተወደጁ: ወይም የተዛመዱ ቤተሰቦች፥ ቤተ ዘመዶችና ወዳጆች: እንደየፍቅራቸውና ቅርበታቸው: ትከሻ ለትከሻ፥ ከዚያም አልፎ: ጕንጭ ለጕንጭ እስከመሳሳም የሚደረስበት ሰላምታ አለ:: የሥጋ: የመንፈስ: የትምህርትና የመሳሰለው አባቶችንና እናቶችን: አያቶችንና አረጋውያንን: ዝቅ ብሎ ጉልበት እስከመሳም የሚደርሰው የትሕትና ሰላምታ: ምርቃትንና በረከትን የሚያስገኝ መኾኑ: ሊዘነጋ አይገባም::

## የሰላምታ ቃሎቻችን: መልእክት አላቸው::

ስለዚህ ኢትዮጵያውያን: ሰላምታቸውን ለሌላው የሚያቀርቡት: እግዚአብሔር: ለእርስዎ፥ ለእናንተ፥ ላንተ ወይም ላንቺ: "ጤና ይስጥልኝ!" ብለው: እጅ በመንሣት እንጂ: "ታዲያስ! ሰላም!" ብለው: እንደባዕዳንና እንደአሕዛብ: "እጅ በመስጠት" እና "የሌላውን በመጨበጥ": ወይም: "Hi! Hi!" (ሃይ! ሃይ!) እያሉ፥ አንድ እጅን: ወደላይ ዘርግቶ በማወዛወዝ አይደለም::

ለሌላውም: ሰላምታ ላቀረበላቸው: አጸፋውን የሚመልሱት: "እግዚአብሔር ይመስገን! እኔ ደህና ነኝ!" ብለው: አሁንም: "እጅ በመንሣት" እንጂ: እንደባዕዳንና አረማውያን: እጅን እንደሰጡና እንደተጨባበጡ: "ደህና! ደህና!" በመባባል ብቻ አይደለም:: ለተደረገላቸውም ውለታ: "እጅ እየነሡ": "እግዚአብሔር ይስጥልኝ!" ይላሉ እንጂ: እንደሃይማኖተ ቢሶች: የሌላውን እጅ በመጨበጥ: "አመሰግናለሁ!" አይሉም:: ሲለያዩም: እግዚአብሔር: "ጤና ይስጥልኝ! በደህና ዋሉ!" ብለው: እጅ በመንሣት እንጂ: እንደባዕዳኑ: "Chiao! Chiao!" ("ቻው! ቻው!") የሚለውን የጣልያንኛ ቃል: ወይም: እጅን ወደላይ እያነሡ: "Bye! Bye!" (ባይ! ባይ!) የሚለውን የእንግሊዝኛ ቃል በመለዋወጥ አይሰነባበቱም::

እንግዲህ: በዘመናዊው የኪነ ጥበብ ሥልጣኔ እጅግ የተራመዱት ጃፓኖች እንኳ: "እጅ በመንሣት" ያቆዩትን: የሰላምታ አሰጣጥ ባህላቸውን እንደያዙ: በማንነታቸው: ለመቀጠል ሲችሉ: በነጻነት ህልውናችንና በአገር ሕዝብነታችን: የረዥም ዕድሜ ቅድሚያ ያለን: እኛ: ኢትዮጵያውያን ግን: በሰላምታ እያስመሰልን: ለባዕዳን: እጃችንን በመስጠታችን: ከአባቶቻችንና ከእናቶቻችን: ኑዛዜና ፈቃድ ውጪ: ራሳችንን: በሃይማኖት ሳይቀር ለጠላት ማስማረካችንንና ማስገዛታችንን፥ አገራችንንም: በጠላት አስወርረን: በገንዘብ ጭምር መሸጣችንን: በየዕለቱ: ለዓለሙ መመስከራችን መኾኑን ተገንዝበነዋልን?

## ኢትዮጵያ:
## ስለአለባበሷ ሥርዓት:
## ትውልዷን ስትፋረድ!

ስለአለባበሳችንስ! ፈጽመን: አውሮጳውያን: ወይም ምዕራባውያን: ወይም ፈረንጆች ኾነናል:: አይደለም እንዴ?:: ዘመናዊዉን ትምህርት ከተማርነው፥ ከጥራዝ ነጠቁና ከከተሜው መካከል: የአገራችንን ልብስ: ለዓውደ ዓመት እንኳ የምንለብሰው: ስንቶቻችን ነን? እጅግ ጥቂቶች ነን እኮ! ምናልባት: የመልበስ ፍላጎት ኖሮን: የምንለብስ ብንኖር እንኳ: አለባበሱን ስለማናውቅበት: አንድ ባዕድ የኾነ ሰው: "እንዲህ አድርገህ ልበሰው!" እየተባለ እንደሚነገረው ተዋናይ መስለን ነው የምንለብሰው::

## ባለቤቱ:
## በቤቱ ባይተዋር ሲኾን!

ይህ: የባዕዳኑ፥ የምዕራባውያኑ፥ የፈረንጆቹ የአለባበስ ባህል: በኢትዮጵያ: በሴቱም ኾነ: በወንዱ ዘንድ: እጅግ የተንሠራፋ መኾኑ በግልጽ ይታያል:: ለምሳሌ: ባለቤቱ: "ኩታ": በቤቱ: ባይተዋር ኾኖ: ይህንኑ ስሙን: ጥቂት ቀየር፥ መልኩን: ሰልከክ፥ ቁመናውንም: ሸንቀጥ አድርጎና እንግዳ ፈረንጅ ኾኖ: ከውጭ የተመለሰው: coat (ኮት) ወንድሙ: እነሆ: በባለቤቱ ቤት ሠልጥኖ ሲያዝዝ ይገኛል! በዚህም: ባለቤቱን: "ኩታን": በአገሩ ላይ በከፍተኛ ንቀትና ውርደት እንዲታይ አድርጎታል:: ("ኮት" የሚለው ቃል: "ኩታ" ከሚለው ተወስዶ: "ስፍ ኩታ" ማለት መኾኑን መመልከት ነው::)

## ኢትዮጵያ፡

ይህ ኹኔታ የሚታየው ደግሞ፡ በአለባበሱ ዘርፍ ብቻ አይደለም፤ "ኢትዮጵያዊ" የኾነውና "የፈረንጅ" ወይም "የባዕድ" የኾነው፡ ለንጽጽር፡ ወይም ለምርጫ በሚቀርቡበት መድረክ ላይ ኹሉ ነው እንጂ:: በአሁኑ ጊዜ፡ ከጥንታውያኑ፡ የዓለም አህጉር መካከል፡ በዘመኑ ትውልዱ ምክንያት፡ በአጠቃላይ ኹለንተናዋ፡ "ባለቤቱ፡ በቤቱ ባይተዋር፥ ባይተዋሩ፡ በሰው ቤት ባለቤት" የኾነበት አገር ቢኖር፡ ኢትዮጵያ፡ ኾና ትገኛለች::

### "ባለኩታው" ኢትዮጵያዊ፡ ሲናቅና ሲዋረድ!

የዘመኑን፡ ዓለማዊ ሥልጣኔ፡ እንደሃይማኖት በተከተለው ወገን ዘንድ፡ ከአገር ልብሱ ብቻ ሳይኾን፡ ከለባሹም ሰው ይልቅ፡ የክብሩን ቦታ የያዘው፡ የባዕዳኑ ልብስ ስለኾነ፡ የኢትዮጵያዊነት፡ አንዱ ምልክት የኾነውን፡ "ነጠላ" ወይም "ኩታ" ደርቦ መታየት፡ ለዚያ ሰው፡ በዘመናዊው ትውልድ ዘንድ፡ የመጨረሻውን፡ የውርደትና የንቀት ምልክት ተጎናጽፎ እንደመታየት የሚያስቆጥር ከመኾን ደረጃ ተደርሷል:: ይህንንም፡ "ባለኩታ"፥ ወይም "ኩታ ለባሽ" የኾነው፡ የዚህ መልእክት መጽሐፍ አዘጋጅ፡ ከዚህ ቀጥሎ በሠፈረው፡ በራሱ "ገጠመኝ" አረጋግጦታል::

ኹኔታው የደረሰው፡ በኩታውና በባለኩታው አገር፡ በኢትዮጵያ ላይ፥ በአገሩ፡ በኢትዮጵያ ስም በሚጠራው፡ አየር መንገድ ነው:: ወደባሕር ማዶ የሚበርርበትን፡ የጉዞ ወረቀቱን (ticket ቲኬት) ለማስቈረጥ፡ በመናገሻዪቱ ከተማ ውስጥ ካሉት፡ የአየር መንገዱ ጽሕፈት ቤቶች መካከል፡ በአንዱ እንደተገኘ፡ በተራው የተቀበለችው ጸሓፊ፡ ባለጉዳዩ ባልጠበቀው መልክ አነጋገራና የጉዞ ወረቀቱን አዘጋጅታ እስከሰጠችው ጊዜ ድረስ፡ ለአንድም አፍታ፡ ቀና ብላ፡ ዓይን ለዓይን ሳታየው፥ ከእርሱ ለቀረበላት የምስጋና ሰላምታም እንኳ፡ አጸፋውን በአግባቡ ሳትመልስለት አሰናበተችው::

እርሱም፡ "ይህ የኾነው፡ ለምን ይኾን?" እያለ፡ ሲያወጣ ሲያወርድ ከቆየ በኋላ፡ ጉዞውን ለመጀመር በሚሣፈርበት ዕለት፡ በአየር ማረፊያው ተገኝቶ ሣለ፡ በዚያ ክነበሩት የአየር መንገዱ ኀላፊዎች መካከል፡ አንዳንዶቹ፡ ይህን መንገደኛ፡ ለይተው አውቀውት ኖሮ፡ ተመካክረው፡ ከሚበርርበት፡ ከዝቅተኛው፡ የቈጠባ ክፍል፡ ወደከፍተኛው ባለማዕርግ ክፍል ተዛውሮ እንዲጓዝ ወሰኑ፤ ውሳኔውንም፡ በሚነግሩት ጊዜ፡ ያ፡ በማንነቱ ብቻ፡ በልዩ አክብሮት ይታሰብና ይገመት የነበረው ኢትዮጵያዊው መንገደኛ፡ በሰውነቱ ላይ፡ ያን ኩታውን ደርቦ፡ በታያቸው ጊዜ፡ አስተሳሰባቸውና ግምታቸው፡ በቅጽበት ተለውጦ፡ በዚያ አለባበሱ፡ በዚያ የማዕርግ ክፍል መገኘት፡ አግባብና ተስማሚ መስሎ ስላልታያቸው፡ ያን፡ ለእነርሱ፡ "የውርደት ማቅ"፥ ለእርሱ ግን፡ "የክብር ልብሱ" የኾነውን፡ ኩታውን ማውለቅ እንዳለበት እንዲነገረው ተደረገ::

እርሱ ግን፡ ይህን አሳብ ባለመቀበል፡ "ኢትዮጵያዊነት"፡ ወይም "ኢትዮጵያዊ ኾኖ መታየት"፡ በትውልዱ ዘንድ፡ ከምን ዓይነቱ፡ የግምት አዘቅት ውስጥ ተወርውሮና ተጥሎ እንደሚገኝ ባየበት፡ በዚህ ገጠመኝ እየተደነቀና እየተከዘ፥ እያዘነም፡ ያንኑ፡ የኢትዮጵያዊነቱን የክብር ምልክት እንደተጐናጸፈ፡ የ"ኢትዮጵያ"ን ስምና "የአንበሳ" ምልክቷን በተሸከመው ጥያራ (airplane)፡ የበረራ ጉዞውን መቀጠልን መረጠ!

የተመደበለትን፡ የበረራ ወንበር ይዞ በሚጓዝበት ጊዜም፡ ከአስተናጋጆቹ ይቀርብለት የነበረው የውስጥ መስተንግዶ፡ ከውጭዎቹ የተለየ አልነበረም፤ ገና ከመነሻው፡ ጋዜጣና መጽሔት እንኳ፡ ለመንገደኞች በትሕትና ሲቀርብላቸው፡ "ለእርሱ ይኼ ምኑ ነው? አያስፈልገውም!" ተብሎ ይሆን? እንጃ፡ ለእርሱ ብቻ ተነፍጎት ታለፈ!

ይህን የመሰለው ኹኔታ የሚታየው፡ የዕድሜ ወጣቶች በበዙበት፡ አየር መንገዱን በመሰሉ፡ ዘመናውያን አካባቢዎች ብቻ ሳይኾን፡ በዕድሜ ላቅ ባሉትም ዘንድ ጭምር፡ በባሰ መጠን፡ ሥር የሰደደ መኾኑን ለመጠቈም፡ ይኸው "ጨርቅ ለባሽ" ኢትዮጵያዊ፡ በሌላ አጋጣሚ፡ የደረሰበትን ተመሳሳይ ድርጊት፡ እንዲህ ሲል፡ ባጭር ያወጋል፡፡

## ሌላው አሳዛኙ አጋጣሚ፡፡

ምድሪቱ፡ ያው፡ የባለቤቱ፡ የኵታውና የባለኵታው አገር የኾነችው፡ ኢትዮጵያ+ ከተማዪቱም፡ ያቺው፡ አዲስ አበባ ናት፤ የሚርመሰመሱትም፡ የኵታውና የባለኵታው ወገኖች፡ ኢትዮጵያውያን ናቸው፤ ቦታው፡ ወደውጭ አገር ለሚጓዙ መንገደኞች፡ የኬላ ደብተር (Passport = ፓስፖርት) እና የይለፍ ፈቃድ የሚሰጥበት፡ የአገሪቱ መንግሥት መሥሪያ ቤት ነው፤ ባለጉዳዩ፡ ብዙ ነው፡፡ እዚያ፡ ከወንዱም ከሴቱም መካከል፡ ያገሩን ሸማ ተጎናፅፎ የተገኘው፡ እርሱ፡ "ባለኵታው" ብቻ ነው፡፡ ከባለጉዳዩም+ ከሠራተኛውም፡ ኹሉም፡ እርስ በእርሱ ሲተያይና ሲነጋገር፡ እርሱን ግን፡ አንድም ሰው፡ ቀና ወይም ዘወር ብሎ የሚያየው የለም፡፡ ጥቂት እንደቆየ፡ ይኸው ባለኵታ፡ እጥላ ሥር ቆሞ የተራ ጥሪውን በሚጠባበቅበት ጊዜ፡ ከባለጉዳዮቹ መካከል፡ እርሱን በጣም የሚያውቀው+ እንዲያውም፡ በደርግ እሥር ቤት፡ ከሰባት ዓመታት ለኾነ ዘመን፡ አብሮት የነበረ፡ የመከራ ጓደኛው፡ ወደእርሱ አቅንቶ ሲመጣ አየው፤ ደስ ብሎት፡ ሰላምታ ሊሰጠው፡ ዓይን ዓይኑን እየተመለከተ ሲጠባበቀው ሣለ፡ ከፊቱ ሲደርስ፡ ሌሎቹን ኹሉ፡ አንድ በአንድ እያማተረ አይቶ፡ እርሱን ሳያየው፡ እጥፍ ብሎ ይራመድ ጀመር፡፡

ያ የመከራ ጓደኛው፡ ወዲያ ወዲህ ይል የነበረው፡ በእርሱ፡ በባለኵታው አጠገብና ፊት ለፊት ስለነበረ፡ "ይህን ያህል፡ ሲመላለስ፡ በአጋጣሚ እንኳ፡ እንዴት ወደእኔ ቀና ብሎ አይመለከትም! እንዴት ሳያየኝና ዝም ሊለኝ ይችላል! አይቶ እንዳላየ መኾኑ ይኾን? በከባድ አሳብ በመዋጡ ይኾን? አልፎ አልፎ ደግሞ፡ ሌሎችን ያነጋግራል፤ በእኔ የተቀየመበት ነገር ይኖረው ይኾን? ወይስ ከእግር እስከራሱ፡ በምዕራባውያን የከበረ ልብስ ተከናውኖና ተሽቀርቅሮ ስለነበረ፡ እኔን፡ ፡ጨርቅ ለባሽ+ ገጠሬ ነው፡ ብሎ መናቁ ይኾን? አይ! ነጠላ መልበስ፡ ወይም ባላገርነት፡ እንዴት ሊያስንቅ ይችላል?" በማለት፡ ሲያወጣ ሲያወርድ፡ ምናልባት፡ ከእኩል ሰዓት በላይ የኾነ ጊዜን አሳለፈ፤ በመጨረሻ፡ "ሳንነጋገር ቢኼድ ይቆጨኛል! በእርሱ በኩል ጎደለ ብዬ፡ የእኔን ግዴታ መተው የለብኝም!" ብሎ፡ ይህ ጉደኛ ጨርቅ ለባሽ ኢትዮጵያዊ፡ ያ፡ ወዳጁና የእሥር ጓደኛው፡ ከአጠገቡ ሲደርስ፡ "አቶ ጌታቸው!" ብሎ ሲጠራው፡ ቀና ብሎ አይቶ፡ "ውይ! ንቡረ እድ?! እርስዎ ነዎት እንዴ! አላየሁዎትም ነበርእኮ!" ብሎት፡ ሰላምታ ተለዋውጠውና ተጨዋውተው ተለያዩ! እኒያ ሰው፡ አቶ ጌታቸው ማኀተመ ሥላሴ ይባላሉ፡፡

## ኢትዮጵያ:

# የአንድ ኢትዮጵያዊ: የጀግንነት ድርጊት::

የአጼ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት: በተለይ: ፋሺስት ጣልያን: ከኢትዮጵያ ከተባረረ በኋላ: ለፈረንጆቹ አለባበስ: አክብሮትን፥ ቅድሚያንና ብልጫን ሲሰጥ: ኢትዮጵያዊውን የአለባበስ ሥርዓት ግን: በራሱ ሕዝብ ዘንድና በራሱ አገር ሳይቀር: ምን ያህል: ለውርደት፥ ለጥቃትና ለንቀት እንደዳረገው የሚያሳየውን እውነተኛ ተውኔት እንመልከት!

በዚህ ነገር: እጅግ የሚቆጭ: አንድ እውነተኛ የታወቀ ኢትዮጵያዊ: በአንድ ብሔራዊ በዓል ምክንያት በተዘጋጀ የቤተ መንግሥት ታላቅ ግብር ላይ እንዲገኝ: የግብዣው ወረቀት ስለደረሰው: ጸዓዳ የኾነ የአገሩን ልብስ ለብሶ: ልክ በሰዓቷ ሲደርስ: በቤተ መንግሥቱ ግቢ: የውጭ በራፍ ላይ ቆመው: በተጨናነቀው ደጀጠኚ መካከል: ተጋባዡን የሚያስተናግዱት አጋፋሪዎች: እንኳንስ በአክብሮትና በትሕትና ተቀብለው: ወደውስጥ ሊመሩት ይቅርና: ዘወር ብሎ የሚያየውና የሚያሳልፈው ሰው እንኳ አጣ! በእጁ እየጠቀሰና እየጮኸ ቢጣራም: የሚያዳምጠውና ቁም ነገር የሚሰጠው አላገኘም::

“መቼም: እዚህ ድረስ መጥቼ አልመለስም!” ብሎ፥ እንደምንም ተጋፍቶ: ከአጋፋሪዎቹ ዘንድ ደረሰና: ለመግባት ዘው ሲል: አንዱ አጋፋሪ: በድፍረቱ ተገርሞና ተናዶ: “እንዴት አንተ!” ብሎ ወደኋላው በኃይል ገፈተረው! መገፍተር ብቻ ሳይኾን: በያዘውም ሽመል ዠለጠው! ኢትዮጵያዊውም ተጋባዥ: በዚህ እጅግ ቢያዝንም: ተስፋ ሳይቆርጥ: “እኔ: እከሌ ነኝ እኮ! ወይም ለእልፍኝ አስከልካዩ ንገሩልኝ!” ብሎ: የበደለውን አጋፋሪ: በጽሙና ቢማጸነውም: “ኧ! ምን? ደሞ፥ 'እኔ እከሌ ነኝ' ይለኛል!? የማን ቀልደኛ ነህ? ኺድ ወዲያ!” ብሎ እንደገና ሊያጉላላው ሲሞክር ሽሽት ብሎ: ቆሞ ይመለከት ጀመር::

በዚህ መካከል: ጓደኞቹ ባለሥልጣኖች: በፈረንጆቹ አለባበስ ተከውነው ሲመጡ: ገና ከሩቁ: አጋፋሪዎቹ: ተጣድፈው ኼደው: እጅ ነሥተው: ተቀብለው: መንገዱን እየከፈቱላቸው፥ ከፊትና ከኋላም አጅበው: በክብር ሲያስገቧቸው: ይኸው “ኩታ ለባሽ” ተጋባዥ: በመገረም: ዝም ብሎ ይመለከት ነበር እንጂ: ከእነርሱ: አንዳቸውን እንኳ ጠርቶ: ለአጋፋሪዎቹ እንዲነግሩለት አልሞከረም፤ ይህን ለማድረግ: ቀድሞውንም አሳብ አልነበረውምና!

በዚህ ኹኔታ መቆየቱ: ሌላ የባሰ ችግርን መጋበዝ እንጂ: ሌላ ምንም የሚጠቅም ነገርን የማያስገኝ መኾኑን ሲያረጋግጥ: የግብዣው ሰዓት በጣም እንዳያልፍበት: ለተሽከርካሪ ነጂው: (chauffeur ሾፌር) ተገቢውን መመሪያ ሰጥቶ: በፍጥነት ወደቤቱ ኼደ፤ እንደሥራ ጓደኞቹ: ሳታሙንና ጥቁሩን የፈረንጆቹን የክብር ልብስ ለብሶና በዚያ አጊጦ ወደቤተ መንግሥቱ ቀልጥፎ ተመለሰ: እዚያም ሲደርስ: በዚያ: በሚያውቀውና ሲመለከት በቆየው አቀባበል: ገና ከሩቅ: መንገዱ እየተከፈተለት፥ ማንነቱም ሳይጠየቅ: በግራና በቀኝ እየተሰገደለት: ስተት ብሎ: ከግብሩ አዳራሽ ሲደርስ: የእልፍኝ አስከልካዮች: እጅ ነሥተውና በትሕትና ተቀብለው: ስሙ ወደተጻፈበት ወንበሩ መርተው: አስቀመጡት::

የግብሩ ሰዓት ደርሶ፡ አጼው በዙፋናቸው ላይ እንደተቀመጡ፡ ግብዣው ሲጀመር፡ ያ፡ ወደግብሩ እንዳይገባ ተከልክሎ፡ በውርደት የተባረረው፡ የፊተኛው ኢትዮጵያዊና ወደግብሩ እንዲገባ ተፈቅዶለት፡ በክብር የተቀመጠው፡ የኋለኛው ፈረንጅ፡ የሚቀርብለትን ምግብና መጠጥ እያነሣ፡ ለሰውነቱ ማጉረስና ማስጐንጨት ሳይኾን፡ ለዚያ ለልብሱ ብቻ ይመግብና ያጠጣ ጀመር፤ ማለትም፡ ልብሱን በምግቡ ይቀባ፥ መጠጡንም፡ በልብሱ ላይ ያፈስስ ጀመር።

እዚያም፡ በአጠገቡና በአካባቢው የተቀመጡት ተጋባዦች፥ ወዲያ ወዲህ የሚራወጡት አሳላፊዎችም፡ በድርጊቱ ተደንቀው እየተሣሣቁ ሣሉ፡ ድርጊቱን፡ ከሩቅ፡ በመገረም ይመለከቱ የነበሩት አጼ፡ ያ፡ የሚች ባለሚላቸው ልጅ፡ ለምን እንደዚያ እንዳደረገ፡ በእልፍኝ አስከልካያቸው አማካይነት ቢያስጠይቁት፡ "የተጋበዝኩት እኔ ሳልኾን፥ ወይም ኢትዮጵያዊ ሰውነቴ ሳይኾን፡ ይህ የተሸከምኩት የፈረንጅ ልብሴ ስለኾነ ነው!" ብሎ፡ መልሱን ሰጠ። ከዚያ አያይዞም፡ ቀደም ሲል፡ እንደብርሃን ፀዳል በነጣው፡ ኢትዮጵያዊ ልብሱ ተሸልሞ በመጣ ጊዜ፡ በዚያ ልብሱ ምክንያት ብቻ፡ በገዛ አገሩና በገዛ ቤተ መንግሥቱ አደባባይ፡ በገዛ ወገኖቹ፡ የደረሰበትን ውርደትና እንግልት፥ በኋላ ደግሞ፡ እንደጨለማ ድቅድቅ በጠቆረው፡ የፈረንጅ ልብስ ተሸንቅጦ በተመለሰ ጊዜ፡ የተበረከተለት አክብሮትና እንክብካቤ እንዴት እንደነበረ፡ ኹሉንም አስረዳ!

ያ ድርጊት፡ የዚያን ጊዜዪቱ ኢትዮጵያ፡ ሕዝቧን ይዛ፡ በምን ኹኔታ ላይ እንዳለችና ወደየትስ አግጣጫ እያመራች እንደኾነ፡ ዛሬ የደረሰባትን የውድቀት ፍጻሜ፡ በአጠቃላይ የሚያመለክት፡ ከጀግና አርበኛ የተሰጠ፡ ብርቱ የማስጠንቀቂያ ምልክት እንደነበረ ግልጽ ነው። ይህን የመሰለውን ጀብድ የፈጸሙት፡ ቆራጡ ኢትዮጵያዊ፡ የብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ልጅ፡ ብላታ ሢራክ እንደኾኑ ይነገራል።

## ኢትዮጵያዊው ልብስ፡ "ጸዓዳ" (ነጭ) የኾነበት ምክንያት።

ኢትዮጵያዊው የአለባበስ ሥርዓት፡ እንደማናቸውም ኢትዮጵያዊ ሥርዓት፡ የተመሠረተው፡ በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖት ላይ ስለኾነ፡ ለደስታም ኾነ ለኀዘን፡ ምንጊዜም፡ ነጭ የኾነበት፡ በቂ የኾነ የራሱ ምክንያት አለው፤ ይኸውም፡ ከሐሰት ጨለማ ወደእውነት ብርሃን፥ ከኃጢአት ባርነት ወደጽድቅ ነጻነት፥ ከዲያብሎስ ተገዥነት ወደእግዚአብሔር ልጅነት፥ በመጨረሻም፡ ከዘለዓለም ሞት ወደትንሣኤ ሕይወት የተሸጋገርን መኾናችን እንዲታወቅበት ታስቦ የተደረገ በመኾኑ ነው። አዎን! እኛ ኢትዮጵያውያን፡ ሰው ኾኖ፡ ፍጥረቱን ኹሉ ባዳነው፡ በእግዚአብሔር ልጅ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ድል አድራጊነት የተገኘውን፡ የዘለዓለምን ሕይወት ብርሃናዊ ጸጋ የተላበስን መኾናችንን ለማረጋገጥ ነው፡ በኀዘናችን ጊዜ ሳይቀር፡ ነጭ ልብስ የምንለብሰው፤ የሚች ቤተሰብም፡ በያንገታቸው፡ ነጭ ክር የሚያሥሩት።

የኩታው የአለባበስ ቅጥ፡ ለወንዶችም፥ ለሴቶችም፡ ይለያያል። በቤት፥ በውጭ፥ በሥራ ላይ ሲኾኑ፥ በእንግድነት፡ ወደሌላ ሰው ቤት፥ ወደማናቸውም መሥሪያ ቤትና የአገልግሎት ቦታ ሲገቡ፥ በቤተ ክርስቲያን፥ በቤተ መንግሥት፥ በደስታና ወይም በኀዘን፥ በመሳሰሉት አካባቢዎችና ኹኔታዎች ጊዜ፡ አለባበሱ፡ ለየራሱ፡ ልዩ መልክ አለው።

ይህንንም ኹሉ፡ እያንዳንዱ፡ በየቤተሰቡ ይማረዋል፤ በልማድም ያውቀዋል፡፡ ለምሳሌ፡ በኃዘን ወቅት፡ ለምልክት እንዲኾን፡ ሴቶቹ፡ ኩታውን አጥፈው፡ በጥለቱ በኩል በመከናነብ ይለብሱታል፤ ወይም፡ የኩታውን ጥለት፡ አንዱን ወገን፡ በወገባቸው ላይ ታጥቀው፡ ሌላውን ወገን ደግሞ ይከናነቡታል፤ ዋናዎቹ ኀዘንተኞች ግን፡ ወደአንገታቸው አጣፍተው፡ ከደረታቸው ላይ ይቋጥሩታል፤ ይህም "ማሸረጥ" ይባላል፡፡

እንግዲህ፡ ይህን የመሰለውን፡ ፍጹም የሠመረ ኢትዮጵያዊ የአለባበስ ሥርዓት ነው፡ የአጼ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት፡ ከራሱ፡ ከቤተ ምልክናው ጀምሮ፡ በቤተ ክህነቱና በቤተ ሕዝቡም ዘንድ ጭምር እንዲናቅና እንዲዋረድ+ እንዲጠላም ያደረገው፡፡ ይህንንም ያደረገው፡ አዎን+ ይኸው ነጩ ልብሳችን ቀርቶ፡ በእርሱ ቦታ፡ በአውሮጳውያንና በግብፃውያን ሥርዓት፡ ጥቁሩ ልብስ እንዲተካ+ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያንም፡ የክብር+ የበዓል+ የደስታና የኀዘን መግለጫ+ የማንነታችንና የምንነታችን መታወቂያ እንዲኾን ጭምር፡ በአዋጅ በማሳወቅ ነው፡፡

በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖቱና ሥርዓቱ ጸንቶ የሚገኘው፡ የኢትዮጵያ ቤተ ሕዝብ፡ ከከተሜው ይልቅ የገጠሩ፡ እስከዛሬና ዛሬም ቢኾን፡ እያደረገ እንደሚታየው፡ ነጭ ልብሱን ተጐናጽፎ የሚወጣው፡ በክብር+ በበዓልና በደስታው ቀን ብቻ ሳይኾን፡ በኃዘኑም ጊዜ መኾኑ፡ በቂ የኾነ፡ ሃይማኖታዊ ምክንያት እንዳለው፡ ከላይ ተገልጿል፤ ይህም ምክንያት፡ በዲያብሎስ መሣሪያነት የገባው ሞት+ ከመቃብርና ከሙስናው ጋር፡ "እነሆ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ተወገደ!" በማለት፡ ብርሃን ተጐናጽፈውና ነጭ ልብስ ለብሰው፡ ትንሣኤውን፡ ለእነማርያም መግደላዊት ያበሠሩት የመላእክቱ ምሥራች፡ ዛሬም መፈጸሙን፡ ፀዓዳ በኾነው በአለባበሱ ሥርዓት ተረጋግጦ ይታወቃል፡፡

አዎን! እያንዳንዱ፡ በሕይወተ ሥጋ ቋሚ የኾነው ምእመን፡ ያ፡ ከሥጋ ቁራኝነት ተላቅቆ ያረፈው ምእመን፡ "ሞት+ መቃብርና ሙስና ሳያገኘው፡ በክርስቶስ፡ የትንሣኤ ልጅ ኾኖ፡ ህልውናውን፡ በዘለዓለም ሕይወት በመቀጠል ይኖራል!" የሚል መልእክት ያለውን፡ የምሥራች ድምፁን ለመስማትና ለማሰማት፡ በፍትሐተ ጸሎቱ ሥርዓትና በቀብሩ በዓል ላይ፡ ነጭ ልብሱን ለብሶ ይገኛል፤ የሣልስቱና የዓርባው ቀኖች ሥርዓትም፡ በዚሁ፡ በክርስቶስ ትንሣኤና ዕርገት ምሥጢራት ላይ ተመሥርቶ የሚፈጸም ነው፡፡

## በዚህስ ምግባር፡ ተከታይ ያገኘው ማነው? ኢየሱስ ክርስቶስ ወይስ ዲያብሎስ?

የዛሬው ትውልድ ግን፡ በሌሎቹ ድርጊቶቹ ኹሉ እንደሚታየው፡ የሚሰማውና የሚከተለው+ የሚያደርገውም፡ አምላኩና መሪው ኢየሱስ ክርስቶስ ያለውንና ያደረገለትን ሳይኾን፡ የዚያን ተቃራኒ፡ ማለትም፡ ባዕድ የኾነውን፡ የዲያብሎስን ቃልና ተግባር መኾኑን፡ ይኸው በየድርጊቱ፡ በገሃድ እንመለከተዋለን፡፡ ይህ እውነታ፡ ከሌላው ኹሉ ጊዜና ኹኔታ ይልቅ፡ በይበልጥ፡ ተረጋግጦና ገዝፎ የሚታየው፡ ያው፡ በታወቀው፡ በለቅሶአችንና በኀዘናችን ጊዜ በሚለበሰው ጥቁር ልብስና በሚፈጸመው የዋይታ ድርጊት ነው፡፡

ይኸውም፡ "ሕያዋን ነን" የሚሉት፡ ቋሚ ወገኖቹ፡ በዚያ፡ በጥቁር ልብሳቸው ተሸፋፍነው፡ ያን፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ፡ የብርሃን ልብስ ተጎናጽፎና በብርሃናውያን መላእክት ታጅቦ፡ ወደዘለዓለም ሕይወት እየገባ ያለውን ወገናቸውን፡ ልክ፡ እጅና እግሩን ታሥሮ+ በጨለማም አጽፍ ተጠቅልሎ፡ ለዲያብሎስና ለሠራዊቱ ወደተዘጋጀው፡ ሲዖልና ገሃነም ሊገባ ሲኼድ፡ ተሰብስበው እየሸኙት መስለው መታየታቸው ነው።

በኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ በኀዘን ጊዜ ሳይቀር፡ ነጭ ልብስ ተለብሶ፡ የሚካኼደው የአለባበስ ባህል፡ ምክንያቱ፡ ይህ መኾኑ እየታወቀ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በቤዛነቱ መሥርቶ ያጸናውና የቀደሰው፡ ይኸው ኢትዮጵያዊ መልካም ሥርዓት፡ እንዲህ፡ ከኢትዮጵያ እየተወገደና በባዕዳን ጥቁር ልብስ እየተተካ+ የዲያብሎስ የኾነውም፡ ባዕዱ ልማድ እየሰፈነ እንዲኼድ መደረጉን፡ ባለቤቱ ኢየሱስ ክርስቶስና እናቱ ድንግል ማርያም ሲመለከቱ፡ መልእክታቸው ተቀባይ በማጣቱ፡ የቱን ያህል ያሳዝናቸው!?

እኛ "እምቢ!" ስንላቸው፡ በዚህ ረገድ፡ እናትና ልጁ፡ የሚያደርጉትን እስቲ እንመልከት! ታላላቆቹን ባለሥልጣኖች+ ከበርቴዎቹንና ምሁራኑን ሊያሳፍሩ፡ በሰው ዘንድ ከተናቁት+ በእነርሱ ዘንድ ግን ከከበሩት ኢትዮጵያውያን አማኞቻቸው መካከል፡ ወንዶችንና ሴቶችን ልጆች እያስነሡ፡ ኢትዮጵያውያን፡ ከእነርሱ፡ በሃይማኖት ያገኟቸውን ጸጋዎች ኹሉ፡ ለምሳሌ፡ ይኸው ግርማ-ሞገስ ያለው ነጭ ልብሳቸው+ "ኢትዮጵያ" የሚለው መጠሪያ ስማቸው+ አረንጓዴ፡ ቢጫና ቀይ ቀለማት ያለው፡ የቀስተ ደመና ሰንደቅ ዓላማቸውና ብቸኛ የኾነው ባለፊደል ቋንቋቸው፡ በመላው የዓለም ሕዝብ አደባባይ ላይ ሳይቀር፡ እንዲታወቅ+ እንዲከበርና እንዲወደድ ሲያደርጉ፡ የዛሬው ትውልድ፡ በገዛ ዓይኑ እያየ ነው። ለዚህም፡ በቅርቡ፡ በ፲፱፻፺፫ ዓ. ም. በሲድኒ፡ የአውስትራሊያ ከተማ በተካሄደው፡ "ኦልምፒያድ" በተባለው የጨዋታ ትእይንት ላይ የኾነውንና የተገኘውን የድል መጠን፡ በማስረጃነት መጥቀሱ ይበቃል።

## ኢትዮጵያ፡
## ስለቋንቋዋና ፊደሏ፡ ትውልዷን ስትፋረድ!

የቋንቋስ ነገር እንዴት ነው? ይህም፡ በሥነ ቃላት ተከናውኖ፡ በንግግር ለሚደመጠውና በሰዋስው ሥርዓት ታንጾ፡ በሥነ ጽሑፍ ለሚነበበው ቋንቋ፡ የህልውና መሠረቶቹ፡ ፊደልና አኀዝ (የቁጥር ምልክት) ናቸው። እነዚህ ሀብታት፡ "አገር" ተብሎ ለሚጠራ፡ ለአንድ ሕዝብ+ ወይም፡ ያ ሕዝብ፡ "አገር" ተብሎ ሊጠራ ከማይቻልበት ደረጃ ደርሶ በሚገኝበት ጊዜ፡ "የዚያ ሕዝብ ወገን ነው" የሚያሰኘውን ብቅዓት ይዞ የተገኘ፡ አንድ ሰው ካለ፡ ለዚሁ ግለሰብ፡ የማንነቱና የምንነቱ መታወቂያ ነው።

በዚህ መሠረት፡ ግእዝና ከእርሱ የተወለደው፡ ዐምሐርኛ የሚባለው ኢትዮጵያኛ፡ ከፊደላቸው፡ ከ"አበገደ" እና ከአኀዛቸው፡ ከ"፩-፪-፫-፬" ጋር፡ የኢትዮጵያውያን፡ የማንነታቸውና የምንነታቸው መታወቂያ ኾነው ኖረዋል! ዛሬም አሉ! ወደፊትም ይኖራሉ። የኢትዮጵያን ፊደል፡ ከነአኀዙ፡ ከሌሎቹ የዓለም ፊደሎችና አኃዞች የተለየ የሚያደርገው፡ አንዱ ባሕርዩ፡ ራሱን የቻለ፡ ምሥጢራዊ ትርጉም ያለው መኾኑ ነው።

## የግእዙን ፊደል: ከነአኀዙ ለማጥፋት
## የሚካኼደው ዘመቻ

ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ለማጥፋት የሚደክሙት: የጥንቶቹም÷ የመካከለኞቹም÷ የዛሬዎቹም ጠላቶቿ: የሚያተኩሩት: በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖቷ ላይ ብቻ ሳይኾን: ከነፊደላቸውና አኀዛቸው: የዚህች ሃይማኖት መታወቂያ÷ ማስተማሪያና መገለጫ በኾኑት: በግእዝና ኢትዮጵያኛ (ዐማርኛ) ላይ መኾኑን: የእነዚህ ሕያዋን ውርሶችና ቅርሶች ባለአደራ÷ ባለቤትና ተጠቃሚ የኾነው ቤተ ሕዝብ: አስቀድሞ አውቆ: ተገቢውን ጥንቃቄ እንዲያደርግ: ይህ ማሳሰቢያ÷ ማንቂያና ማስጠንቀቂያ እንዲሰጠው አስፈላጊ ኾኗል::

በአገር ላይ የመጣ: አንድን በሽታ ለማጥፋት: ሕጋዊ ታዋቂነትና የመሥራት ኀይል ያለው ድርጅት ተቋቁሞ: የዚያን በሽታ ተውሣክ ፈጽሞ ለማውደም በሚደረገው ዘመቻ ዓይነት: እነዚህንም የከበሩና የተቀደሱ: የኢትዮጵያ ሕያዋን ውርሶችና ቅርሶች: ደብዛቸውን ሳይቀር ለመደምሰስ: ባዕዳንና ያገር ውስጥ ጠላቶች: የያዙት ዘመቻ: የበሽታው ማጥፊያ ድርጅት ምሳሌ: "ዘየሐፅፅ" (የሚያንስ) ቢኾንበት እንጂ: አይበዛበትም::

ይህ ዘመቻ: በተደራጀና በተቀናጀ ኀይል: በሥርዓትና በይፋ መካኼድ የጀመረው: ያው: ለዚህ: ለባዕዳንና ለወገን ጠላቶች ደባ: በመሣሪያነት ባገለገለው: በአጼ ኀይለ ሥላሴ: ሰብአዊ መንግሥትና ዘመን እንደነበረ: በጊዜው "ይጠኑ!" እየተባሉ የተደከመባቸው: ፀረ ፊደል የኾኑ የዘመቻ ዕቅዶች: በብዛት ተመዝግበው ይገኛሉ:: ከእነዚያ መካከል: ዝርዝር ውስጥ መግባት ሳያስፈልግ: አንዱ ብቻ: ከዚህ በታች: በምሳሌነት ቀርቧል:የሚገርመው: እነዚያ ጥናቶች: "ፊደላቱና አኀዛቱ በዝተዋልና: ይቀነሱ!" በሚለው ግድያ ብቻ ሳይወሰኑ: "መኖራቸውም አያስፈልግምና: ጨርሰው ተወግደው: በእነርሱ ቦታ: የባዕዳኑ: በተለይም: የላቲኑ ቋንቋና ፊደል ቢተኩ ይሻላል" የሚል አሳብ ቀርቦ እንዲጠና መፈቀዱ ነው:: ሊላው የሚያስደንቀው ነገር: ይህ አሳብ: ወደጥናት ደረጃ ከፍ ብሎ መተሳለፉ ብቻ አይደለም፣ ለውሳኔ መቃረቡም ጭምር ነበር እንጂ::

እውነተኞች ኢትዮጵያውያን: በአጼ ኀይለ ሥላሴ ዘመን "ይኾናል!" ብለው የማያስቡት: ይህ: የቋንቋውና የፊደላቱ ነገር: በዚያን ጊዜ እንኳ: እስከዚህ ለውሳኔ አሰጣጥ ተዳርሶና እንደሊላው ጉዳይ ኹሉ: የኢትዮጵያ ቤተ ሕዝብና ቤተ ክህነት: በዝርዝር ሳያጠኑትና ሳይስማሙበት: በተቀነባበረ የጥድፊያ ጉባኤ ብቻ "ታይቷል" ተብሎ፥ በሥራ ላይ ሊውል ተቃርቦ እንደነበረ ሲያስታውሱት: ይዘገንናቸዋል:: ይኹን እንጂ: ያው ጉዳይ: ዛሬ: በኦሮሞው ብሔረሰብ ዘንድ: ለውሳኔ በቅቶና በይፋ ታውጆ: በሥራ ላይ እንዲውል ስለተደረገ: ከትዝብት ጋር የሚያሳዝናቸው ከመኾኑ በቀር: ይህን ያህል የሚያስደንቃቸው አልኾነም::

## ግእዝን: ከነፌደሉ ያተረፉ:
## ኢትዮጵያውያን ጀግኖች::

ይህንኑ ግእዝን፥ ኢትዮጵያኛ የኾነውን ዐማርኛን ጭምር: ከነፊደሉ: ማለትም: ከሆህያቱና አኀዛቱ ጋር: ያን ከመሰለ የቅትለት ዘመቻ ለማዳን: በዚያን ጊዜና ከዚያን በፊት: በየዘመናቱ: ታላቅ መሥዋዕትነትን ከፍለው: የቅርሱን ጥበቃ በመጽሐፍ ሳይቀር ከተዉልን መካከል: የቅርቦቹ: አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፥ አለቃ ደስታ ተክለ ወልድና አለቃ አስረስ የኔሰው: እዚህ ላይ ስማቸው ሳይወሳ አይታለፍም:: በተለይም: የኢትዮጵያ የቃል ኪዳን አምላክ: ከነእናቱ: ይህንኑ ሕያው ቅርስ: ከመጨረሻው የሞት ሞት ውሳኔ የሚያድኑ: ኹለት እውነተኞች ኢትዮጵያውያንን በማስነሣቱ፥ እነርሱንም አጠናክሮ: ያን ተልእኮ: ከግቡ እንዲያደርሱ በማድረጉ: በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነቱ የሚያምነው: ዛሬ ያለውና የወደፊቱ ተከታታይ የኢትዮጵያ ትውልድ: እግዚአብሔርን ሊያመሰግን ይገባል::

እኒያ: የኢትዮጵያ ታማኝ ልጆች የኾኑት: አባትና ልጅ: በቋንቋችን፥ በፊደላችንና በአኀዛችን ላይ ሊፈጸም የተዘጋጀውን: ያን: የሞትበቃ ፍርድ: አፈራርሰው ለማስቀረት የቻሉባት ኃይል: የእግዚአብሔር የእውነት ቃል ስትኾን: እርሷንም: በመንፈስ ቅዱስ እውቀት ያገኟት መኾኗ: የኢትዮጵያ ባዕዳንና ያገር ውስጥ ጠላቶች: ሊቋቋሟትና ሊመልሷት ባለመቻላቸው ተረጋግጧል:: ያች: የእውቀት ጸጋና የአንደበት ኃይል: ምን ዓይነት እንደነበረች፥ ተጋዳዮቹ አባትና ልጅም: አሠቃቂውን ፍርድ እንዴት አድርገው እንዳከሸፉት የሚያስረዳውን ምስክርነት: በራሱ: በልጅዬው ብዕር እንደተጻፈው: ይኸው ቀርቧል::

## የጀግናው ልጅዬው ገድል::

"Matriculation "ማትሪኩሌሽን" የሚባል: የለንደን መካነ አእምሮ (University ዩኒቨርሲቲ) መግቢያ: ከዚያ በፊት ታይቶ የማይታወቅ ፈተና ...መጣና: ተፈትነን: ፈተናውን ስላለፍኩ: ወደእንግሊዝ አገር እንድኼድ: መንግሥት ፈቀደ:: ...በዚያ ሰሞን: አራት ኪሎ: በቅድስት ሥላሴ ግቢ: ስለአማርኛ ፊደል መሻሻል: የተጧጧፈ ክርክር ሲቀጥል: ወደእንግሊዝና ወደአሜሪካ የምንላከው ልጆች: ክርክሩን እንድንሰማ: በትምህርት ምልክና (Ministere ሚኒስቴር) ተጋብዘን ነበር:: ከጉባዔው የገባነው: ከእኔ ሌላ: ምናሴ ኃይሌ፥ ኃይለ ማርያም ከበደና ሌሎችም ነበሩ:: ወደጉባዔው ስንገባ: አዳራሹ ከዳር እዳር: ጢም ብሎ ሞልቶ: መድረኩ ላይ: ኹለቱ ተከራካሪዎች: አቶ አበበ ረታ: የሕዝብ ጤና ጥበቃ ምሉክ (Ministre ሚኒስትር) እና ብላታ መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ *(የቤተ መንግሥት የታሪክና የመጻሕፍት ሹም)* ተፋጥጠዋል:: ሊቀ መንበሩ: ብላታ ዘውዴ በላይነህ የሥራ ምሉክ: እነርሱን: ግራና ቀኝ አድርገው: እመኻከል: ከፍ ባለ ቦታ: በግርማ ተቀምጠዋል:: እልፍለቃ (Colonel ኮሎኔል) ታምራት ይገዙ: የራስ እምሩን ሓሳብ ይዞ መጥቶ: ተመልካቹ ሕዝብ ከሚቀመጥበት: በግምባር-ቀደም: በመጀመሪያ ረድፍ ተቀምጧል:: አቶ ብርሃኑ ድንቄም: *(ኋላ: በአሜሪካ: የኢትዮጵያ መንግሥት እንደራሴ)*: ከእርሱ በኋላ: በ፪ኛው ነው፥ በ፬ኛው ረድፍ ተቀምጧል:: ለእኛ: ለወጣቶቹ የተያዘልን ቦታ: አዳራሹ መኻከል ላይ: በስተቀኝ ሲል ነበር::

"ገብተን፡ ቦታችንን የያዝነው፡ "በላቲኑ *ሥርዓት*+ በላቲኑ ፊደል እንጻፍ!" የሚለው፡ የብላታ መርስዔ ኀዘን ሐሳብ ወደመሸነፉ አጋድሎ+ "የእኛኑ ፊደል፡ ቅጥሉን አንድ ዓይነት አድርገን፡ አሻሽለን፡ በእርሱ እንሥራ!" የሚለው የአቶ አበበ ረታ ሐሳብ ሳያሸንፍ፡ ክርክሩን የሚያዳምጠው ሕዝብ፡ "ያቶ አበበን እንቀበለው! እንቀበለው!" ብሎ ተጨንቆ፡ በሚያመነታበት፡ ደቂቃ ላይ ነበር:: የተከራካሪዎቹ ሐሳብ፡ መቼም፡ ቀደም ብሎ፡ በአዲስ ዘመን *ጠማረ ሕዝብ* (Gazetta ጋዜጣ) ላይ ተጋግሎ ነበርና፡ እፊታችን ቁጭ ብለው ያየናቸው፡ አቶ ብርሃኑ ድንቄ፡ የጥንታዊው፡ የሀገራችን ፊደል፡ ጠበቃ ኾነው፡ "አይነካ! አይቀነስ! አይለወጥ!" ብለው፡ *በጠማረ ሕዝቡ* (በGazettaው በጋዜጣው) ላይ፡ ሽንጣቸውን ገትረው በመከራከራቸው፡ የማደንቃቸውና በሐሳብም የምደግፋቸው ነበሩ:: እኔም፡ በተማሪነት ዓቅሜ፡ "የአባታችን+ የቅድመ አያታችን+ ታሪካችንና ሃይማኖታችን የተጻፉበት ፊደል አይነካ!" የምል ስለነበርኩ፡ አቶ ብርሃኑ ድንቄን በመደገፍ፡ ለአዲስ ዘመን *ጠማረ ሕዝብ* (Gazetta ጋዜጣ) አዘጋጅ፡ ለብላታ ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ፡ በወዳጃቸው፡ በምናሴ ኃይሌ እጅ፡ ከፍ ያለ መጣጥፍ እንዲያትሙልኝ ልኬ ነበር:: እርሳቸው ግን፡ ያን ጊዜ፡ የጤና ጥበቃ *ምሉክ* የነበሩትን፡ ቀንደኛ ተከራካሪና የብርሃኑ ድንቄ ተቃዋሚ የኾኑትን፡ አቶ አበበ ረታን ፈርተው፡ የኔን ጽሑፍ ሊያትሙልኝ ካሉ በኋላ፡ ሳያትሙ፡ በምናሴ በኩል፡ መልሰውልኛል::

"በዚያን ጊዜ፡ "የአማርኛ ፊደል ይሻሻል!" የሚባልበት ዋናው ምክንያት፡ "*ዕትም መጻፍያ* (ለtypewriter ለታይፕራይተር) አያመችም!" መባሉ ነበር:: እኔ በበኩሌ፡ ለ*ዕትም መጻፍያ* አሳምሮ እንደሚመች፡ ለብላታ ወልደ ጊዮርጊስ፡ በላክሁት ጽሑፍ፡ ደህና አድርጌ አሳይቼ ነበር:: ያን ጊዜ፡ የአማርኛ *ዕትም መጻፍያ* ገና አልተሠራም ነበርና፡ ክርክሩ፡ በዚያ ላይ አተኩሮ ነበር::

"በተመልካችነት ተጋብዘን የተገኘንበት ጉባዔ ግን፡ *የመንግሥት ምሉካን* (Ministres ሚኒስትሮች) እና ታላላቅ ሰዎች የሚከራከሩበት+ ስንትና ስንት ሰው ጢቅ ብሎ የሞላበት+ የሰው ዓይን ብቻ፡ እንደኔ ያለውን፡ ዓይን አፋር ወጣት የሚገድል የሚመስል ጉባዔ ስለነበር፡ ከኔ፡ ከራሴ፡ የሃይማኖት ስብከተ ጉባዔ፡ በጣም የተለየ ኾኖ ታየኝ:: ስለዚህ፡ ምንም እንኳ፡ "ቱርክ፡ ፈረንጅ ኾናለችና፡ እኛም፡ ፈረንጅ እንኹን!" የሚለው፡ የመርስዔ ኀዘን ሐሳብ፡ መረታቱ ቢሰማኝ+ "አልሸሹም! ገለል አሉ!" የኾነው፡ የራስ እምሩ ሐሳብ፡ "ወድቆ አይቀርም!" ብዬ፡ ደስ ቢለኝም+ ከኹለቱም፡ ይብሱን፡ አደገኛ የኾነው፡ የአቶ አበበ ረቂቅ የማባበያ ሐሳብ፡ "አልወድቅም!" ብሎ፡ ሲንገዳገድ+ አንዳንዴም፡ የመርስዔ ኀዘንንም+ የራስ እምሩንም ማየቴ፡ የኔንም፡ የጥንታዊ ፊደል ጠበቃነት ወኔዬን ነሸጥ አድርጎት ነበር:: ግን፡ ማን ደፍሮ፡ በዚያ ኹሉ ሕዝብ መኻከል!? እሳቱ+ መብረቁ፡ አቶ ብርሃኑ ድንቄ እንኳን፡ ትዕግሥቱን ሰጥቷቸው፡ በተቀመጡበት መቁነጥነጥ እንጂ፡ መናገር ባልፈለጉበት ጉባዔ፡ "እኔን ምን ጥልቅ አደረገኝ?" ብዬ፡ ዐርፌ ተቀምጬ፡ የመርስዔ ኀዘንን መብገን+ የአቶ አበበ ረታን፡ በሳቸው ላይ መጀነን፡ በምፀት ዓይን እመለከታለሁ::

“እዚህ ላይ፡ ምናሴ ኃይሌና ኃይለ ማርያም ከበደ፡ ከኋላዬ ተቀምጠው ሲንሾካሾኩ ነበርና፡ ምናሴ፡ ካጠገቤ ተነሥቶ ኼደ። የጉባዔውን አስተናባሪ፡ ያን ጊዜ፡ የትምህርት ምልክና ዋና ጸሓፊ የነበሩትን፡ አቶ መኰንን ዘውዴን፡ ደፍሮ፡ በጆሮአቸው፡ ምናምን ሲነግራቸውና እርሳቸውም፡ 'እሺ! በጄ!' እንደማለት፡ ራሳቸውን፡ ላይ ታች ሲወዘውዙ አየሁ። ግን፡ 'የግል ጉዳይ ይኖረዋል' ብዬ፡ ነገሩን ከምንም አልጣፍኩትም። ወዲያው፡ ድንክዬው ሊቀ መንበር፡ 'ሌላ ተከራካሪ፥ ሌላ ተናጋሪ ያለ አይመስልምና፡ እንግዴህ፡ ሓሳቡ፡ የኹሉም ተሰምቷል፤' አሉ።

“'የለም፥ ጌታዬ ክቡር ሊቀ መንበር! ተናጋሪ አላለቀም፤ ገና አንድ አለ። የ፪ኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ጨርሰው፡ መንግሥት፡ ወደውጭ አገር የሚልካቸው ወጣቶች፡ ክርክሩን እንዲያዳምጡ፡ በትምህርት ምልክና ተጋብዘው፡ እዚህ፡ እመኻላችን ይገኛሉ። እነርሱ የሚሉት፡ በዚህ ታላቅ ጉባዔ ላይ፡ ከኛም ወገን የምናቀርበው ሓሳብ ስላለን፥ ሓሳባችንን፡ ከኛው መኻከል የሚያቀርብልን ሰው ስለመረጥንና እሱም፡ እዚሁ፡ እመኻከላችን ስላለ፡ እንዲናገር፡ ጉባዔው ይፍቀድልን!፡ ነው የሚሉት፤' አሉ አስተናባሪው። ይህ ሲሰማ፡ ሕዝቡ በሹክሹክታ ሲንቻቻ፡ ቤት *(ቀፎውን)* እንደሚለውጥ የንብ ሠራዊት፡ ያስገመግም ጀመር።

“'ይህ፡ አዲስ ነገር ነው፤ የሚፈቀድ አይመስለኝም። የጉባዔውን ሥነ ሥርዓት ያፈርሳል። የሚናገር ሰው እንዳለ፡ ስሙን አስቀድሞ እንዲያስመዘግብ ጠይቀን፡ የተመዘገቡት፡ ተናግረዋል። አሁን፡ አዲስ ተናጋሪ መቀበል አንችልም።' አሉ ሊቀ መንበሩ።

“'ወጣቶቹ የመጡት፡ ከኮተቤ ድረስ ነው። በመኪና መታጣት ምክንያት ነው የዘገዩት!' አሉ አስተናባሪው።

“ሊቀ መንበሩ፡ ወጣቶቹን 'እምቢ!' ብለው፡ ወጣቶቹ እንዲጠሏቸው አልፈለጉም። ስለዚህ፡ በግራና በቀኛቸው ያሉትን ኹለቱን ተከራካሪዎች ጠየቋቸው።”

እነርሱም፡ ተስማሙ። በዚህ ጊዜ፡ “እነምናሴና ኃይለ ማርያም፡ በድንገት ጭብጨባቸውን ለቀቁት። ሕዝቡም፡ የእነርሱን አርአያ ተከትሎ፡ አጨበጨበ። ጭብጨባው ሲበርድ፡ ሊቀ መንበሩ፡ 'የወጣቶቹ ተናጋሪ፡ ታዲያ የታል? ማነው? ይጠራ! ይቅረብ! አለ? የለም? አቶ መኰንን! ስሙን ይዘኸዋል?' አሉ።

“አስተናባሪው፡ 'ስሙ፡ እዚህ አለ!' አሉና፡ የያዙትን የስም ዝርዝር፡ አየት ካደረጉ በኋላ፡ የአዲሱን ትውልድ ተወካይ ወጣት ተናጋሪ ስም፡ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ጠሩ። አንባቢ ሆይ! ይህ፡ ተናጋሪነቱን እስከዚያች ደቂቃ፥ እስከዚያች ሴኮንድ (second= ካልዕት) ድረስ ያላወቀው፡ የአዲሱ ትውልድ ተወካይ፡ ማ ይመስልሃል?

“'መንግሥቱ ለማ! :መንግሥቱ ለማ፡ የሚባል ተማሪ ይውጣና ይናገር!' አሉ አስተናባሪው።

“በድንጋጤ፡ የምይዘውን አጣሁት፤ በግራና ቀኝ፥ ከፊትም፥ ከኋላም የተቀመጡት፡ የዘመኑ ወጣት ተማሪ ጓደኞቼ ኹሉ፡ ነገሩ፡ በጣም አስቋቸው፡ 'ተነሥ! ተነሥ! ተነሥ!' እያሉ፡ ይጐተጕቱኝ ጀመር።

“'''መንግሥቱ ለማ፡ የሚባለው ተማሪ የታል?' አሉ አስተናባሪው። 'ይጠበቃል እኮ! ጊዜ የለንም!' ...እኔ ግን፡ አስተናባሪው እንዳያዩኝ፡ ከወንበር ወርጄ፡ እመሬት ተደብቄአለሁ። 'የታል? የለም እንዴ!' አሉ አስተናግሪው መልሰው።

"እኔ፡ በዚያች ደቂቃ፡ ያለሁበት የመንፈስ ኹኔታ፡ በድንጋጤው ላይ፡ የዓይን አፋርነት ጭንቀትን፥ በዚያ ላይ ደግሞ፡ ንዴትን ያደባለቀ ነበር። ንዴቱና ቁጣው፡ በምናሴ ኃይሌና በኃይለ ማርያም ከበደ፡ በኒያ በኹለቱ ተንኰለኞችና ቀልደኞች ነበር። ቢኾንም፡ ምናሴ ተነሥቶ፡ ለአስተናባሪው መለሰላቸው፡ 'መንግሥቱ ለማ፡ አለ፤ ይኸው እዚህ ነው!' አለና፡ ከኃይለ ማርያምና ከሌሎቹ ባለጡንቻዎች ጋር ተጋግዘው፡ ከተወሸቅሁበት ጎትተው አወጡኝ። የግድ በጕልበታቸው፡ በዚያ በጉባዔ መኻከል አቆሙኝ።

"...ከዚያ፡ ሌሎቹ ተማሪዎች፡ ተቀባበሉኝና ከእነርሱ መኻከል አስወጥተው፡ በጉባዔው ሕዝብ መኻከል፡ ብቻዬን አቆሙኝ። የተሰበሰበው ሕዝብ፡ በእውነት ተማሪ መኾኔን፡ ከአለባበሴ አይቶ፡ በጭብጨባ አበረታታኝ። እኔም፡ ከዓይናፋርነት የተነሣ፡ ሳልገለማመጥ፡ መሬት መሬቱን ብቻ እያየሁ፡ መተላለፊያውን ተጕዤ፡ የመድረኩን ደረጃ፡ ራሴን ደፍቼ ወጣሁ።

"በፊደል መሻሻል ጉባዔ ላይ፡ ከዚያ ኹሉ ሰው ፊት ቆሞ፥ የመንግሥት ምሉካን እና ታላላቅ ባለሥልጣኖች መኻከል ቆሞ መናገር፡ ልክ፡ በልጅነት፡ ያበሻ ኮሶ እንደመጠጣት ኾኖ ታየኝ። ጭብጨባው፡ እንደእናቴ ሙገሳ ነበር፤ ኮሰው ደግሞ፡ የአደባባይ ንግግር (discourse፡ ዲስኩር) ማድረጉ ነበር፤ ኹኔታው፡ ሞት ነበር የመሰለኝ፤ ሲያስፈራ! አለመናገሩ ግን፥ 'እምቢ!' ብሎ፡ ይቅርታ መጠየቁ ግን፡ በተማሪ ቤታችንና በጓደኞቼ ዓይን፡ የሞት ሞት ስለኾነ፡ በነፍሴ ቆርጬ፡ ልናገር ተሰናዳሁ። 'ቆራጥና ጪስ፡ መውጫ አያጣም!' የሚለው ያባቶቻችን ምሳሌ፡ ድንገት ሳላስበው፡ ከሕሊናዬ ድቅን አለ።

""'መንግሥቱ ለማ" የተባለው ወጣት፡ ይኸ ነው?' አሉና፡ ሊቀ መንበሩ፡ የሥራ ምሉኩ፡ ከእግር እስከራሴ የዝቅዝቅ ተመለከቱኝ።

"...ይህ፡ እልክ አስገባኝ፤ ...ዓይናፋርነቱም፡ በአንዴ ተገፈፈልኝ። ድምፄን ከፍ አድርጌ፡ ንግግሬን ጀመርኩት። በተማሪ ቤታችን፡ እሑድ፡ እሑድ ማታ፡ ከኹለት ዓመት በላይ፡ ሃይማኖት መስበኬ፡ ለካ ሳላውቀው፡ የአደባባይ ንግግር መናገር አስተምሮኝ ኖርዋል! ንግግሩን ገና ስጀምር፡ በእኔ አስተያየት፡ የቆየው ታሪካችን፡ ከትውልድ ወደትውልድ፡ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው፡ ከአራት ጀምሮ፡ ወንጌልን ይዞ፡ የቀሩት መጻሕፍት ቅዱሳት የተጻፉበት ያገራችን ፊደል፡ ከፈረንጅ ፊደል፡ ምንም የሚያንስበትና የሚበዛበት ስለሌለ፡ "ይለወጥ! ወይም ይሻሻል!" የሚለውን ሐሳብ፡ በፍጹም የምቃወም መኾኔን ስገልጥ፡ ጭብጨባው፡ ከዳር እስከዳር አስተጋባ። አቶ ብርሃኑ ድንቄ፡ በተለይ ከሩቅ ሳያቸው፡ ፈንጥዘውም አላባሩ! ...እኔ ያን ጊዜ እንደገመትኩት፡ ሕዝቡ፡ ገና ከመጀመሪያው፡ ቀጥዬ፡ ምን እንደምል ሳያውቅ፡ ለእኔ፡ እንዲያ አድርጎ ያጨበጨበው፡ የልቡን ስለነገርኩት ነበር። ከተሰበሰበው፡ ከመቶ፡ ዘጠና አምስቱ እጅ፡ በፊደላችን የሚኮራ፥ ፊደላችን እንዳይነካ የሚመኝ፥ ለፊደሉ፡ 'ሙት!' ቢሉት፡ የሚሞት ነበር።

'የላቲን ፊደል እንቀበል!' የሚለውን ሐሳብማ፡ 'ጣልያን፡ ተመልሶ ይግዛን!' እንደማለት ነበር የቆጠረው። ግን፡ ከሕዝቡ ውስጥ፡ ይህን ሐሳቡን ደፍሮ፡ በጉባዔው ላይ የሚናገር፡ አንድ እንኳ አልነበረም።

ባለሥልጣኖቹን ይፈራል፤ ምን ይደረግ? አበበ ረታ፥ ዘውዴ በላይነህ፡ የመንግሥት ምሉካን ናቸው፤ መርስዔ ኀዘንም፡ ወደዚያው ናቸው፤ አስተናባሪው፡ አቶ መኰንን እንኳ፡ የትምህርት ምልክና ዋና ጸሐፊ ናቸው፤ እልፋለቃ ታምራትም፡ የደጃች ይገዙ ልጅ፡ ታላቅ መኳንንት ናቸው።

"የባሰ ይባስ፡ ታምራት ይገዙ፡ ይዘው የቀረቡት፡ የራስ እምሩን፡ 'ፊደላችን ይለወጥና፡ በፈረንጅ መንገድ ይሥራ!' የሚለውን ሐሳብ ነው። ራስ እምሩ፡ የደጃች ኃይለ ሥላሴ ልጅ ናቸው፤ ደጃች ኃይለ ሥላሴ ዓባይነህ ደግሞ፡ ከራሳቸው መኳንንትነት ሌላ፡ የንጉሠ ነገሥቱን አክስት አግብተው፡ እምሩን የወለዱ ናቸው። ስለዚህ፡ በሕዝቡ አይፈረድም። እርግጥ፡ በሕዝቡ መኻከል፡ የፊደላችን ጠበቃና አርበኛ፡ አቶ ብርሃኑ ድንቄ ተገኝተዋል። እርሳቸውም ቢኾኑ፡ በዝምታ፡ ኹኔታውን፡ አንጀታቸው እያረረ ይመለከቱ ነበር እንጂ፡ ለመናገር አልፈለጉም። በጠማሪ ሕዝብ ላይ፡ አቶ አበበ ረታን ተሚግተዋል፤ በክርክሩ ስላልተቻሉ፡ የባለሥልጣን ተፅዕኖ ወድቀባቸው፡ የእርሳቸው፡ የክርክር ጽሑፍ፡ በጠማሪ ሕዝብ እንዳይታተም፡ ታግዶባቸዋል። እርሳቸውንም ኾነ፡ ሌላውን ሕዝብ፡ ከልብ ያስፈነደቀው፡ ከዘመኑ፡ የተማሩ ወጣቶች አንዱ፡ ያውም፡ ወደውጭ አገር እንዲኼድ የታጨና የአዲሱ ትውልድ አባል የኾነ፡ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ፩ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪ፡ 'ፊደላችን፡ ከማንም ፊደል አያንስምና፡ አይለወጥም!' ማለቱ ነበር። ተከራካሪዎቹን፡ ኹለት ባለሥልጣኖች፥ ሊቀ መንበር የኾኑትን ምሉክ እና እልፋለቃ ታምራትን ጭምር፡ ይህ፡ ያልታሰበ፡ አዲስ ኹኔታ፡ በመጀመሪያ፡ አስገርሟቸዋል፤ ቀጥሎ፡ አስደስቷቸዋል፤ ደግሞም፡ አስቆጥቷቸዋል። ግን፡ ኹሉንም፡ እኩል አልነበረም፡ ነካ ያደረጋቸው።

"'ፊደላችን አይለወጥ! ከብዙው ይሻላል፤ ከማንም አያንስም!' የሚለው ሐሳብ፡ ከተማሪው፥ ከአዲሱ ትውልድ፡ አንዱ ከኾንኩት፡ ከእኔ አፍ መውጣቱ ያስገረማቸው፡ ኹሉንም ነው። ውስጥ ውስጡን ያስደሰታቸው፡ የለውጥ ሐሳባቸው ውድቅ በመኾኑ፡ መሸነፍ የተሰማቸውን፡ መርስዔ ኀዘንንና ታምራትን ነው። ያስቆጣቸው ደግሞ፡ ሐሳባቸው፡ ሊረታና ሊያሸንፍ፡ አፋፍ ላይ ከደረሰ በኋላ፡ በእኔ ምክንያት፡ ሊጨናገፍባቸው የኾነውን፡ አበበ ረታን ነበር። ስለዚህ፡ ዋናው ተከራካሪ፡ አቶ አበበ ረታ ኾኑና፡ ሌሎቹ፡ በመንፈስ፡ የእኔ ደጋፊ ኾኑ! ድጋፍ የሰጡኝ፡ እኔን ወይም ሐሳቤን ወደው ሳይኾን፡ የእነርሱ ወድቀ፡ ያቶ አበበ ከሚያሸንፍ፡ 'የሦስቱም፡ አንድነት፡ ውድቅ ቢኾን ይሻላል!' በሚል፡ በ'እኔ ከሞትኩ፡ ሠርዶ አይብቀል!' ስሜት መኾኑ፡ ቀስ በቀስ፡ በሙግቱ ላይ ተገለጸልኝ።

"በበኩሌ፡ 'ፊደላችን አይለወጥም!' ብዬ ስከራከር፡ መርስዔ ኀዘን፡ 'ቱርክ፡ የጥንት ፊደሎቿን ትታ፡ ለዘመኑ ሥልጣኔ አሠራር የሚያመቻትን፡ የላቲንን ፊደል ተቀብላለች' ብለው ላቀረቡት ክርክር፡ 'ቱርክ፡ ታዲያ፡ የራሷን ፊደል ጥላ፡ በሥልጣኔ እርምጃ የት ደረሰች? ከዚያው፡ ዱሮ ከነበረችበት፡ ጥቂት እንኳ ፈቀቅ አላለችም። ጃፓን ግን፡ ከእኛ ፊደል፡ መቶ ጊዜ፥ ሺ ጊዜ የሚያስቸግረውን፡ የራሷን ፊደል ይዛ፡ በሥልጣኔ እርምጃዋ፡ ያለመጠን፡ በአጥፍ ድርብ በማደጓና በመመንደጓ፡ በጦርነት እንኳ፡ ድሮ፡ መስኮብን፥ ቀጥሎም፡ ፹፻፼ (ስማንያ ሺ እልፍ) ወይም ፰፻ (ስምንት መቶ) አእላፍ (800,000,000 = eight hundred million) ሕዝብ ያለውን ቻይናን አሸንፋለች።

በአቶሚክ ብትሸነፍም: ወደፊት ባጭር ጊዜ ውስጥ: ያቶሚክ ፈንጂ (bomb ቦምብ) ትሠራለች:: ይህ የሚያሳየው: ያንድን አገር: የሥልጣኔ እርምጃ: ወደኋላ የሚያስቀረው: ሌላ ሌላ ነገር ነው እንጂ: ፊደሉ አለመኾኑን ነው::' ይህንን ስል: አንጀቱ የራሰው÷ የጉባዔውን አዳራሽ: ጢም ብሎ: ከአፍ እስከገደፉ የሞላው ሕዝብ አጨበጨበ::

"ቀጥዬ: አቶ አበበ ረታ: 'ፊደላችን: ለእጅ መኪና ጽሕፈት አይመችም!' ላሉት ስመልስ: 'የፈረንጁ የፊደል ገበታ: ሃያ ስድስት ፊደላት ብቻ ነው ያሉት ቢባልም: በፈረንጁ ዕትም መጻፍያ መኪና ላይ የሠፈረው: ኹለት የተለያየ: የፊደል ገበታ: ትልቅና ትንሽ - Small & Capital letters መኾኑን÷ ስለዚህ: የፈረንጁ ፊደል: ጠቅላላው ቁጥር: ሃያ ስድስት ሳይኾን: ሃምሳ ኹለት መኾኑን÷ የእኛም: ቅጥሎቹን: ከፊደላቱ ለይተን: በመኪናው ላይ ብናሠፍራቸው: ቅጥላቸው ተለይቶ ለብቻው ቢሠፍር÷ የማይቻሉትን ፊደላት: እንዳለ ብናስቀምጣቸው÷ እንዲሁም: እነ ቾ÷ ጇ÷ ዠ÷ ጸ÷ቷ÷ ኋ... ወዘተን: በዋና ፊደላቸው ብቻ ብንተካቸውና ተጨማሪውን ምልክት ለብቻው ብናሠፍረው: ለጽሕፈት መኪና የማያስቸግሩ መኾናቸውን: በጥቁር ሰሌዳ (በblackboard በብላክቦርድ) ላይ: በጠመኔ እየጻፍኩ አሳየሁኝ::

"...የእኔ ንግግር: በዚያ ማብቃቱን: ለሊቀ መንበሩ አስታውቄ: ከመድረኩ ወርጄ: ወደቀድሞው መቀመጫዬ ሳመራ: የሕዝቡ ጭብጨባ ቀለጠ:: ወዲያው ትርምስ ኾነ! ...እኔም: ሹልክ ብዬ ወደ(ወላጆቼ) ቤት አመራሁ:: ስኼድ: በመንገድ ላይ: ለሀገራችን ጥንታዊ ፊደል: ሽንጤን ገትሬ ተከራክሬ: ለዘለቄታው እንኳ ባይኾን: ለጊዜው ጠላቶቼን: አፋቸውን በማስያዜ: በልቤ ሳልደሰትና በዚያ ኹሉ ሕዝብ መኻከል: ዓይናፋርነቴን ገፍፎ: አንደበቴን የፈታልኝን አምላክ: 'ተመስገን!' ሳልል አልቀረሁም::

## የጀግና አባትዬው ገድል::

"በበነጋው: ምሳ ተበልቶ: አባቴ: በዚያ በጎሽ ዋንጫቸው: ጠላ ሲጎነጩ: ለእኔም: የምበላው እንዲቀርብልኝ አዝዘው: ምሳዬን በልቼ: ከጨረስኩ በኋላ: ዋንጫቸውን አንሥተው: 'ና! እንካ!' አሉኝ:: እጅ ነሥቼ ተቀበልኩና: እቦታዬ ተመልሼ ተቀመጥኩ:: ዋንጫቸውን አጋምሰው: አባቴ: ለሰው ሲሰጡ: መቼም ምልክት ነው፤ ያ ሰው: "አንድ: እሳቸውን ደስ የሚያሰኝ ሥራ ሠርቷል!" ማለት ነው:: እኔም: 'ምን አድርጌ ይኾን: ይህ ክብር የደረሰኝ?' እያልኩ ባሰላስልም: ለጊዜው: ምክንያት አልታየኝም ነበር:: 'ምን አድርጌ ነው?' ብሎ መጠየቅ: ድፍረት ይኾናል፤ ስለዚህ: እርሳቸው እስኪያመጡት: ዝም ብዬ: ከዋንጫው ፉት! ፉት! እያልኩ ጠበቅሁ::

"'ሰማሁ! ተባረክ! ይባርክህ! እንዲህ ነው: "የለማ ልጅ" ማለት! እንዲህ ነው! ለምሳ: ከመንፈሳዊ ጉባዔ ስመጣ: አንድ: የማላውቀው ሰው: እመንገድ ላይ አቁሞ: 'ጎበዝ ልጅ ወልደዋል! ዛሬ የሠራው ሥራ: እንዲህ አይምሰልዎ!' አለኝ:: 'ምንድነው የሠራው?' ብለው: 'ያባቶቻችንን: የኢትዮጵያ ፊደል: "በፈረንጅ ይለወጥ!" የሚሉትን ተኩላዎች: በክርክር ደህና አድርጎ ደብድቧቸዋል፤ ረቷቸዋል:: እኛን: ደስ እንዳለን: እርስዎንም: ደስ እንዲልዎ ይገባል!' ብሎኝ: ትከሻና ትከሻዬን ስሞኝ: መንገዱን ቀጠለ::

"'እርግጥ: ይህን አድርገሃል?' አሉ::

"'ሳልወድ: በግድ: እነምናሴ ኃይሌ: እጄን ጎትተው: አውጥተው ነው: እክርክር ውስጥ ያስገቡኝ!' አልኳቸው::

"'እንዲያ ነው! ኾኖም: ለማ ቀድሞሃል!' አሉ::

"'በምኑ?' አልኳቸው::

"'በዚሁ: በፊደሉ ክርክር ነዋ! በዚያ ሰሞን: ይኸው ነገር: ለመንፈሳዊ ጉባዔ: "ሊቃውንቱ ይነጋገሩበት!" ተብሎ: መርስዔ ኀዘን: ራሱ አልመጣም፤ እዚያው: እኛው መኻከል ያሉ: የእርሱ ብጤዎች ናቸው: ነገሩን የቀሰቀሱት፤ አንዱ: "ይለወጥ!" ሲል: አሥሩ: "አይለወጥም!" ሲሉ÷ አንዱ: "ምን አለበት ቢለወጥ! ይጠቅማል እንጂ: አይጎዳ!" ሲል: አሥራ አምስቱ: "እንዴት ተብሎ! እንዴት ታስቦ!" ሲሉ: ድብልቅልቃቸው ወጥቶ: ቀኑን ሙሉ ዋሉበት:: ለማ አልተናገረም፤ ዝም ብሎ: እጃቸውን ያያል:: ጠና ጠና ያልነው: አልተናገርንም:: ሊቀ ሊቃውንት ቀጸላ: "ስምንተኛው ሺ ሲደርስ እንዴት ነው?" አሉኝ:: ታዲያ: ምናለ! ክርክሩ ቀጠለ:: መጯጯህ ኾነ! "አንተ: እንዲህ ነህ! አንተ: እንዲህ፤ አንተ: እንዲህ ነህ!" መባባል መጣ:: በኋላ: ሊቀ ሥልጣናቱ: ተከራካሪዎቹን አስታግሠው: "ከዚህ በፊት ያልተናገሩ: ከሽማግሌዎቹ ይናገሩ! እነርሱም ይሰሙ!" አሉ::

"'ለማ ተነሣ:: "እንግዴህ: ይህ ታሪካችን÷ መጻሕፍት ቅዱሳታችን÷ የጻድቃን÷ የሰማዕታት ገድል የተጻፈበት: ያባቶቻችን ፊደል: 'አሮጌ ነው፤ ጊዜው አልፏል፤ አይረባንም፤ እሱን አንፈልገውም!' አይደለም? 'እሱ በቃን! ሰለቸን!' አይደለም? 'ይለወጥልን፤ በሱ ቦታ: ሌላ ፊደል ይተካልን!' ካላችሁ: ለማ: የሚጣላችሁ አይደለም፤ እኔ ለማ: ከክርክራችሁ አልገባም:: እንዲያውም: 'በርቱ! ይቅናችሁ!' ነው የምል:: ይመስገነውና ፈጣሪዬ: ጤናውን ሰጥቶ: ከዚህ አድርሶኛል፤ ሸምግያለሁ:: ያቅሜን ተምሬአለሁ፤ ከዚህ በኋላ: 'ፊደል ልቁጠር! ንባብና ጥፈት ልማር!' አልልም፤ ጊዜው አልፏል:: ይመስገነው÷ ከጣልያን ዘረፋ የተረፉት: በጥንቱ በአባቶቻችን ፊደል: በብራና የተጻፉት መጣፎች: ከቤቴ አሉ፤ እስከዕድሜዬ መጨረሻ: እነሱን እነባለሁ፤ በዚህ እናንተን አላስቸግርም፤ ራሴን ችያለሁ፤ ለእኔ አታስቡ!

"'"ብቻ÷ ለእናንተስ አታስቡም ወይ? ለሕዝቡስ? እንደሚባለው: የኢትዮጵያ ሕዝብ ተቆጥሮ: ከክርስቲያኑ: እስላሙ: በቁጥር ይበልጣል÷ ይበዛል ይባላል:: እስላም ደግሞ: ለቁርዓኑ: ሙት ነው፤ ቁርዓኑ ለተጻፈበት: ለዓረቡ ቋንቋ÷ ለዓረቡ ፊደል: ቀናዒ ነው፤ ቋንቋውም÷ ፊደሉም: ነፍሱ ነው፤ ይወደዋል ሲበዛ:: ዛዲያ: የኢትዮጵያ ሕዝብ: እስላሙም÷ ክርስቲያኑም: ካልለመደው: ባይኾን: ገሚሱ የወደደው አይሻልም? ኹለቱም ቢያዝኑ: ምን ይረባል? ባይኾን: አንዳቸው ይደሰቱ! ፊደላችን: ዓረብኛ ይኹን!" ብዬ ተቀመጥኩ::

"'ጉባዔው: ብጥብጥ ብሎ ተበጠበጠ:: "አለቃ ለማ: 'የእስላም ፊደል ይኹን!' አሉ! አሉ? አሉ!" ኾነ! "የእስላም ፊደል? አዎ! የዓረቡ የእስላም ፊደል!" መባባል ኾነ! ጉባዔው: የጨረባ ተዝካር ኾነና: በዚያው ተበታተነ!' አሉ::

"አባቴ፡ የቀድሞው የግብፃዊው ሊቀ ጳጳሳችን፡ የአቡነ ቄርሎስ ወዳጅ መኾናቸውንና በኋላ፡ በእርሳቸው ቦታ፡ የእኛው አበሻ፡ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት መተካቱን፡ በጥብቅ የተቃወሙ መኾናቸውን ሲናገሩ ሰምቻቸዋለሁ:: "'ፈደላችን፡ ዓረቡ ይኹን!' ያሉት፡ በዚህ ሳቢያ ይኾን?" ብዬ፡ ምክንያቱን ጠየቅኋቸው::

"'ሞኙ! "ለማ፡ ከግእዙ ፈደላችን፡ ዓረቢውን ይመርጣል!" ብለህ ነው? የለም! ለማ፡ ለብልሃቱ ነው፡ "ዓረቡ ይኹን!" ያለ:: ለማሸበሪያ! ጉባዔውን ለማፍረስ ነው:: እውነትም፡ እንደተመኘሁት፥ እንዳሰብኩት ኾነልኝ! ቀናኝ:: 'የእስላም ፊደል! የስላም ፊደል? የስላም ፊደል? ...' እያለ፡ ያ ባለቀብ፥ ባለካባና ባለጥምጥም ኹሉ፡ ተደናግጦ ተበታተነ:: ከዚያ ቀን ወዲያ፡ በመንፈሳዊ ጉባዔ፡ የፊደል መለወጥ ነገር አልተነሣም:: ያ መርስዔ ኀዘንም፡ ዝር አላለ:: ዛሬስ፡ በጉባዔው ነበር?' አሉ::

"'ነበሩ! ተናገሩ! ግን፡ ሕዝቡ፡ ሐሳባቸውን አልተቀበላቸውም:: ከእርሳቸው በቀር፡ የራስ እምሩንም፥ ያበበ ረታንም፡ ሕዝቡ አልተቀበለውም:: ለእኔ ነው፡ ያጨበጨበው!' አልኳቸውና፡ እንደቀልድ አድርጌ፡ የኾነውን ኹሉ፡ በዝርዝር አወጋኋቸው::

"'ተመስገን ፈጣሪዬ! ተመስገን! ቸርነትህ፡ ማለቂያ የለው!' አሉ ለመደምደሚያ:: 'ፊደላችን፡ ሊተርፍልን ነው መሰል!'" [፲፱]

ለእኒህ፡ ኹለት፡ ታማኞች፥ ተጋዳዮችና ጀግኖች ኢትዮጵያውያን፡ አባትና ልጅ፡ ለሊቀ ምሁራን አለቃ ለማ ኃይሉና ለተወዳጁ ልጃቸው፡ የቅኔው ደራሲ መንግሥቱ ለማ፡ ከቅዱሱ ኪዳን፡ የኢትዮጵያ ቤተ ሕዝብ፡ ተገቢው ሕያው ሙገሳ ሊቀርብላቸው፥ መዘከርም ሊደረግላቸው ይገባል::

## ኢትዮጵያ፡
## ስለሆህያቷ ሥርዓት፡ ትውልዱን ስትፋረድ!

በጥንታዊውና በባለቤቱ፡ የአገሪቱ ቋንቋና ፊደል ቦታ የላቲኑን የመተካቱን ነገር፥ እንዲሁም፡ "ምንጊዜም ቢኾን፡ 'ይጨመሩ!' ይባላል እንጂ፡ እንዴት 'ይቀነሱ!' ይባላል?" የሚለውን ትችት፡ እዚህ ላይ እናቁምና፡ እስቲ "የግእዝ ሆህያት ይቀነሱ! አኀዛቱም ይሠረዙ!" ወደሚለው ዘዬ እንመለስ!

## "ሆህያት ይቀነሱ!" የሚያሰኙ፡
## በቂ ምክንያቶች አሉ ወይ?

አንድ ቋንቋ፡ በዘመኑ የሥልጣኔ ዕድገት መጠን፡ ልዩ ልዩ ድምፅ የሚያስፈልጉትን ሆህያት እየፈጠረ እንዲኼድ ይገደዳል እንጂ፡ ሊቀንስ አይችልም:: ለምሳሌ፡ እንግሊዝኛ የሚናገሩ ሕዝቦች፡ የኢትዮጵያኛው፡ "ጠ"፥ "ጸ"፥"ፀ"፥ "ጰ"፥ "ጨ"፥ "ሸ"፥ "ቸ"፥ "ኸ"፥ "ዠ"፥ "ኘ" ስለሌላቸው፡ ወይ አዲስ ቃል በመፍጠር፡ አለዚያ፡ ያሏቸውን ፊደላት በማቀናጀት፡ የሚፈለገውን ድምፅ እንዲሰጡ ያደርጋሉ! ለምሳሌ፡ የ"ሸ"ን ድምፅ ለማግኘት፡ "sh"፥ የ"ቸ"ን ድምፅ ለማግኘት፡ "ch"፥ የ"ኘ"ን ድምፅ ለማግኘት፡ "gn" ብለው እንደሚጽፉት ማለት ነው::

ይኹን እንጂ: የ"ጠ"ን፥ የ"ጸ"ን፥ የ"ፀ"ን፥ የ"ጰ"ን፥ የ"ጨ"ን፥ የ"ኸ"ንና የ"ዠ"ን ድምፅ ለማግኘት: ነጥብ እና/ወይም ሠረዝ የታከለባቸው: የሆህያት ቅንጅትን ቢፈጥሩም: ከአንደበታቸው አለመገራት የተነሣ: ትክክለኛ ድምፃቸውን ማስገኘት አልቻሉም። ለምሳሌ: "ጸ" ለማለት የፈጠሩት ቅንጅት: "ts": ምላሳቸውን: የቱንም ያህል ከጥርሳቸው ጋር አጣግተው: እስትንፋሳቸውን በኃይል ቢገፉትም: እውነተኛውን ድምፅ ሊያሰማ እንዳዳገታቸው ይታወቃል።

እንግዴህ እነርሱ: እንዲህ በመሰለ ማጥ ውስጥ ተዘፍቀው: መፍትሔ በመፈለግ: የሚዳክሩበትን ችግር: እኛ አስቀድመን አስወግደነዋል ማለት ነው። ጥንቱኑም ችግሩ የለብንም። ታዲያ: እነርሱ: በእነርሱ ዘንድ: እንደአዲስ ፈጥረው: ሕያዋን ሊያደርጓቸው የሚፈልጓቸውን: እነዚህን የፊደላችንን: ሕያዋን ሆህያት: እኛ ደግሞ: እንዴት ከሕያውነት አውጥተን: ወደመቃብር ለማውረድ: የሞት ፍርድ ልንወስንባቸው እንጥራለን? ይህም ማለት: የሌለብንን ችግር ለመፍጠር: ለምን እንሞክራለን?

እንኳንስ: አሁን ያሉትን ሆህያት ልንቀንስ ይቅርና: ወደፊት: እንዲያውም መጨመር እንደሚያስፈልገን ግልጽ ነው። ይህም ይታወቅ ዘንድ: በሌሎቹ ቋንቋዎች ዘንድ ያሉትን ድምፆች: የእኛ ሆህያት ገና አካትተው ያልጨረሱ በመኾናቸው: አዳዲስ ሆህያትን መቅረጽ የሚያሻን የመኾኑ ነገር እየጐላ ኼዷል። ለዚህም: በርካታ ምሳሌን ማቅረብ ይቻላል። በቅርብ ካሉት መካከል: ጥቂቶችን ለመጥቀስ ያህል: ለምሳሌ: በፈረንሳይኛ: "r"፥ ወይም በእብራይስጥና በዓረብኛ: በ"ገ" ድምፅ ላይ የተመሠረተ ኾኖ: በትናጋ የሚነገር፥ ደግሞም: እንግሊዝኛ ተናጋሪዎች: "the"፥ ወይም በዓረብኛ: "ዟ" የሚሉትን: ምላስ: በላይና በታች የፊት ጥርስ መካከል ኾኖ: በእኛ: በ"ዘ" ድምፅ ላይ የተመሠረተ፥ እንዲሁም: እንግሊዝኛ ተናጋሪዎች: "birth"፥ ወይም በዓረብኛ: "ሷ" የሚሉትን: ምላስ: በላይና በታች የፊት ጥርስ መካከል ኾኖ: በእኛ: በ"ሰ" ድምፅ ላይ የተመሠረተ ድምፅን: በትክክል የሚያሰማ ሆሄ የለንም፤ ስለዚህ: ይህን የመሰለውን እጦት ለማሟላት: አዲስ ሆሄ መቅረጽ: ወይም ካሉት ሆህያት መካከል ተቀራራቢውን በመምረጥ: በዚያ ላይ ልዩ ምልክት አክለን ማቅረብ አለብን ማለት ነው።

ይህም: በእኛ ዘንድ እንግዳ ድርጊት አይደለም፤ የሩቁን ድርጊታችንን ለማዘከር: "ጰ"፥ "ፐ"፥ "ጨ"፥ "ሸ"፥ "ቸ"፥ "ኸ"፥ "ጀ"፥ "ዠ"፥ "ኘ": ፳፬ቱን መሠረታውያን ሆህያት በያዘው ፊደላችን ላይ: ኋላ የተጨመሩ ሲኾኑ: የቅርቡን ድርጊታችንን ለማውሳት ደግሞ: ለኦሮምኛ ቋንቋ አስፈላጊ ኾኖ በመገኘቱ: ወደኋላ ቀደም ብሎ: ይህን ዓይነት አጭር የቁመት ሠረዝን " ' " በ"ጸ" አናት ላይ በማሥፈር: "ጰ"ን ለማስገኘት: እንደተቻለ ኹሉ: አሁን ደግሞ: ይህንኑ ዓይነት ሠረዝ " ' " በ"ደ" አናት ላይ በማሥፈር: "ዸ" የሚለውን: ምላስን በትናጋ ላይ አኑሮ: እንደ"ደ" እስትንፋስን ወደውጭ በኃይል በመግፋት ፋንታ: እስትንፋስን ወደውስጥ በመሳብ የሚገኘውን ድምፅ የሚያሰማ ሆሄ ለመቅረጽ ተችሏል። "V" ለሚለውም: ለፈረንጆቹ ሆሄ: እንዲሁ: በ"በ" አናት ላይ: ከሆሄው ጋር ያልተገናኘ: ክፍት የአግድም መስመር በማድረግ: ይህንኑ ድምፅ በትክክል የሚያሰማ: "ቨ" የተባለውን ሆሄ ለማስገኘት ተችሏል።

## የግእዝ ማንነትና ምንነት።

ኢትዮጵያዊው ፊደል፡ "ግእዝ" በሚል ስሙ፡ የመጀመሪያው የሰው ዘር የቋንቋ መገለጫ ነው። የዚህ እውነታ፡ ማረጋገጫው፦

፩ኛ፦ የራሱ የ"ግእዙ" ትርጓሜ የሆነው፥ "መጀመሪያ" እና "ነፃ" የሚለው የጥሬ ዘሩ ቃል፥

፪ኛ፦ በሰባት ብዛት የሚወሰን ቁጥር፡ መለኮታዊ ምሥጢር እንዳለበት ስለሚታመን፡ እያንዳንዱ ፊደል፡ በሰባት ስሞች፥ ድምፆችና መልኮች ተለይቶ መታወቁ፥

፫ኛ፦ የእያንዳንዱ ፊደል፡ የመጀመሪያ ቅርጽ፡ አፍ ሳያስከፍት፡ ግዑዝ በሆነው በተፈጥሮ ድምፅ ብቻ የሚነገር መኾኑ፤

፬ኛ፦ የፊደሉ መነሻ "አ"፡ "አዳም" በሚል ቃል፡ በወንድና ሴት ጾታ፡ ለተፈጠሩት፡ ለመጀመሪያዎቹ ሰዎች፡ መጠሪያ ኾኖ መሰጠቱ፤

፭ኛ፦ ሌሎቹ የሰዎች ቋንቋዎችና ፊደሎቻቸው፡ በተናጋሪዎቻቸው ሕዝቦች ወይም ጎሣዎች ስም ሲጠሩ፡ "ግእዝ" ግን በራሱ ብቻ መጠራቱ፥

፮ኛ፦ በ"አ" ጀምሮ በ"አ" የሚፈጽም በመሆኑ፡ "አልፋና ኦሜጋ፥ መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ" ብሎ፡ ኋላ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ተብሎ ራሱን በሰውነት የገለጸው "እግዚአብሔር"፡ በዚህ ስሙ የታወቀበትና አምልኮቱ የሚፈጸምበት ቋንቋና ፊደል ኾኖ በሕያውነት እስከዛሬ እንዲቀጥል ማድረጉ፥

፯ኛ፦ በምድር ላይ የሚኖሩ የሰው ልጆች ኹሉ፡ ተወልደው፡ በሕፃንነታቸው፡ መናገር በሚጀምሩበት ጊዜ፡ ቋንቋቸውና ፊደላቸው የተለያዩ ሲኾኑ፡ አፋቸውን መፍታት፥ አባቶቻቸውንና እናቶቻቸውንም ለይተው መጥራት የሚጀምሩበት፡ "አባባ!"፥ "እማማ!" የሚባሉት ቃላት፡ "አብ አብ አብ"፥ "እም እም እም" የተባሉትን፥ ትርጉማቸው፡ "አባት አባት አባት"፥ "እናት፥ እናት፥ እናት" የኾነውን፡ ቀጥታ የግእዙን ቃላት መኾኑ ናቸው።

## የመደበኞቹ ሆህያት፡ ምሥጢራዊ ትርጓሜ።

፳፪ቱ ቀዳሚዎችና መደበኞች ሆህያት፡ ለየቅላቸው፡ በዚያው በግእዝ ባሕርያቸው፡ ስመ አምላክነት ያለው ምሥጢራዊ ትርጓሜ አላቸው። ይኸም እንደሚከተለው ነው፦

አ፡ "አሌፍ" ይባላል። በግእዙ፡ "አሌፍ ብሂል፡ 'አብ ፈጣሬ ኵሉ ዓለም'" የሚለው ትርጉሙ፡ "አሌፍ፡ 'ዓለሙን ኹሉ የፈጠረ፡ እግዚአብሔር አብ'" ማለት ነው።

በ፡ "ቤት" ይባላል። በግእዙ፡ "ቤት ብሂል፡ 'ባዕል እግዚአብሔር' የሚለው፡ "ቤት፡ 'እግዚአብሔር፡ ኹሉን የሚሰጥ ባለጸጋ'" ማለት ነው።

ገ፡ "ጋሜል" ይባላል። በግእዙ፡ "ጋሜል ብሂል፡ 'ግሩም እግዚአብሔር'" የሚለው፡ "ጋሜል፡ 'እግዚአብሔር፡ የሚያስፈራ አምላክ'" ማለት ነው።

ደ: "ዳሌጥ" ይባላል፤ በግእዙ "ዳሌጥ ብሂል 'ድልው እግዚአብሔር' የሚለው: "ዳሌጥ: 'እግዚአብሔር: በኹሉ ዝግጁ'" ማለት ነው::

ሀ: "ሂ" ይባላል:: በግእዙ: "ሂ ብሂል: 'ህልው እግዚአብሔር' የሚለው: "ሂ: 'እግዚአብሔር: በኹሉ አድሮ የሚኖር'" ማለት ነው::

ወ: "ዋው" ይባላል:: በግእዙ: "ዋው ብሂል: 'ዋህድ እግዚአብሔር' የሚለው "ዋው 'እግዚአብሔር በሥላሴ አንድነት የሚመለክ'" ማለት ነው::

ዘ: "ዛይ" ይባላል:: በግእዙ: "ዛይ ብሂል: 'ዝኩር እግዚአብሔር' የሚለው: "ዛይ: 'እግዚአብሔር: በፍጥረቱ ሲታሰብ የሚኖር'" ማለት ነው::

ሐ: "ሔት" ይባላል:: በግእዙ: "ሄ ብሂል: 'ሕያው እግዚአብሔር' የሚለው: "ሄ: 'እግዚአብሔር: ኅልፈት የሌለበት: ለዘለዓለም የሚኖር'" ማለት ነው::

ጠ: "ጤት" ይባላል:: በግእዙ: "ጤት ብሂል: 'ጠቢብ እግዚአብሔር' የሚለው: "ጤት: 'እግዚአብሔር: ጥበቡ የማይደረስበት'" ማለት ነው::

የ: "ዮድ" ይባላል:: በግእዙ: "ዮድ ብሂል: 'የማን እግዚአብሔር' የሚለው: "ዮድ: 'እግዚአብሔር: የቀኝ እጅ'" ማለት ነው::

ከ: "ካፍ" ይባላል:: በግእዙ: "ካፍ ብሂል: 'ከሃሊ እግዚአብሔር' የሚለው: "ካፍ: 'እግዚአብሔር: ኹሉን ቻይ አምላክ'" ማለት ነው::

ለ: "ላሜድ" ይባላል፤ በግእዙ "ላሜድ ብሂል 'ልዑል እግዚአብሔር' የሚለው: "ላሜድ: 'እግዚአብሔር: ከኹሉ የላቀ'" ማለት ነው::

መ: "ሜም" ይባላል:: በግእዙ: "ሜም ብሂል 'ምዑዝ እግዚአብሔር' የሚለው: "ሜም: 'እግዚአብሔር: መልካም ሽታ ያለው'" ማለት ነው::

ነ: "ኖን" ይባላል:: በግእዙ: "ኖን ብሂል: 'ንጉሥ እግዚአብሔር' የሚለው: "ኖን: 'እግዚአብሔር: ነገሥታትን የሚሠይም: ዘለዓለማዊው ንጉሥ'" ማለት ነው::

ሠ: "ሣምኬት" ይባላል:: በግእዙ: "ሣምኬት ብሂል: 'ሠፋኒ እግዚአብሔር' የሚለው: "ሣምኬት: 'እግዚአብሔር: በኹሉ ላይ የሠለጠነ ጌታ'" ማለት ነው::

ዐ: "ዔ" ይባላል:: በግእዙ: "ዔ ብሂል: 'ዐቢይ እግዚአብሔር' የሚለው: "ዔ: 'እግዚአብሔር: ታላቅ አምላክ'" ማለት ነው::

ፈ: "ፌ" ይባላል:: በግእዙ: "ፌ ብሂል: 'ፍቁር እግዚአብሔር' የሚለው: "ፌ: 'እግዚአብሔር: የፍጥረቱ ወዳጅ አምላክ'" ማለት ነው::

ጸ: "ጻዴ" ይባላል:: በግእዙ: "ጻዴ ብሂል: 'ጻድቅ እግዚአብሔር' የሚለው: "ጻዴ: 'እግዚአብሔር: እውነተኛ አምላክ'" ማለት ነው::

ቀ: "ቆፍ" ይባላል:: በግእዙ: ቆፍ ብሂል: 'ቅሩብ እግዚአብሔር' የሚለው "ቆፍ 'እግዚአብሔር: ለፍጥረቱ ቅርብ የኾነ አምላክ'" ማለት ነው::

ረ: "ሬስ" ይባላል:: በግእዙ: "ሬስ ብሂል: 'ርእስ እግዚአብሔር' የሚለው: "ሬስ: 'እግዚአብሔር: የፍጥረቱ ኹሉ ራስ'" ማለት ነው::

ሰ: "ሳን" ይባላል:: በግእዙ: "ሳን ብሂል: 'ስቡሕ እግዚአብሔር' የሚለው: "ሳን: 'እግዚአብሔር: በፍጥረቱ ዘንድ ሊመሰገን የሚገባው አምላክ'" ማለት ነው::

ተ: "ታው" ይባላል:: በግእዙ: "ታው ብሂል: 'ትጉህ እግዚአብሔር' የሚለው: "ታው: 'እግዚአብሔር: ፍጥረቱን: ዘወትር ተግቶ የሚጠብቅ ፈጣሪ'" ማለት ነው::

## ስለግእዝ ፊደል ሆህያት፡ አጭር ሐተታ፤ የሆህያቱ ፍጹምነትና ምሉእነት።

(ሆህያቱና አኀዛቱ፡ በገጽ ፬፻፹፭-፬፻፹፰ ላይ ይገኛሉ።)

"የመጀመሪያዎቹ ሰዎች መነጋገሪያ ቋንቋ ነበር" የሚባለውን፡ የግእዝን ፊደል ሆህያት፡ ፍጹማንና ምሉአን የሚያደርጓቸው ባሕርያት አሏቸው። ከነዚህ መካከል፡ የሚከተሉት ይገኛሉ።

፩ኛ፡- የግእዙ ፊደል፡ በሦስት ማዕርጋት ይመደባል። ይህም አመዳደብ የተመሠረተው፡ በየዘመናቱ፡ አስፈላጊነታቸው እየታወቀ፥ እየጨመረና እየተረጋገጠ በታከሉት የሆህያት ቁጥር ላይ ነው።

አንደኛው፡ ከ"አ" እስከ "ተ" ያሉትን፥ የ"ግእዝ ሆህያት" ተብለው የሚጠሩትንና ከዚሁ ከግእዝ ቋንቋ ጋር ለተፈጠሩት፡ ለ፳፪ቱ ሥነ ፍጥረታት ምሳሌ ኾነው የሚገኙትን፡ መደበኞቹንና "ቀደምቶቹን ፊደላት" የያዘው ነው።

ኹለተኛው፡ ከ"ጸ" እስከ "ቨ" ያሉትን፥ "ተረፈ ሆህያት" ተብለው፡ የቋንቋውንና የፊደሉን ምሉእነት፡ የፍጹም ፍጹም ለማድረግ፤ አስፈላጊነታቸው እየጸደቀ፡ በየጊዜያቱ የታከሉትን፡ ኋለኞቹንና "ተጨማሪዎቹን ፊደላት" የያዘው ነው።

ሦስተኛው፡ ከ"ጐ" እስከ "ቧ" ያሉትን፥ በመደበኞቹና በተጨማሪዎቹ ሆህያት ላይ በተቀረጹ ምልክቶች ምክንያት በመገኘታቸው፡ "ሕፁፃን ሆህያት" የተባሉትን "ያልተሟሉ ፊደላት" የያዘው ነው።

፪ኛ፡- ይህ ኢትዮጵያዊው ፊደል፡ የድምፅ ዓይነቶችን ኹሉ አሟልቶ የያዘ፥ ይልቁንም ሌሎቹ መሰሎቹ የቋንቋዎች ፊደላት፡ የሌሏቸውንና ያላስፈለጓቸውን ጭምር አጠቃልሎ የሚገኝ በመኾኑ፡ በአገሩ ውስጥ ብቻ ሳይኾን፡ በመላው ዓለም ያሉትን ቋንቋዎች ኹሉ ለማስተናገድ በመቻሉ ይረጋገጣል። ይኸውም፡ ለምሳሌ፡- እነ"ሐ፥ ጠ፥ ሠ፥ ዐ፥ ጸ፥ ቀ፥ ጰ፥ ፀ፥ ሸ፥ ቸ፥ ኘ፥ ጀ፥ ጨ፥ ዠ፥ ኸ፥ ኧ፥ ቐ፥ ዸ፥ ቨ"ን የመሰሉት ናቸው።

፫ኛ፡- በኢትዮጵያዊው ፊደል ውስጥ፡ በባሕርያቸው የተለያየ ድምፅ ያላቸው፥ በልማድ ግን፡ ተመሳሳይ ድምፅ ያላቸው መስለው የሚታዩት፡ እነ"አ፡ ዐ፥ ሀ፡ ሐ፡ ኀ፥ ሠ፡ ሰ፥ ጸ፡ ፀ"ን የመሳሰሉት፡ ከድምፃቸው ልዩነት በላይ፡ እያንዳንዳቸው በቋንቋ ላይ ተከሥተው ሲነገሩና በቃላት ውስጥ ተገልጸው ሲጻፉ፡ የሚሰጡት ትርጉም፡ ፍጹም የማይመሳሰል በመኾኑ፡ መደባቸውን እንዳለ ይዘው፡ ተጠብቀው ሊኖሩ ይገባቸዋል።

ይኸውም፡ አንዱ ዓይነት፡ ተመሳሳይ የሚመስል የቋንቋ ቃል፡ በድምፅ ሲነገርና ወይም በጽሑፍ ሲገለጽ፡ ፈጽሞ የተለያየ ትርጉም የሚሰጥ በመኾኑ ነው፤ ማለትም፡ እያንዳንዳቸው ተለይተው የሚታወቁበትን ስማቸውን በመጥራት፡ ለምሳሌ፡ ስለአልፋው "አ" እና ስለዓይኑ "ዐ"፥ ስለሃሌታው "ሀ" እና ስለሐመሩ "ሐ"፥ እንዲሁም ስለብዙኃኑ "ኀ"፥ ስለንጉሡ "ሠ" እና ስለእሳቱ "ሰ"፥ ደግሞም፡ ስለጸድቁ "ጸ" እና ስለፀሓዩ "ፀ" ጠለቅ ብለን ብንመለከት፡ ግእዙ ከሚያበረክታቸው፡ ከብዙ ፍቺዎቻቸው መካከል፡ የሚ. ለውን ማብራሪያ እናገኛለን።

"አብይ፥ አብዮት"፡ "እንቢ ማለት" ማለት ሲኾን፥ "ዐብይ፥ ዐብዮት"፡ "ታላቅ መኾን" ማለት ነው። "ሀለየ"፡ "በዜማ አመሰገነ"፥ እንዲሁም "ሐለየ"፡ "መማለጃ ሰጠ" ማለት ሲኾን፥ "ኀለየ"፡ "አሰበ" ማለት ነው፡ "ሰአለ"፡ "ለመነ" ማለት ሲኾን፥ "ሠዐለ"፡ "ሥዕል ሣለ" ማለት ነው። "ጸፈረ"፡ "ጥፍርን ቆረጠ" ማለት ሲኾን፥ "ፀፈረ"፡ "ወፍ በወጥመድ ያዘ" ማለት ነው። ከዚህ የተነሣ፡ ከኹለቱ ወይም ከሦስቱ ሆህያት፡ አንደኛውን ወይም ኹለተኛውን ወይም ሦስተኛውን መርጦና ለይቶ፡ ከፊደላቱ ገበታ አውጥቶ መጣል፡ የማይቻል በመኾኑ ይታወቃል።

በኢትዮጵያኛውም ቢኾን፡ ዛሬ፡ ከሥርዓት ውጪ ተዘውትሮ ሲደረግ እንደሚታየው፡ ባንድ በኩል፡ "ንጉሥ" የሚለው ቃል፡ "ንጉስ" ተብሎ ሲጻፍ፥ በሌላ በኩል ደግሞ፡ "ሰላም" ብሎ በመጻፍ ፋንታ፡ "ሠላም" ብሎ መጻፍ፡ የሰውን የተፈጥሮ መልኩን፡ በቀዶ ጥገና ለውጦና አጥፍቶ፡ በሌላ ገጽ እንደመተካት የሚቆጠር ነውና፥ የአነባበብና የትርጉምም ለውጥን ሊያስከትል ይችላልና፡ እያንዳንዱ ቃል፡ በሆህያቱ ተለይቶ የሚታወቅበት መልኩ እንዳይለዋወጥ፡ ሥርዓቱ ይጠበቅ ዘንድ፡ ጥንቃቄ እንዲደረግበት ያስፈልጋል።

፩ኛ:- የሆህያቱ መቀነስ፡ የቋንቋ ቀውስን በማስከተል፡ የሚጎዳው፡ ግእዝንና ኢትዮጵያኛውን ዐማርኛ ብቻ አይደለም፤ ነገር ግን፡ በኢትዮጵያ ውስጥ ላሉ፡ ለምሳሌ፡ ለትግርኛ፥ ለአፋርኛ ልሳናትና ከግእዝ ጋር፡ በጣም የቅረበ ዝምድና ላላቸው፡ እብራይስጥንና ዓረብኛን ለመሰሉት፡ ለሌሎች ባዕዳን ቋንቋዎች፡ የንግግርና የጽሑፍ አገልግሎት እጅግ የሚያስፈልጉትን፡ በጕረሮና በአፍ ሙሉ የሚነገሩትን፡ "ኸ"ን፥ "ዐ"ን፥ "ሐ"ን፥ "ኃ"ን፥ "ሠ"ንና "ፀ"ን፡ እነዚህን ኹሉ ማሳጣት ይኾናል። ለምሳሌ፡ "ኸ"፡ በ"ከ" እና በ"ሀ"፥ መካከል ባለ፥ "ዐ" ደግሞ፡ በ"አ" ላይ በተመሠረተ፡ በኃይለኛ የጕረሮ እስትንፋስ የሚነገሩ ድምፆችን የሚሰጡ ስለኾኑ፡ ለትግርኛ፥ ለአፋርኛ፥ ለዓረብኛና ለዕብራይስጥ፡ እጅግ ያስፈልጋሉ፤ ለኢትዮጵያኛው፡ ማለትም፡ ለዐማርኛ ግን፡ ይህን ያህል ላያስፈልገው ይችላል። በሌላ በኩል ደግሞ፡ በተለይ "ዐ"፡ እንደ"ሰ"፡ ለግእዝ፡ እጅግ ያስፈልገዋል፤ ምክንያቱም፡ "ሥዕል ሣለ" የሚል ትርጉም ያለውን፡ "ሠዓለ" የሚለውን ቃል፡ "ለመነ" የሚል ትርጉም ባለው፡ "ሰአለ" በሚለው፡ የአልፋው "አ" እና የእሳቱ "ሰ" ሆህያት ቢጻፍ፡ ትርጉሙ ጨርሶ ስለሚፋለስ (ስለሚለወጥ) ነው።

፭ኛ:- የኢትዮጵያዊው ፊደል፡ እያንዳንዱ ሆሄ፡ በሰባት መልኮች ተቀርፆና በሰባት ድምጾች ተነግሮ፡ ለአንደኛውን ጊዜ ተጠናቅቆ የተዘጋጀ በመኾኑ፡ የሥነ ጽሑፉ ክዋኔ፥ ቅልጥፍናና ደግነት፡ ከሌሎቹ ቋንቋዎች ኹሉ የተለየ አድርጎታል። ሆህያቱን፡ ለ"ፍጹምነት" ማዕርግ ያበቃቸው ልዩ ባሕርይ፡ እያንዳንዳቸው፡ በሰባት የተለያዩ ቅርጾች፥ መልኮችና ድምጾች ተመድበው የሚታወቁባቸው፡ ሰባት መለያ ስሞች ያላቸው መኾኑ ነው። እነዚህም፡ ከዚህ የሚከተሉት ናቸው:-

የመጀመሪያው: “ግእዝ” ይባላል፤ “መጀመሪያ” ማለት ነው:: አፍን ጥቂት ከፈት አድርጎ: በግዑዝ ድምፅ ብቻ ይነገራል:: የቋንቋውና የፊደሉ ስም: “ግእዝ” መባሉ: የመጀመሪያው ቋንቋና ፊደል: እርሱ መሆኑን ለማስረዳት ነው::

ኹለተኛው: “ካዕብ” ይባላል፤ “ኹለተኛ” ማለት ነው:: ድምፁ: ከንፈሮችን አጥብቦ: ወደፊት በመክበብ ይነገራል::

ሦስተኛው: “ሣልስ” ይባላል፤ “ሦስተኛ” ማለት ነው:: ድምፁ: ከንፈሮችን: ወደግራና ቀኝ አጥብቦ በማስፋት ይነገራል::

አራተኛው: “ራብዕ” ይባላል፤ “አራተኛ” ማለት ነው:: ድምፁ: አፍን: ወደላይና ወደታች በመክፈት ይነገራል::

አምስተኛው: “ሓምስ” ይባላል፤ “አምስተኛ” ማለት ነው:: ድምፁ: ከንፈሮችን በመካከለኛ መጠን ወደኋላ በማስፋት ይነገራል::

ስድስተኛው: “ሳድስ” ይባላል፤ “ስድስተኛ” ማለት ነው:: ድምፁ: ጥርስን ገጥሞ: ከንፈሮችን በማላቀቅ ይነገራል::

ሰባተኛው: “ሳብዕ” ይባላል፤ “ሰባተኛ” ማለት ነው:: ድምፁ: አፍን ወደላይና ወደታች ከፍቶና ከንፈሮችን ወደኋላ አጥብቦ: በኃይል በመክበብ ይነገራል::

፩ኛ:- እዚህ ላይ: በልማድ የገባ ታላቅ ስሕተት መኖሩን፥ ሊታረምም የሚገባው መኾኑን: በአጽንዖት ማዘከር ይገባል:: ይኸውም: ግእዙ “አ”: እንደራብዑ “ኣ”፥ ግእዙ “ዐ”: እንደራብዑ “ዓ”፥ ግእዙ “ሀ”: እንደራብዑ “ሃ”፥ ግእዙ “ሐ”: እንደራብዑ “ሓ”፥ ግእዙ “ኀ”: እንደራብዑ “ኃ”: አፍ በሚያስከፍት ድምፅ መነገራቸው ነው:: ከላይ እንደተዘረዘረው: “አ”: “ዐ”: “ሀ”: “ሐ”: “ኀ”: እንደ “በ”፥ “ገ”፥ “ደ”: “አፍ የማያስከፍት: ግእዝ ናቸው” ብለን: በስማቸው ለይተን ከጠራናቸው በኋላ: እንደገና: የሌላ በኾነው: በራብዑ መጥራት: ፍጹም ስሕተት ስለኾነ: ጨርሶ ሊታረም የሚገባው ነው:: አለዚያ: “በ”ን: “ባ”፥ “ገ”ን: “ጋ”፥ “ደ”ን: “ዳ” ብሎ ማንበብ: “ትክክል ነው” እንደማለት ይቆጠራል:: በዚህ መሠረት: ለምሳሌ “አዲስ አበባ” ብለን ለመጻፍ: “ኣዲስ ኣበባ” ብለን መጻፍ አለብን ማለት ነው:: ወይም: አሁን እየተጻፈ እንዳለው: “አዲስ አበባ” ይኹን ካልን: አነባበቡ: “እዲስ እበባ” ይኾናል ማለት ነው::

፪ኛ:- በዚህ ረገድ: ይህ የግእዝ ኢትዮጵያኛ ፊደል: በዓለም ላይ ካሉ ቋንቋዎች ኹሉ ይልቅ: ለማንበብና ለመጻፍ ብቻ ሳይኾን: ለመማር፥ ለማስተማርና ለማወቅም ጭምር: እጅግ የቀለለና የቀለጠፈ ነው ሊባል ይቻላል:: ይኸውም: ቀደም ብሎ እንደተገለጸው: በግእዝ የተለያየ ትርጉምን ከሚያስጡት: ከጥቂቶች በቀር: አንድ ቃል: በኢትዮጵያኛ የሚጻፈው: ቋሚ ኾኖ፥ ለአንዴና ለመቼውም ጊዜ እንደማይለወጥ ተደርጎ: በተወሰኑ ሆህያት ብቻ ነው::

ይህንንም: በአጭር መግለጫ ማስረዳት ይቻላል፤ በላቲን ፊደል የሚጠቀመውን: እንግሊዝኛን: በምሳሌነት ወስደን: "boat" (ቦት = ጀልባ) የሚለውን ቃሉን ብንተችበት: ይህን አንድ ቃል: በኢትዮጵያኛው: የምንናገረው፥ የምንጽፈውም: “ቦት” ብለን: በአንድ ቃል ብቻ ሲኾን: በእንግሊዝኛ ግን: በብዙ መልክ እንጽፈዋለን፤ እንናገረዋለንም:: ይህም: እንዲህ ነው:- bot, bote, bought, bowt, bhot, boht, boet, bott, botte, boatt, boate, boatte, boete, boette… እንዲህ እያለ ሊቀጥል ይችላል::

## የግእዝን ሆሆያትና አኀዛት፡ ማጥቃት ለምን አስፈለገ?

የግእዝ "ሆሆያት ይቀነሱ!"÷ አኀዛትም ይወገዱ!" የሚለው አሳብ፡ ጥንቱኑ እንዴት ተጸነሰ? በዚህ አሳብ ተስማምተውና እንደሌላው ኹሉ፡ ሥርዓቱን፡ በገዛ ሥልጣናቸው አፍርሰው÷ በኢትዮጵያዊው ፊደል ላይ ሊፈጸም፡ ከረዥም ጊዜ ጀምሮ ሲታቀድ የቆየውን ግድያ፡ ዛሬ፡ በድፍረትና በገሃድ ከማካኼድ ያልተመለሱ መኖራቸው ቢታወቅም፡ እንዲያው፡ ቀድሞውኑ፡ "አሳቡ ከወዴት መጣላቸው?" የሚያሰኝ ነው::

በአሁኑ ጊዜ፡ በዓለም ላይ ካሉ አገሮች መካከል፡ ለመኾኑ የትኛው አገር ነው፡ ሆሆያቱን የቀነሰ? ወይም አኀዙን የለወጠ? ጨመሩበት እንጂ አልቀነሱም:: ምናልባት፡ እንዲህ ያደረጉ ካሉ፡ የሚነቀፉ እንጂ የሚሞገሱ አይደሉም፤ ቱርክን የመሰሉትን ማለት ነው:: እጅግ ሠለጠኑ የተባሉት፡ አሜሪካና እንግሊዝ÷ ፈረንሳይ÷ ጀርመን÷ መስኮብ÷ የላቲን አገሮች÷ ጃፓንና ቻይና÷ የዓረብኛ ተናጋሪዎች እንኳ ሳይቀሩ፡ እያንዳንዳቸው፡ ብዙ የሚያስቸግር÷ እጅግ ውስብስብና ከባድ የኾነውን የየራሳቸውን ቋንቋ፡ "ለሥልጣኔያችን እርምጃ፡ መሰናክል ወይም ሳታች ኾኖብናልና፡ እናሻሽል! ፊደላቱን እንቀንስ! ወይም አኃዞቻችንን እናስቀር!" አላሉም:: የእኛዎቹ "ተራማጆች"፡ ወይም "ተስፈንጣሪዎች"፡ ታዲያ ምን ነካቸው? ምን ዓይነት አባዜስ ተጠናወታቸውና ነው፡ የሚያኮሩንንና የሚያስከብሩንን፡ ፊደሎቻችንንና አኃዞቻችንን፡ መቀነስ ብቻ ሳይኾን፡ ጨርሰን፡ "እንሠርዝና በሌላ ባዕድ፡ ያውም፡ በላቲን ፊደል እንተካቸው!" የሚሉት?

ቋንቋ እንደነፍስ ሲኾን፡ ፊደል ደግሞ፡ እንደሥጋ ነው:: ነፍስ በሥጋ አካል ገዝፋ እንደምትታይና እንደምትሠራ ኹሉ፡ ቋንቋም፡ ሕያው ኾኖ÷ ተገልጾ የሚሠራው በፊደል ነው :: እንዲህ ከኾነ፡ አንዲቷን የፊደል ሆሄ÷ አኃዝ ወይም ነጥብ መለወጥ ወይም ማጉደል፡ ከሰውነት አካል፡ አንዱን አባል ቆርጦ እንደመጣልና አካለ ጐደሎ እንደማድረግ ይቆጠራል:: ስለዚህ፡ በዚህ አግጣጫ ሆሆያቱን ለመቀነስ ወይም ለማሻሻል÷ ከዚያም አልፎ ለመለወጥ የተደረገውና የሚደረገው ጎጂ ሙከራ፡ ከላይ እንደተገለጸው፡ በአገርና በማንነት ላይ የተፈጸመ ታላቅ በደልና ወንጀል ከመኾኑ ጋር፡ ከባዕዳን ጋር በመመሣጠር፡ ባለጸጋውን የግእዝን ግምጃ ቤት፡ እንዲበለጽግ በማገዝ ፋንታ፡ ኾን ተብሎ፡ በበለጠ ለማራቆት የሚካኼድ፡ የጠላትነት አድራጎት በመኾኑ፡ ሙከራውን በጊዜው ማክሸፍና ተገቢውን ጥንቃቄ ማደራጀት፡ በብርቱ ያስፈልጋል::

በዚህ ረገድ እየተካኼዱ ላሉ ድርጊቶች፡ አቶ ሐዲስ ዓለማየሁ የተባሉት ደራሲ፡ የፈጸሙትን "ሙያ"፡ በማስረጃነትና በምሳሌነት ማቅረብ ይቻላል:: እኝህ ደራሲ፡ "ፍቅር እስከመቃብር" በሚለው መጽሐፋቸው መቅድም ውስጥ እንደገለጹት፡ ስለሆሆያታችን ያላቸው አስተሳሰብ፡ የፊደላችንን መቀነስ የሚደግፍ÷ በደረሷቸው መጻሕፍት የተጠቀሙትም፡ በተቀናነሱት ሆሆያት ብቻ በመኾኑ፡ አስተሳሰባቸውም ኾነ አድራጎታቸው፡ ከባዕዳኑ ተቃዋሚዎች ሊለይ አይቻልም:: ደራሲው፡ ስማቸውን፡ "ሀ"ዲስ "አ"ለማየሁ ብለው በመጻፍ፡ ያሳዩት የወንጀለኛነት ጥፋት፡ የራሳቸውን ኢትዮጵያዊነት፡ በሌላ ማንነት መለወጣቸውን ከማረጋገጡ በቀር፡ የስማቸው ቃላት ሆሆያት፡ ኹለንተናዊ ልዕልናና ክብር፡ በምንም ሊነካ የማይቻል መኾኑ ሊታወቅ ይገባል::

ደግሞ፡ ሆህያቱንና አኀዛቱን የያዘው፡ የዚህ ፊደል ባለቤቱ፡ "ኢትዮጵያኛ" የተባለው የዐማርኛም አባቱ የኾነው፡ ራሱ ግእዝ ስለኾነ፡ በእነዚህ ንብረቶቹና ሀብቱ ላይ፡ ማንም ባለመብት ኾኖ፡ "ይቀነስ!"፥ "ይሻሻል!" ወይም "ይለወጥ!" ሊል አይችልም። ባለአደራዎቹ፡ የኢትዮጵያ ቤተ ሕዝብ፥ ቤተ ክህነትና ቤተ ምልክና፡ በዛሬዎቹ መሪዎቻቸው ምክንያት፡ የአደራ ግዴታዎቻቸውን መጠበቅ ቢያቅታቸውም፡ ግእዝ፡ በባሕርዩ፡ የቅዱሱ ኪዳን መለኮታዊ ሥራ፥ ጸጋና ቅርስ ስለኾነ፡ የጠላቶቹን የተቃውሞ ኃይል ተቋቁሞ፡ እስከዛሬ፡ በሕያውነት እንደኖረ ኹሉ፡ ወደፊትም ራሱን ችሎና ጠብቆ፡ በዚሁ ህልውናው የሚቀጥል መኾኑን፡ ተፃራሪዎቹ ኹሉ፡ ሊያውቁት ይገባል።

## ባለአደራዪቱን ራሷን፡ እንደአጥፊ ሲያስቆጥሩዋት።

በአሁኑ ጊዜ፡ በቤተ ክህነት ውስጥና በስሟ በኩል ሳይቀር፡ በሚታተሙ መጻሕፍቶች፥ በሚተላለፉትም ደብዳቤዎች ላይ ኹሉ፡ ገጾችና ቁጥሮች፡ ቀንና ዓመተ ምሕረት ጭምር፡ የሚጻፉት፡ ፻፳፫ በሚለው በግእዙ አኀዝ ሳይኾን፡ 123 በሚለው የባዕዳን አኃዝ አይደለምን? በየትምህርት ቤቶችም ውስጥ፡ የቤተ ክህነት በኾኑት ሳይቀር፡ የፊደላትና የአኀዛት ትምህርት መሰጠቱ ቀርቶ የለምን? ይህም፡ የዛሬዎቹ ጳጳሳት ተልእኮ፡ ይህንኑ የባዕዳን ሴራ ማስፈጸም መኾኑን የሚያመለክት፡ አንዱ ማስረጃ ነው።

ይህን የመሰለው የጳጳሳቱ ተልእኮ የተከናወነ መኾኑን በዓይኔ አይቼ ያረጋገጥኩት፡ በናዝሬት ከተማ፡ በቤተ ሕዝቡ ታላቅ ጥረትና ትብብር፡ በከፍተኛ ወጪ ተሠርቶ፡ ቅዳሴ ቤቱ፡ በቤተ ክህነቱ እጨጌ፡ በአባ ጳውሎስና በሌሎቹም ጳጳሳት ተከብሮ፡ በቅርቡ በተመረቀው፡ በአዲሱ የመድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ሕንፃ ግምባር ላይ፡ ሥራው የተወጠነበትን ዘመን የሚያመለክተው ዓመተ ምሕረት፡ በታላላቅ መጠን የተቀረጸው፡ ፲፱፻፹፪ ተብሎ ሳይኾን፡ 1982 ተብሎ፡ በባዕዳን አኀዝ መኾኑን በተመለከትኩበት ጊዜ ነበር።

ቤተ ክህነት፡ የራሷ በኾነው ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ላይ፡ ሐውልት ኾኖ ሲነበብ በሚኖር፡ የዕብነ በረድ ሰሌዳ ላይ፡ የራሷ ቅርስ የኾነውን አኃዟን ማስቀረፅ አቅቷት፥ ቤተ ሕዝቡም፡ በዚሁ ድክመቷ ተባባሪ ኾኗት፡ የባዕዱ አኀዝ፡ እንዲህ እንዲሠለጥን ካደረገች፡ "እስመ ቅንዓተ ቤትከ በልዓኒ"፡ ማለትም፡ "በቤተ መቅደስህ ላይ ስለሚፈጸመው በደል፡ ያደረችብኝ ቅንዓት አቃጠለችኝ!" የሚለው አምላካዊ ቃል፡ ከኹሉም ልቡና ተለይቶ የራቀ፥ ነገሩም ያለቀለት መኾኑን ተገነዘብኩ።

ኢትዮጵያዊ እንደኾነው፡ እንደሌላው ነገር ኹሉ፡ ባለቤቱም ግእዝ፡ ባገሩና በቤቱ፥ በራሱም ወገኖች ዘንድ፡ ይህን የመሰለው ጥቃት ሲደርስበት፡ ለራሱ የተሰማውን ስሜት፡ ማንም ሊናገርለት የሚችል ያለ አይመስለኝም፡ ለነገሩ ግን፡ ሳስጎበኙኝ፡ ላሠሪዎቹ የቤተ ሕዝቡ ተጠሪዎች፡ ጉዳዩን በጥልቀትና በምሬት አስረድቻቸው፡ ያን ባዕድ ቁጥር፡ በባለቤቱ አኀዝ እንዲያስቀይሩት፡ አደራ ጭምር አሳስቤአቸው ነበረ። በባለቤቱ፡ በግእዝ ስም ያቀረብኩት አደራዬ፡ እንዳልተፈጸመም፡ በቅርቡ፡ እቦታው ድረስ ኼጄ አረጋግጫለሁ።

ይህ ነገር: ከዛሬ ሰላሣ አምስት ዓመታት በፊት: አሳስቤ የነበረውን: አንድ ጉዳይ አስታወሰኝ:: ይኸውም: በአዲስ አበባ ከተማ: በብሔራዊው ሸንጎ የደወል ግምብ ላይ ያለው ታላቅ ሰዓት: "የተጻፉበት አኀዞችና የሰዓቱ አቆጣጠር: በኢትዮጵያኛ ሊኾን ይገባል" ብዬ: የቤተ ሕዝቡ ምክር ቤት (Parlement ፓርለማ) አባል በነበርሁበት: ገና በ፲፱፻፶፯ ዓ. ም. ለምክር ቤቱ ጉባዔ: በጽሑፍ አቅርቤው የነበረው የውሳኔ አሳብ ነው::

## በባዕዳኑ ስለተፈናቀሉት:<br>ኢትዮጵያኛ ቃላትና አኀዛት::

በእነዚሁ ሆህያትና አኀዛት ተከናውነው የተሠሩትን: ኢትዮጵያኛ ቃላትና ቁጥሮች: በሌሎች ባዕዳን ቃላትና አኃዛት ለውጦ መተካት: ኢትዮጵያዊውን ሰብአዊ አካል: ማንነቱን: በሕክምና ቀዶ ጥገና እንዲለውጥ እንደማድረግ ይቆጠራል:: ለምሳሌ: ይህን መጽሐፍ የደረስኩበት የጽሕፈት መሣሪያ: በእንግሊዝኛ: "computer"፥ በኢትዮጵያኛ ደግሞ: "መቀመሪያ" ሊባል ሲገባ: "ኮምፒዩተር" ተብሎ በኢትዮጵያኛው ሆህያት ቢጻፍ: መልኩ ምን እንደሚመስል: ራሱ መቀመሪያው: ሆህያቱን ቀይሮ የሚያሳየንን እንመልከት:- "ሰቅቀቆቋቍሰቕ":: እጅግ ያስጸይፋል! አይደለም?

ኢትዮጵያዊው አኃዝ: ወደፊት: ለሒሳብ አሠራርና አያያዝ እንደሚጠቅም ኾኖ ተጠንቶ እስኪዘጋጅ ድረስ: ባዕዳን አኃዞች: በየቋንቋዎቻቸው: በሚሰጡት ግልጋሎት መልክ: እርሱም: ለጊዜው: የሒሳብ አያያዝንና አሠራርን ከሚመለከተው በቀር: በቀየው መደቡ: የአኃዝነት አገልግሎቱን እንዲቀጥል ማድረግ ተገቢና አስፈላጊ ይኾናል::

በምሥጢራት: እጅግ በተራቀቁ: የግእዝ ቃላትና አኃዛት: የበለጸገ ቋንቋ ያላት ኢትዮጵያ: ተቆልፎ የታሸገውን ቤተ መዛግብቷን: ልጆቿ: ከፍተው ለማየት አቅቷቸው: ወይም: ባለመፈለጋቸው ብቻ: እንደችግረኛ ተቆጥራ: በራሷ ቃላትና አኃዛት መጠቀም እየቻለች: አሁንም: ከባዕዳኑ ስትበደርና ስትዋስ መታየቷ: እውነተኞች ኢትዮጵያውያንን: ገና: ቅር እያሰኛቸው ያለ: አንዳንድ የቀረ ድክመት መኖሩን ያመለክተናል:: ይህም ሲባል: አልፎ አልፎ: በኢትዮጵያኛው ቋንቋ መካከል ይሠነቀሩ የነበሩትን: የባዕዳኑን ቃላት: በተለይም የእንግሊዝኛ የኾኑትን: ከግእዝ በተወረሱ ቃላት ተክቶ የመጠቀሙ ይዞታ: ከቅርብ ጊዜ ወዲህ: በበለጠ እየተጠናከረ በመኼዱ: በዚህ ረገድ: የሚያኰራ መሻሻል እየተደረገ መኾኑን ባለመዘንጋት ነው::

ተፈጥረው ከኖሩበት የኢትዮጵያዊነት ቦታቸው ተፈናቅለው በባዕዳን ቃላት በመተካታቸው: የአቤቱታ ጩኸታቸውን: አዘውትረው ከሚያሰሙት: የቀሩ: ጥቂ ኢትዮጵያኛ ቃላት መካከል: ወደፊት በእውነተኛው ኢትዮጵያዊ የቋንቋ ባለሥልጣን ተቋም እስኪጸድቁ ድረስ: ወደጥንታዊው የህልውና መካናቸው ተመልሰው: አገልግሎታቸውን መስጠት ይቀጥሉ ዘንድ: ያጋጠሙኝን: በዚህ መጽሐፍ መጨረሻ ገጾች ላይ (ከገጽ ፩፻፹፱-፩፻፺፯) ተዘርዝረዋልና: በእነዚሁ ቃላታችን እየተጠቀምን እንድንቆይ አሳስባለሁ:: በዚህ መጽሐፍ ውስጥ: የራሳችን: የኢትዮጵያኑ ከኾኑት በቀር: በባዕዳኑ: በአንዳቸውም ባለመጠቀሜ: መዝገበ ቃላታችን፥ እንዲሁም: የፊደላችን ሆህያትና አኀዛት: ለቋንቋችንና ለሥነ ጽሑፋችን: ብቁ መኾናቸውን ለማረጋገጥ የቻልሁ ይመስለኛል::

## ኢትዮጵያ፡ የሊቃውንቷን ምግባር ስትፋረድ!

የዘመኑ የኢትዮጵያ ትውልድ፡ በትውፊት የደረሰውንና ዛሬ እየተወቀሰበት ያለውን፡ ይህን የመሰለውን፡ የተዝረከረከና ባለቤት ያጣ፡ የብሔራዊ ውርስ አያያዝ፡ ቀደም ብሎ፡ በጊዜው ሊያስተካክለውና ሊያዳብረው በተገባ ነበር። ነገር ግን፡ ይህን ማድረግ አልተቻለውም፤ ምክንያቱም፡ ያ፡ የአጼ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት፡ የዚህ ተግባር አገልጋዮች የኾኑት ምሁራንና ሊቃውንት፡ ሙያቸው፡ የዕለት ጉርስ እንኳ የማያስገኝ፡ ርካሽ እንዲኾን፥ እነርሱ፡ "ቄሶች" ተብለው፥ ተግባራቸውን የሚያካኺዱበት ተቋም፡ "የቄስ ትምህርት ቤት" በሚል የመዘበቻ ስያሜ እንዲጠሩ በማድረጉ፡ በባሕርዩ፡ ኢትዮጵያዊ የኾነው ነገር ኹሉ፡ በራሱ በትውልዱ ዘንድ፡ እንዲናቅና እንዲዋረድ፥ እንዲጠላም በመኾኑ ነበር።

በዚህ ጉዳይ፡ ከማናቸውም ቤቶች ይልቅ፡ በባለአደራነቷ፡ የበለጠ የኃላፊነት ተጠያቂነት ያለባት፡ ቤተ ክህነት ምን አደረገች? አሁንስ ምን እያደረገች ነው? የሚለውን ጥያቄ ማቅረብና ተገቢውን መልስ ማግኘት ያስፈልግ ነበር። ዳሩ ግን፡ ዛሬ፡ በቤተ ክህነት በኩል እየተካኼደ ያለውን ኹኔታ፡ በገዛ ዓይኖቹ የሚያየው፡ ማናቸውም እውነተኛ ተመልካች፥ ወይም፡ የዚህ መጽሐፍ አንባቢ፡ እስከዚህ ዓምድ ድረስ እንደዘለቀው፡ ኹሉንም የተገነዘበው ስለኾነ፡ ወደሌላ ተጨማሪ ሐተታ መኼድ አስፈላጊ መስሎ አልታየኝም።

ከዚህ ይልቅ፡ ነገሩን፡ በጥሩ ምሳሌነት ሊያስረዳና አጥጋቢ የኾነውን መልእክት ሊያስተላልፍ በሚችል፡ በአንድ ልዝብ ቀልድ፡ ላጠቃልለው እወድዳለሁ። ይኸውም፡ አንድ ያገሬ ተወላጅ፡ ታምሞ፡ በአልጋ ላይ እየማቀቀ ሣለ፡ ሊጠይቁት የኼዱት ወዳጆቹ፡ እንደኢትዮጵያውያን ልማድ፡ "እግዚአብሔር ይማርህ!" ባሉት ጊዜ፡ "የሚቀትረኝ (ማለትም፡ በሕመም ጥሎ የሚገድለኝ) ማን ኾነና!" ብሎ የመለሰላቸውን ያስታውሳል።

## በስብሳቢው ማንነት የታወቀው፡ የቤተ ክህነት ሊቃውንት ጉባዔ ተጠያቂነት።

ይህን ታላቅ ብሔራዊ በደል በሚመለከት፡ ከየራሳቸው ጀምሮ፡ በሰብአዊው ሕሊና፥ በቤተ ሕዝቡና በእግዚአብሔር አደባባይ ፊት፡ በኃላፊነት የሚጠየቁት፡ ጳጳሳቱ ብቻ አይደሉም። በተለይ፡ በደርግ ምጽአት ዋዜማ ላይ፡ በሰበካ ጉባዔ የተጠናከረችው ቤተ ክህነት፡ ከዚህ በላይ ስለተዘረዘሩት ጉድለቶች፡ ያለባትን ግዴታና ኃላፊነት ሳትፈጽም በመቅረቷ፡ ከሌሎቹ ጋር፡ በይበልጥ፡ ከተጠያቂነት ሊያመልጥ የማይችለው፡ "የሊቃውንት ጉባዔ" የሚባለው፡ የቤተ ክህነቱ አንዱ ክፍል ጭምር ነው እንጂ። ይህ ጉባዔ፡ "ይህን የመሰለውን ግዳጅ ለመፈጸም ዐቅም የለውም" እንዳይባል፡ እንኳንስ፡ መላውን አባሎች የያዘው ጉባዔ ይቅርና፡ የጉባዔው ሰብሳቢ የነበሩት፡ አለቃ አያሌው ታምሩ የሚባሉት የቤተ ክህነት ምሁር ብቻ እንኳን፡ ግዳጃቸው በኾነው በዚህ ተግባራቸው፡ ምን ዓይነት አስተዋጽዖ ሊያበረክቱ እንደሚችሉ፡ በሊቃውንት ጉባዔ ሰብሳቢነታቸው፡ ሲፈጽሙት በኖሩት ሥራ፡ በቀላሉ ይታወቃል።

ይኸውም፡ እኚሁ ሰው፡ ከነበራቸው እውቀት፥ ችሎታና ተደማጭነት አኳያ፡ ከአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ጀምሮ፡ ዛሬ እስካሉት እጨጌ፡ እስከአባ ጳውሎስ ድረስ፡ በትረ ሥልጣኑን፡ በየተራ እየተከታተሉ በያዙት፡ ሥጋውያንና መንፈሳውያን ገዢዎችና ባለሥልጣናት ፊት፥ በየአደባባዩም፡ በሕዝብ መካከል እየቆሙ፡ በስፋት ያሰሙት የነበረው፡ ውዳሴና ስብከት፡ በብዙዎች ዘንድ የሚታወስ በመኾኑ ነው።

## የሊቃውንት ጉባዔ ግዳጅ፡ ሳይፈጸም መቅረቱ።

የሊቃውንት ጉባዔ ግዳጅ፡ አንድ ብቻ ነው፤ ይኸውም፡ የኢትዮጵያን ሃይማኖታዊ ቅርስ መጠበቅና ማሳወቅ። ነገር ግን ግዳጁ፡ በትክክል ተፈጽሞ ለመልካሙ ፍሬ አልበቃም።

የጉባዔው ሰብሳቢ፡ አለቃ አያሌው፡ በአሁኑ ጊዜ፡ የራሳቸው የግል ክብርና ጥቅም ስለተነካባቸው ብቻ፡ እንዲያ ያወድሷቸው በነበረው፡ በዘመኑ እጨጌ፡ በአባ ጳውሎስ ላይ፡ የተቃውሞና የውንጀላ ክስን፡ በብርቱ በመሠንዘር፡ ጩኸታቸውን፡ በተገኘው መስመር ኹሉ፡ በቃልም፥ በነፋስ ድምፅም፥ በጦማረ ሕዝብም፡ የቱን ያህል እያሰሙ እንደኾነ፡ ኹኔታውን የሚከታተለው ማናቸውም ሰው ያውቀዋል። እርሳቸውም፡ "በአባ ጳውሎስ ላይ፡ ይህን የማደርገው፡ በሊቃውንት ጉባዔ ሰብሳቢነቴ ነው" ስለሚሉ፡ "ታዲያ! ከዚህ ይልቅ፡ ከላይ ስለተጠቀሱት የባለአደራነት ጉድለቶች፥ በጠቅላላም፡ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ስለተብራሩት ቁም ነገሮች፡ ለምን አልተናገሩም? ወይም፡ ሊኾን የሚገባውን ለምን አላደረጉም?" ተብለው፡ በማናቸውም አስተዋይ ተመልካች ዘንድ ቢጠየቁ፡ ምን ምላሽ ሊሰጡ ይኾን?

መቼም፡ ሌላ የሚያደርጉት ነገር እንኳ ባይኖር፡ ቢያንስ፡ ቢያንስ፡ ያው፡ በታወቀው ተናጋሪነታቸውና አወዳሽነታቸው፡ "በአንደበትዎ እንኳ፡ ከቶ ምን ቃል አሰሙ?" ተብሎ ለሚቀርብላቸው ጥያቄ፡ የሚሰጡት ምላሽ፡ ምን ይኾን? ደርግ፡ "እግዚአብሔር የለም!" ብሎ፥ "ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ" የሚለውንም፡ የኢየሱስ ክርስቶስን መለኮታዊ ማኅተም ሽሮ በተነሣና ራስዋ ቤተ ክህነት ቀብታ፡ ዘውዱን ያቀዳጀቻቸውን አጼዋን፡ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን፡ ከዙፋን አውርዶ፡ በእሥር ቤት ውስጥ በጣላቸው ጊዜ፥ በመጨረሻም፡ በግፍ በገደላቸው ጊዜ፡ ምን ተናገሩ? በጊዜው፡ እጨጌ ከነበሩት፡ ከአባ ቴዎፍሎስ ጋር፡ በኹሉም ነገር፡ ተባባሪ አልነበሩምን? ከዚያ በኋላ፡ በተከታታይ ከተተኩት፡ እጨጌዎች ጋር፡ ዛሬ እስካሉት፡ እስከአባ ጳውሎስ ድረስ፡ እርሳቸውንም፡ በግል ጥቅምና ሥልጣን ምክንያት እስኪጣሏቸው ድረስ፡ የኹሉም ግብረ አበር ኾነው አልኖሩምን? በመጨረሻስ፡ ከዛሬው እጨጌ፡ ከአባ ጳውሎስ ጋር ጸብ ክርክር የጀመሩት፡ በላያቸው፡ ሊቀ ጳጳስ በመሾም እና/ወይም በጡረታ እንዲገለሉ በማድረግ፡ በጥቅማቸውና በክብራቸው ላይ ስለመጡባቸው አይደለምን?

ሥጋውያን፥ ዓለማውያን የኾኑ ሰዎች፡ የአድር ባይነት ጠባይና ተግባር ቢታይባቸው፡ ላያስደንቅ ይችላል፤ ምክንያቱም፡ በአቋማቸው፡ ሥጋውያን፥ ዓለማውያን ስለኾኑ ነው! ነገር ግን፡ በሃይማኖታውያንና በመንፈሳውያን ዘንድ ግን፡ ይህን የመሰለው ኹኔታ ሲከሠት፡ እጅግ ያሳፍራል?

ጳጳሳቱንና አለቃ አያሌውን የመሰሉትን ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት፡ በዓለም ሕዝብ ፊት ሳይቀር፡ ከአሳዛኝ ግምት፥ ትዝብትና ቅሌት ላይ የጣላቸው፡ ይኸው እንደኾነ፡ ተደጋግሞ ተነግሩዋል:: በእኒሁ ሰዎቿ ምክንያት፡ ስመ ጥሩዋና ገናናዋ የኢትዮጵያ ቤተ ክህነት፥ ሃይማኖቷ ሳይቀር፡ በባዕዳኑ ብቻ ሳይኾን፡ በራሷ ልጆች ዘንድ ጭምር፡ ከጽኑ ጥርጣሬ ላይ መውደቋ፡ አሌ ሊባል ከቶ አይቻልም::

የሊቃውንቱ ጉባዔ ሰብሳቢ፡ አለቃ አያሌው፡ በነበራቸው ኃላፊነትና ዛሬ በሚገኙበት ኹኔታም ቢኾን፡ እንዲህ፡ "ሥልጣኔ ለምን ተነካብኝ?" በማለት፡ የራስን ጥቅም ለማስጠበቅ፥ ወይም፡ በቀልን ለመወጣት ሲባል ብቻ፡ በማያስፈልግ ውዝግብና ንትርክ፡ ጊዜያቸውንና የአእምሮ ኃይላቸውን፥ እውቀታቸውንና ችሎታቸውን ከማባከን ይልቅ፡ ቤተ ክህነት፡ በሃይማኖታችን ብቻ ሳይኾን፡ በቋንቋችን፥ በፊደላችንና በሥነ ጽሑፋችን፡ በጠቅላላም፡ ከዚህ በላይና በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በተተቸባቸው የባህል ይዞታዎቻችን ላይ ጭምር ስለደረሱት ቀውሶች፡ ተገቢው እንዲፈጸም መታገሉ አይሻልም ነበር ወይ?

## የሃይማኖትን አቋም የሚያናጋ ደማሚት::

ለነገሩማ፡ አለቃ አያሌው፡ ቀደም ብለው፡ በድፍረት ይፈጽሟቸው በነበሩት ግልጽ ስሕተቶች፡ "ኻይ! ይተዉ እንጂ!" የሚል፡ የበላይ ተመልካችና ተቆጣጣሪ ባለመኖሩ ነው እንጂ፡ ብዙ ጉድለቶች አሉ አይደለምን? ከእነዚህም መካከል፡ አንዱቱን ብቻ በምሳሌነት እጠቅሳለሁ:: ይህም፡ በእርሳቸው ሰብሳቢነት ይመራ የነበረው፡ የቤተ ክህነቱ የሊቃውንት ጉባዔ፡ ራሱ ተርጉሞ፡ በትንሣኤ ማተሚያ ድርጅት ባሳተመው፡ በግእዙ አዲስ ኪዳን ነጠላ ትርጓሜ ውስጥ፡ የተጻፈ፡ አንድ ከባድ ቃልን ይመለከታል::

ያም ቃል፡ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ተጽፎ እንደሚነበበው፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በቃና ዘገሊላ የሠርግ ቤትና በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሳለ፡ እናቱን ቅድስት ድንግል ማርያምን በመጥራት፡ የተጠቀመበት ነው:: እርሱም፡ "አባትህንና እናትህን አክብር!" የምትለዋን መለኮታዊት ሕግ፡ ጥንት፡ በኪዳነ ልቦና፡ በመጀመሪያዎቹ ሰዎች ሕሊና፥ ኋላም፡ በኪዳነ ኦሪት፡ በታቦተ ጽዮን ጽላት ላይ ጽፎ የሰጠው፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ቅድስት እናቱን የጠራበት ቃል፡ "ማንም ሰብአዊ ልጅ፡ ለወለደችው እናቱ፡ ባለው ፍቅርና አክብሮት እንደነበረ አይጠረጠርም!" የሚለውን ሃይማኖታዊ ሥነ ምግባር ከማጽናት በቀር፡ ሊያናውጸው የሚችል አይደለም:: በዚህ ረገድ፡ "ፀረ ማርያሞች" የተባሉት፡ የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት እንኳ፡ በዚሁ ሥርዓተ መለኮት በማመን፡ የወንጌላዊዉን የአጠራር ቃል፡ "እናቴ ሆይ!" እያሉ፡ አስተካክለው መተረጐማቸው ይታወቃል::

የኢትዮጵያ ሊቃውንት ጉባዔ ሰብሳቢ፡ እነአለቃ አያሌው ግን፡ የአምላክን እናት ብቻ ሳይኾን፡ በራሱ በመለኮት ላይ እንደመዘበት በሚያስቆጥር የሃይማኖት አቋማቸው፡ ያንኑ በዮሐንስ ወንጌል የተጻፈውን አመልካች ቃል፡ "ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ እናቱን፡ ቅድስት ድንግል ማርያምን፡ 'ሴትዮ! አንቺ ሴት!' ብሎ ነው የጠራት" እያሉ፡ በታላቅ ድፍረትና ንቀት ተርጉመውታል::

መቼም: ምክንያት ማቅረብ: ለሊቃውንቱ ቀርቶ: ለማንም ሰው አይገድድምና: "እንዲህ ብለን የተረጐምነው: የግእዙ ቃል: 'ብእሲቶ' ስለሚል ነው!" ይሉ ይኾናል:: እንዲህ ከተባለ: ከዚህ የሚከተለው መጠይቃዊ ምላሽ: ይሰጣቸዋል:- ታዲያ: ለምንድር ነው: በማቴዎስ ወንጌል: "ብእሲ ወብእሲት" የሚለው የግእዙ ቃል: "ባልና ሚስት" ተብሎ የተተረጐመው? ወይም: እንደዛሬው: የጨዋ አነጋገር: "ባለቤትዋና ባለቤቱ" እየተባለ የሚተረጐመው? ለምን፡ ቃል በቃል: "ወንድና ሴት" ተብሎ አልተተረጐመም? ወይም: በግእዙ: "ብእሲተ ጸጢፋር" የሚለው: ለምን: በትክክለኛው አተረጓጐም: "የጸጢፋር ሚስት" ተባለ? ወይም: በሌላ አነጋገር: "የጸጢፋር ባለቤት" ይባላል? ለምን: በቀጥታ: ቃል በቃል: "የጸጢፋር ሴት" ተብሎ አልተተረጐመም? "ብእሲሃ" የሚለውስ: ለምን: "ወንዷ" ተብሎ: አይተረጐምም? ለምንድር ነው: ተቃንቶ: "ባሏ" ወይም "ባለቤቷ" ተብሎ የሚተረጐመው?

ይህ: ለማንም እሩቅ ብእሲ፥ ለማንም ተራ ወንድና ሴት የሚሰጠው: የቃልና የአክብሮት ትርጉም: እንዴት: ለኢየሱስ ክርስቶስና "የአምላክ እናት" ለተባለችው: ድንግል ማርያም ይነፈጋቸዋል? ለዚያ ኹሉ የትድግናና የቸርነት ሥራቸው ውለታ: ይህ እንኳ ይብዛባቸው? ያውም: "ኢትዮጵያውያን ነን" ከሚሉ: ሊቃውንት?! ይህ ድርጊት: ጌታ: በመስቀል ላይ ተሰቅሎ: *"ጸማእኩ! ውኃ ጠማኝ!"* ባለ ጊዜ: ልቦናቸውንና ግብራቸውን ስላወቀ: "እምቢ! አልጠጣውም!" ብሎ: በዝምታ: ፊቱን ቀለስ በማድረግ: የመለሰውን መራራ ሐሞትን ካቀረቡለት: ከአይሁድ የጭካኔ ድርጊት ተለይቶ አይታይም!

## ስለሰበካ ጉባኤ:
## የማውቀውን ለመመስከር::

ሌላው: የአለቃ አያሌውን እውነተኛ ማንነት: ቢያንስ ቢያንስ ለራሴ ለማወቅ የተረዳሁበት ድርጊት አለ፤ በዚህም: ነገሩን የሚያውቁት ኹሉ: ከአንደበታቸው አውጥተው ሊናገሩት ባይፈልጉ እንኳ: በየሕሊናቸው ባሳደሩት ትዝብት ይተባበሩኛል ብዬ አምናለሁ፤ ይህም: ስለሰበካ ጉባኤ መቋቋም: ከውጥኑ ጀምሮ እስከፍጻሜው ድረስ የኾነውን ይመለከታል:: እርሳቸውና እኔ: በቤተ ክህነት ውስጥ አብረን የሠራን በመኾናችን: በሥራና በአገልግሎት ደረጃ ብቻ በቅርብ እንተዋወቅ ነበረ::

እንደማናቸውም የእግዚአብሔር ሥራ: የሰበካ ጉባኤንም ነገር: "ሰው: ራሱ: ከራሱ አንቅቶ: ራሱ ሠራው!" ሊባል የማይቻል፥ የማይገባም መኾኑን: የእግዚአብሔር ወገን የኾነ: የእውነት ሰው ኹሉ የሚያውቀው ነው:: በዚህ መሠረት: መንፈስ ቅዱስ: ይህን የሰበካ ጉባኤ ጽንሰ ሐሳብ: በማን አእምሮ ውስጥ አሳድሮ፥ ረቂቁን አስጽፎና በሚመለከተው የቤተ ክህነት ጉባኤ ላይ ቀርቦ ከተፈቀደ በኋላ: ተቋቁሞ: ለፍሬ እንዲበቃ ያደረገው: በማን መሣሪያነት እንደኾነ: ራሳቸውም ያውቁ እንደነበረ: ራሳቸው: በግዘፍ የፈጸሟቸውን ድርጊቶች: እዚህ ላይ መጥቀሱ ይበቃል::

ይኸውም: ይህንኑ የሰበካ ጉባኤ: በጊዜው ለማቋቋም ይቻል ዘንድ: በቅድሚያ: ስለዐዋጁና ስለአፈጻጸሙ: አንቀጽ በአንቀጽ በመተንተን: ለቤተ ሕዝቡ ማስረዳት አስፈላጊ በመኾኑ: በዚህ ረገድ: በጽሑፍ ያዘጋጀሁትን ዝርዝር ማብራሪያ: በኢትዮጵያ ነፋስ ድምፅ (Radio ራዲዮ) ጣቢያ አማካይነት: በየዕለቱ ጠዋት አሰማ እንደነበረ ማወቃቸው: አንዱ ነው::

# ኢትዮጵያ:

ሌላው ደግሞ: ያን ተግባር አጠናቅቄ: በአዲስ አበባ አድባራትና በየክፍላተ ሀገሩ በምዘዋወርበት: በ፲፱፻፷፭ ዓ. ም.: ተራቸው ኾኖ በነበረው: በአንደኛው ሰንበተ ክርስቲያን: በዚያን ጊዜ: እርሳቸው: የደብሩ አስተዳዳሪ በነበሩበት: በደብረ አሚን: ቅዱስ ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን: እኔ ራሴ ተገኝቼ: በተካኼደው ሥርዓት ላይ: ራሳቸው በይፋ ያሰሙት የምስክርነት ቃልና የፈጸሙት ምግባር ነው::

በዚያ ሥርዓት ላይ: እኔ: ስለሰበካው ጉባኤ: ለቤተ ሕዝቡ የማደርሰውን መልእክት አድርሼ ከጨረስሁ በኋላ: እርሳቸው ተነሥተው: ስለሰበካው ጉባኤ ውጥንና ከዚያ ደረጃ መድረስ: ምክንያቱ እኔ መኾኔን በማብራራት: ራሳቸው የሰጡት የምስክርነት ቃል: ቢያንስ ቢያንስ: በሕይወተ ሥጋ እስካለን ድረስ: ምንጊዜም የሚዘነጋ አይደለም:: ለዚያ ትምህርታዊ ስብከታቸው ማጠቃለያና ማሠሪያ ያደረጉትም: "ቃለ ዐዋዲ እንዘ ይሰብክ በገዳም": ማለትም: "በምድረ በዳ የሚጮህ: የአዋጅ ነጋሪ" የተባለለትን መጥምቁ ዮሐንስን በመጥቀስና ማንም ሊመስለው የማይገባ ሲኾን: እኔን: እንደእርሱ በመቁጠር÷ እንዲሁም: ተልእኮዬን: የሰበካው ጉባኤ ደንብ ታትሞ ከወጣበት: "ቃለ ዐዋዲ" ተብሎ ከተሠየመው: ጦማረ ሕዝብ ጋር በማመሳሰል: የተናገሩት ቃል ነበር:: ለዚያም ቃላቸው ማረጋገጫ ይኾን ዘንድ: በደብሩ ካህናትና ምእመናን÷ በራሳቸውም ስም ያበረከቱኝ: የ"ቃለ ዐዋዲው" ምሳሌና የራሷም መጠሪያ: በግእዝ "ቃለ ዐዋዲ" የኾነችው: ቃጭል: ወይም መረዋ: ዛሬ ድረስ: ለምስክርነትና ለመታሰቢያነት: በእኔ ዘንድ ትገኛለች::

ታዲያ÷ የአባ ቴዎፍሎስ: አፅም: ወደቤተ ክርስቲያን መቃብር እንዲገባ በተደረገበት ቀን: የተለመደ የውደሳ ስብከታቸውን ባሰሙበት ጊዜ: ስለሰበካ ጉባኤ አቋቋም: ጠቅሰው ሲናገሩ: "የሰበካ ጉባኤን ደንብ ያረቀቁም÷ በመላ ኢትዮጵያም ተዘዋውረው በሥራ ላይ ያዋሉ: አቡነ ቴዎፍሎስ ናቸው!" ማለታቸው ምን ማለት ነው? ያን: እውነተኛውን የቀድሞ ቃላቸውን ማጠፍስ ለምን አስፈለገ? የእግዚአብሔርንስ ሥራ ለሰው መስጠት ይገባል ወይ? "ይህ የእግዚአብሔር ሥራ: በሥልጣን ዘመናቸው ተደረገ!" ቢሉ እንኳ ያስኬዳል፤ ተገቢም ነው!

ደግሞስ: ሌላውን ኹሉ: "በመስማት አረጋገጥኩ!" ሊሉ ይችሉ ይኾናል፤ ነገር ግን: በተለይ: "ደንቡን ያረቀቁት እርሳቸው ናቸው" ያሉትን: የምስክርነት ቃላቸውን ለመስጠት: ለእርሳቸው: ማየት ለተሣናቸው ሰው: እንደምን ይቻላቸዋል? "ማን ያርዳ? የቀበር! ማን ይመስክር የነበር!" በሚለው ምሳሌ መሠረት: ይህን ድርጊት: በዐይነ ሥውርነታቸው እንዴት ሊያረጋግጡት ነው? እርሳቸው ይህን ቃል ሲናገሩ: እኔ በሕይወት ቆሜ: እየተንቀሳቀስሁ መኾኔን÷ ሌሎችም: እውነቱን የሚያውቁ: በሕይወተ ሥጋ እየኖሩ መኾናቸውን አላወቁትም ልበልን? እነርሱስ የቱን ያህል ይታዘቧቸው?! ወይም: "አልሞትኩም ብዬ አልዋሽም!" እንደተባለው: እኔ ገና በሕይወተ ሥጋ ያለሁ ብኾንም: ዘመኑ ባመጣው ክህደትና ዓመፅ ምክንያት: "እንደሞትኩ ቆጥረውኛል!" ማለት ነውን? ሰዎች ዝም ቢሉስ: በጽሑፍ ተዘጋጅቶና ተራብቶ: በአስፈጻሚዎቹ እጅና በመዝገብ ቤት የሚገኘው: የቃለ አዋዲው ማብራሪያ ጥራዝ: በምስክርነት አይጮህምን? እኔም: ይህን ተናገሩ የተባለውን ቃላቸውን: ቀደም አድርጌ ብሰማውም: ለማመን አቅቶኝ ቆይቼ ነበር፤ ኋላ ግን: በጦማረ ሕዝብ: በጽሑፍ ታትሞ ወጥቶ ሳነብበው: የሰማሁት: እውነት መኾኑን አረጋገጥሁ::

ከላይ እንደጠቀስኩት፡ መንፈስ ቅዱስ፡ ይህን የሰበካ ጉባዔ ጉዳይ፡ ከጽንሰ ሐሳቡ አንሥቶ፡ ደንቡንና ማብራሪያውን፡ በጽሑፍ አርቅቆ እስከመቅረጽ፥ ከዚያም፡ አስፈቅዶ፡ በአዋጅ እስከማውጣትና በሥራ ላይ እስከማዋል ያደረሰው፡ እኔን፡ ትሑት አገልጋዩን መሣሪያ አድርጎ መኾኑን፡ እርሳቸው ወይም ሌሎች፡ እርሳቸውን የመሰሉት ሊክዱት ቢሞክሩም፡ የእግዚአብሔር እውነት የፈጸመችውን፡ ይህን የተልእኮ ግዳጅ፡ እኔ፡ እንዴት ልክደው ይቻለኛል? አይቻለኝም። ይህን የመሰለው ሐሰት፡ በይፋና በድፍረት፡ እንዲህ መነገሩንና መጻፉን እየሰማሁና እያወቅሁ፡ እኔም በበኩሌ፡ ይህን የምስክርነት ቃሌን ሳልሰጥ ብቀር፡ ከሕሊናዬ በላይ፡ በፈጣሪዬ ዘንድ አያስጠይቀኝምን?

ይህ የአለቃ አያሌው ድርጊት፡ የእርሳቸውን እውነተኛ ማንነት፡ ቢያንስ ቢያንስ፡ ለእኔ ለራሴ ሊያሳውቀኝ ችሏል። ስለዚህ፡ ከእርሳቸው፡ ያውም፡ የቤተ ክህነት የሊቃውንት ጉባዔ ሰብሳቢ ከተባሉት አፍ፡ በይፋና በድፍረት ሲነገር የተሰማው፡ ይህ ውሸት፡ እውነቱን በማውቀው፡ በእኔ፡ በአንድ ሰው ዘንድ ብቻ ሳይኾን፡ የራሳቸውን ሕሊና ጨምሮ፡ "ለዚች እውነት፡ ምስክሮች ናቸው" በምላቸው፡ በሕይወተ ሥጋና በሕይወተ ነፍስ በሚገኙት ሰዎች ዘንድ ሳይቀር፡ የዛሬዋን ቤተ ክህነት፡ ከነሰዎቿ፡ በአሳዛኝ ግምት ላይ እንደጣላት ልሸሽገው ያዳግተኛል።

ዘመኑ፡ የእርሱ በመኾኑ ብቻ፡ የዲያብሎስ ሐሰት፡ በእግዚአብሔር እውነት ላይ ሠልጥኖ፡ ሊያሸንፍ ከቶ አይችልም። የተባለው፡*"ወጽድቁሰ ለእግዚአብሔር ይሄሉ ለዓለም"* ማለትም፡ "የእግዚአብሔር እውነት ለዘለዓለም ትኖራለች" ነው። የሚፈራርሰውና ለዘለዓለም የሚደመሰሰው፡ የዲያብሎስ ሐሰት እንጂ፡ የእግዚአብሔር እውነት አይደለችም። ይህና ሌላው ኹሉ፡ የሰዎች ሐሰት ተጠቃልሎ፡ በእግዚአብሔር እውነት ላይ፡ ምንም ዓይነት ኢምንትነት ሊኖረው ከቶ አይታሰብም። ለኹሉ፡ ዋጋውን ከሚከፍለውና ከመለኮታዊ ዳኝነቱ፡ ማንም ማምለጥ ከማይቻለው፡ ኃያል አምላክ፡ ኹላችንም፡ ትክክለኛ ፍርዱን እንጠብቃለን።

እንግዴህ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት የኾነችውን፡ ኢትዮጵያን፡ በአሁኑ ጊዜ፡ በአጠቃላይ፡ ካለችበት ውድቀት ያደረሳት፡ በቤተ ምልክናውና በቤተ ሕዝቡ በኩል የተፈጸመው፡ የክህደትና የዓመፅ ድርጊት ብቻ ሳይኾን፡ በይበልጥ፡ በቤተ ክህነቱም በኩል፡ እስካሁን እየተካኼደ ካለው ጋር፡ ይህም፡ የጳጳሳቱንና የአለቃ አያሌውን የመሰለው አድራጎት ተዳምሮ መኾኑን መገንዘብ፡ ለማንኛውም አስተዋይ ተመልካች የሚያዳግተው አይመስለኝም።

## ለእሥር ቤቱ ገጸ በረከት፡ የተሰጠው ምላሽ።

ከዛሬው የክህደትና የዓመፅ ዘመን የተነሣ የተጋለጠውን፡ የአለቃ አያሌውን እውነተኛ ማንነት ያወቅሁበት፡ ሌላው አጋጣሚ ደግሞ አለ፤ ይህም፡ ባጭሩ እንዲህ ነበር። በ፲፱፻፸፬ ዓ. ም. ከደርግ እሥር ቤት እንደወጣሁ፡ በዘመኑ፡ የቤተ ክህነቱ እጨጌ የነበሩት፡ አባ ተክለ ሃይማኖት፡ በዚያን ጊዜ፡ የቤተ ክህነቱ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ የነበሩትን፡ ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛውን፡ እመኖሪያ ቤቴ ድረስ ልከው፡ ሊረዱኝ የሚፈልጉ መኾናቸውን በመግለጽ፡ በእኔ በኩል የምፈልገው ነገር እንዳለ፡ ፍላጎቴን እንድገልጽላቸው ጠየቁኝ።

## ኢትዮጵያ፡

እኔም፡ "በደርግ እሥር ቤት ሣለሁ፡ ለዛሬው የኢትዮጵያ ትውልድ፡ በተለይም፡ አእምሮው፡ በዘመናዊው፡ የምዕራባውያን ሥጋዊ እውቀት ለታነፀው፡ ለወጣቱ ወገን፡ ለሴቶቹም፥ ለወንዶቹም ይጠቅማል፥ ያስፈልጋልም" ብዬ "አዳምና ሔዋን በኢትዮጵያ" በሚል አጠቃላይ ርእስ፡ "ኢትዮጵያዊው፥ በእውነት ፍለጋ! በእውቀት ፍለጋ! በጦቢያ ፍለጋ!" በሚሉ ንዑሳን አርእስት፡ ያዘጋጀሁት፡ ሦስት ጥራዞችን የያዘ መጽሐፍ ስላለ፡ ታትሞ ቢሠራጭ፡ ቤተ ክህነት፡ በአሁኑ ጊዜ ያለባትን ኀጻጅ፡ በመጠኑም ቢኾን ለመወጣት ይረዳታል! እኔም፡ በዓቅሜ ላበረክተው የምችለው ድርሻ ይህ ነው!" ብዬ መልስ ሰጠሁ። እጨጌውም፡ መጽሐፉ እንዲታተም ፈቅደው፡ በቅድሚያ ግን፡ በአግባቡ ታይቶ፡ አስተያየት እንዲቀርብበት፡ በጠቅላይ ሥራ አስኪሃጁ እጅ፡ እኔም ባለሁበት፡ የሊቃውንት ጉባዔ ሰብሳቢ፡ አለቃ አያሌው፡ የመጽሐፉን ረቂቅ ተረከቡ።

በዚያን ቀን፡ በእሥር ቤት ያልጠየቁኝ፥ ከደርግ እሥር ቤት ስወጣም፡ "እንኳን እግዚአብሔር አስፈታህ!" ያላሉኝ አለቃ አያሌው፡ "ብታሠር ኀበኛችሁኝ!" የሚለውን የጌታ ቃል፡ መነሻ በማድረግ፡ "ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በእሥር ቤቱ ውስጥ፡ አብሮ እየኖረ፡ በመንፈስ ቅዱስ ያዘጋጀው ድርሰት ነው" በሚል ቃል፡ የተለመደ ከንቱ ውዳሴያቸውን በማሰማት፡ በጠቅላይ ሥራ አስኪያሃጁና በሊቃውንቱ ጉባዔ አባሎች ፊት፡ የአቀባበል ንግግር ካደረጉልኝ በኋላ፥ እኔም፡ ለማናቸውም ደራሲ እንደሚደረገው፡ "ለአንዳንድ ማብራሪያ፡ ወይም ጥያቄ ሳስፈልግ፡ ምንጊዜም ይመቸኛልና፡ ብትጠሩኝ ልመጣ ይቻለኛል" ብዬ መልስ ከሰጠሁ በኋላ ተሰነባበትን። ለብዙ ወራት፡ ጥሪያቸውን እየተጠባበቅሁ ሣለሁ፡ አንዳችም ጥሪ ሳይደርሰኝ፥ መጽሐፉ፡ ያለአንዳች መሸኛ ደብዳቤና አስተያየት፡ ሌጣውን ተመለሰልኝ።

እንግዴህ፡ የቤተ ክህነት፡ የሊቃውንት ጉባዔ፡ በዚህ፡ በሌላኛው የዘዴ አሠራሩ፡ ያስመሰከረው ነገር ቢኖር፡ ራሱ፡ ጉባዔው፡ የከሃዲውና የዓመፀኛው ደርግ፥ የኢትዮጵያ ጠላቶችና የዲያብሎስ አገልጋይ መኾኑን ነው። ይህም፡ መጽሐፉ፡ በእግዚአብሔር እውነት ላይ ተመሥርቶ፡ ቅዱሳት መጻሕፍትንና ዘመናዊዉን ሥነ እውቀት፡ ዋቢ በማድረግ፡ የኢትዮጵያን ማንነት በግልጽ እያብራራ፡ ለእነዚህ ባላጋራዎቿ ተገቢውን ምላሽ የሚሰጥ ሲኾን፥ እኔም፡ በዚያን ጊዜ፡ እሥሮ የፈታኝን ደርግን ኾነ ሌሎቹን ተቃዋሚ ኃይላት ሳልፈራ፡ ያን የመሰለ ድርሰት፡ እንደዚያ በይፋ ማቅረቤ የታወቀ ሲኾን፡ "ለኢትዮጵያ፡ ሽንጡን ገትሮና እስከሞት ድረስ ቆሞ ይከራከርላታል!" ተብሎ የሚጠበቀው፡ የቤተ ክህነት፡ የሊቃውንት ጉባዔ፡ ይህን መጽሐፍ፡ በዚህ መልክ ተቃውሞ መመለሱ፡ እርሱ ከሚወክላቸው እጨጌና ጳጳሳት ጋር፡ ኢትዮጵያን ሊያጠፏት ለተነሡት ጠላቶቿ፡ ጥሩ መሣሪያ ኾኖ መገኘቱን፡ ቢያንስ ቢያንስ ለእኔ አረጋግጦልኛል። እነዚያም፡ የእሥር ቤት ፍሬዎች የኾኑት መጻሕፍት፡ እግዚአብሔር፡ ፈቃዱ ኾኖ፡ ለኅትመት በሚያበቃቸው ጊዜ፡ አንባቢዎች ተመልክተው፡ "የየራሳቸውን የአስተያየት ብያኔ ይሰጡበታል" ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ።

እውነተኛው የመንፈስ ቅዱስ አሠራርማ: በኒቅያ፥ በቁስጥንጥንያና በኤፌሶን ጉባዔያት ላይ እንደታየው፥ እንደተደረገውም: ሃይማኖትን የሚነካ: አንዳንድ ነቀፅ፥ ሕፀፅ ወይም ኑፋቄ የሚገኝበት ትምህርት: ወይም ድርሰት ሲሰማና ሲነበብ: ባለቤቱ: በጉባዔ ላይ ተጠርቶና ቀርቦ: በግልጽ ተነጋግረው በስምምነት በመወሰን: ፍሬያማ ውጤት ይገኝበታል:: የክፋትና የኃጢአት፥ የክህደትና የዓመፅ አበጋዝ የኾነው የዲያብሎስ አገልጋዮች ግን: ሥራቸውና የሚሠሩበት ዘዴያቸው፥ ነገራቸውም ኹሉ: ወደብርሃን እንዲወጣ አይፈልጉም:: ይህማ የኾነ እንደኾነ: ጨለማ: ብርሃን ሲመጣበት: እንዳልነበረ ኾኖ እንደሚጠፋ ኹሉ: የሐሰተኞችም ሐሰታቸው: ከነአበጋዙ: ድራሹ እንደሚጠፋ ያውቁታልና: የእውነት ነገር: ተድበስብሶና በዝምታ ብቻ ተረሳስቶ እንዲረሳ ያደርጉታል::

ይህን ለመሰለው የዓለሙ ኹኔታ: ከዚህ በታች የተጠቀሰው: የጌታ ቃል: በቂ መመሪያችን ኾኖ: ተከታዮቹን ያጽናናናል:- *"ብርሃን ወደዓለም ስለመጣ: ሰዎችም ሥራቸው ክፉ ነበርና: ከብርሃን ይልቅ: ጨለማን ስለወደዱ: ፍርዱ ይህ ነው:: ክፉ የሚያደርግ ኹሉ: ብርሃንን ይጠላልና፤ ሥራውም እንዳይገለጥ: ወደብርሃን አይመጣም፤ እውነትን የሚያደርግ ግን: ሥራው: በእግዚአብሔር ተደርጎ እንደኾነ ይገለጥ ዘንድ ወደብርሃን ይመጣል::"* [፲፱፩]

## ኢትዮጵያ:
## በአጠቃላይ: ትውልዷን
## ስትፋረድ!

"ሀገረ እግዚአብሔር"፥ "የክርስትና ደሴት"፥ "ብሔረ አግዓዚት" በምትባለው አገር: በኢትዮጵያ: በተለይ በአዲስ አበባና በሌሎች ከተሞች ውስጥ: በየገጠሩ ሳይቀር: በአሁኑ ጊዜ: በመዓልት ኾነ: በሌሊት ምን እየተካኼደ ነው? በአገሪቱ: ዜና ማሠራጫዎችና የሕዝብ መገናኛዎች: የባዕዳኑ፥ የዓለማውያኑና የሥጋውያኑ ከኾነው በቀር: የእግዚአብሔር: ስሙ እንኳን ይጠራባቸዋልን? በአረማውያንና በአሕዛብ ዘንድ: "ይፈጸሙ ነበር" ሲባሉ የምንሰማቸውና አሁንም: በባዕዳን አህጉር ውስጥ: በይፋ ሳይቀር የሚፈጸሙት: ባዕድ አምልኮን፥ "ደነሰ": "ኃጢአት ሠራ" በሚለው ግልጽ ቃል: ያለማቋረጥ የሚቀልጠውን: የዘፈኑንና የዳንሱን ድብልቅልቅ፥ የዝሙትና የኃጢአት ተግባራትን፥ ግብረ ሰዶምንና የእርቃን ሥጋ ጭፈራን ሳይቀር: የመሳሰሉት: ለወንጀል ምንጭ፥ ለቀሣፊ ደዌያትም መንሥዔ የኾኑት: የ"አስረሽ-ምቺው" ዝግጅቶችና ድርጅቶች: በኅብረተሰቡ ዘንድ ሰፍነው: በይፋ እንዲካኼዱ የሚደረግበት ይዞታ: ሊወገድ ቀርቶ: ወሰንና ገደብ እንኳ የተደረገለት መስሎ አይታይም::

## የማየ አይኑ (የጥፋቱ ውሃ) ማዕበል:
## ጨርሶ እንዳያስጥም::

ይህ ኹሉ ድርጊት: የቅዱሱ ኪዳን ማኅደር በኾነችው: በኢትዮጵያ ምድር ላይ: Democracy "ዲሞክራሲ" በሚባለው "ሕዝባዊ አገዛዝ" ስምና ሽፋን: ያለኃፍረት ሲፈጸምና መረን ተለቅቆ ሲካኼድ: የቤተ ክህነቱ መሪዎች: እጨጌውና ጳጳሳቱ: ምን እያደረጉ ነው?

እነዚህን የከፋትና የጥፋት ኃይሳት፡ በረቂቅ ብቻ ሳይኾን፡ በገሃድም፡ በይፋ እየተዋጓቸው ነውን? ወይስ ሥጋዊዉን ሥልጣንና ኃይል ፈርተው፡ በኖሩበት ዝምታ እንደቀጠሉ ናቸው? ወይስ ኃይሳቱ ያስነሡት የማየ አይኅ (የጥፋት ውሃ) ማዕበል፡ ቤተ ሕዝቡን አጥለቅልቆ እስኪያሰጥማቸው ድረስ፡ ዝም ብለው ቆመው፡ እየተመለከቱ ናቸው? ወይስ ማዕበሉን እንዲቋቋም፡ ያሳነጹሳቸው መከላከያ ግድብ አለ? ያም ካልኾነ፡ ራሳቸው፡ ቤተ ሕዝቡና የቤተ ክህነቱ ወገኖች የኾኑት ካህናቱ፡ በየግላቸውም ኾነ፡ ወይም፡ በቡድን እየኾኑ፡ የእነዚያን ኃይሳት ወረራ፡ ተከላክለው ለመግታት፥ ቢቻልም፡ መክተው ለማቆም፥ አለዚያም፡ አጥቅተው ለመመለስ እንዲችሉ ተደርጓል ወይ? በዚህ የሰልፍ አግጣጫ ያለውንም፡ የደፈጣ ውጊያና ተጋድሎ ለማካኼድ በሚያበቃቸው፡ በሃይማኖታዊውና በመንፈሳዊው የጦር ዕቃ ትጥቅ ተሟልተው ተደራጅተዋል ወይ? ትጥቁ ተሰጥቷቸው ከኾነስ፡ የጦር ዕቃውን፡ እንዴት ሊሠሩበትና ሊጠቀሙበት እንደሚችሉ የሚመራቸውን፡ አስፈላጊውን ትምህርትና ሥልጠና፡ በሚገባው መጠንና ብስለት አግኝተዋልን?

እነዚህን የመሰሉ፡ ብዙ ጥያቄዎች ሊኖሩ ይችላሉ፤ መዘርዘሩ፡ ይህን ያህል አስፈላጊ አይመስልም። ለእነዚህና እነርሱን ለመሰሉት ጥያቄዎች፡ መልስ ለመስጠት፡ ከቤተ ክህነቱና ከቤተ ምልክናው ይልቅ፡ በይበልጥ፡ ቤተ ሕዝቡ፡ ብቁነትና ግቡነት ይኖረዋልና፡ መልሱ በምግባር የሚጠበቀው በዚያ በኩል መኾኑ ሊታወቅ ይገባል።

## ለመክሊቶቹ ባለቤት፡ ስለምንሰጠው ምላሽ፡ ተዘጋጅተናል?

በአሁኑ ጊዜ፡ ቀደም ብለው ከተሠሩት የቤተ ክህነት ሕንፃዎችና ተቋሞች፥ በተለይም፡ የሰበካ ጉባዔ ህልውና ባስገኛቸው የገቢ ምንጮች ምክንያት፡ ሥጋዊ ኑሮአቸው፡ ምናልባት የተመቻቸላቸው መስሏቸው የሚዝናኑ፡ ጳጳሳት እንዳሉ፡ ለእነርሱና በየሀገረ ስብከቱ፥ በየደረጃውም ላሉት፡ ለቤተ ክህነቱ፡ መምሪያ ኃላፊዎችና ሠራተኞች፥ ለየአድባራቱ አለቆች፥ ለየገዳማቱ አበምኔቶችና እመምኔቶች፥ ለየገጠሩም ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪዎች፥ እንዲሁም፡ ቀሳውስትንና ዲያቆናትን፥ መነኰሳትንና መነኰሳይያትን፥ መምህራንንና ማኅሌታውያንን፥ የሰበካ ጉባዔዎችን የሥራ አባላት፡ ወንዶቹንና ሴቶቹን፥ አዛውንቱንና ወጣቱን ለሚያጠቃልለው፡ ለመላው የካህናትና የምእመናን ማኅበር፡ ይህን እላለሁ!

ባለቤቱ፡ ሊቀ ካህናት ወንጌሠ ነገሥት፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከንግሥት እናቱ፡ ቅድስት ድንግል ማርያም ጋር፡ ለጥያቄና ለፍርድ የሚመጣበት፡ የመጨረሻ ጊዜ መኖሩን፥ በዚያን ጊዜም፡ እኛ፡ የቃል ኪዳን አገልጋዮቹ ጭምር፡ እያንዳንዳችን፡ በነፍስ ወከፍ፡ በፊቱ ቀርበን መጠየቃችን እንደማይቀር፡ ኹላችንም፡ በሃይማኖት አውቀነውና ተቀብለነው፡ ለሌሎችም የምናስተምረው እውነታ ነው።

*ይህንንም: ,ዩ: በሦስት ደረጃዎች ለተመደቡት አገልጋይዎቹ: እንደየዓቅማቸው: አምስት፥ ኹለትና አንድ መክሊቶችን ሰጥቷቸው: ወደሩቅ አገር ከኼደ በኋላ: ኖሮ ኖሮ: ተመልሶ መጥቶ: እያንዳንዳቸውን እየጠራ: በዚ,ዩ: በየግላቸው በተቀበሉት የአደራ ገንዘብ: ምን ሠርተው፥ ስንት እንዳተረፉ ተቆጣጥሮ: እንደየሥራ ፍሬአቸው: ዋጋቸውን እንደከፈላቸው ጌታ: እርሱም: ሊቀበሉት ታድመው: ሲጠባበቁት በቆዩትና በዝግጅታቸው: አምስቱ: 'ልባሞች'፥ አምስቱ ደግሞ: 'ሰነፎች' በተባሉት: በአሥሩ ደናግል ዘንድ: በሌሊት: ድንገት እንደደረሰው[፻፵፪] ሙሽራ: እንደሚመጣ: በተወልን መለኮታዊ ቃሉ: አበክሮ ነግሮናል።*

እንግዲህ: እውነታው ይህ ከኾነ: በሥጋና በነፍስ፥ በመንፈስም ጭምር: ማንም ሊያመልጥባት ከማይቻለው: ከዚያች: የጥያቄና የፍርድ ቀን በፊት: እያንዳንዳችን: የሚገባንን ፈጽመንና እርሱን ለመቀበል ተዘጋጅተን መገኘት ይኖርብናል። ይህም ሲኾን: ቀደም ብሎ: በተለይም: ከደርግ ወዲህ: በአጼውና በእጨጌው፥ በቢትወደዱና በጸሓፊ ትእዛዙ፥ በቀሩትም: የቤተ ሕዝቡ፥ የቤተ ምልክናውና የቤተ ክህነቱ ባለሥልጣኖች ላይ: ይኸው እስካሁን ደርሶ እንደታየውና እንደሚታየው: እያንዳንዳችን: ወይም ገሚሶቻችን: ወይም ኹላችን: ድንገት: አንድ ቀን: በአካለ ሥጋ: በቤተ ሕዝቡ ዘንድ: ተጠርተን: "ይህ ኹሉ ሲኾን: በኃላፊነታችሁ ምን አደረጋችሁ?" ተብለን ከመጠየቅ የማንድን መኾናችንን ልንዘነጋው አይገባም።

እኔም: በዚህና በቀሩት መጻሕፍቴ ውስጥ የተገለጹትን መልእክታት ያቀረብኩት: ቀደም አድርጌ: ደጋግሜ እንዳስገነዘብሁት: ለሌላ ሳይኾን: ከላይ በተጠቀሰው: መለኮታዊ ቃለ ምሳሌ መሠረት: ለእኔም: በዓቅሜ የተሰጡኝን መክሊቶች: "ሠራህባቸውን? ምን ዓይነት ሥራ? ስንት አተረፍክ?" ብለው ለሚጠይቁኝ: ለዚያ ዘለዓለማዊ ጌታና ለዚያች ንግሥት እናቱ: የምሰጠው በቂ መልስ፥ የማስረክበውም የሥራ ፍሬ እንደላጣ ብዬ መኾኑ: በኹሉ ዘንድ እንዲታወቅልኝ "አደራ" እላለሁ።

ያች: በብሉዩ ኪዳን: ጥንታዊቷና አረጋዊቷ የተባለችው፥ በአዲሱ ኪዳንም: አዲሲቱና ዘመናዊቱ የምትባለው ኢትዮጵያ: ዛሬ: ከሕዝቧ ጋር: የምትገኝበት ኹኔታዋ: እንግዲህ: ይህ ነው! ደጃፉ ተበርግዶ: ያለገደብ: እንደጎርፍ እንዲገባና ኢትዮጵያዊዉን ባለቤት: መብቱን ገፍፎ እንዲያጥለቀልቀው: የተፈቀደለት: የባዕዳኑ ሃይማኖትና ምግባር: ሥርዓትና ባህል: በአገራችን: የቱን ያህል እንደሰፈነና እንደሠለጠነ: የዘመኑም ትውልድ: ከአጠቃላይ ድክመቱ የተነሣ: ከራሱ አልፎ: እርሷንም: እንዴት አድርጎ: ለጥቃት እንዳጋለጣት: ከላይ: በምሳሌነት የተጠቃቀሱት: አንዳንድ ኹኔታዎች በሚበቃ ያስረዱ ይመስለኛል። ይህ አሳዛኝና አሳሳቢ ኹኔታም: በቤተ ክህነቱ አካባቢና በየአገር ቤቱ ሳይቀር: በከፍተኛ ፍጥነት እየተስፋፋና እየተባባሰ በመኼድ ላይ ስለሚገኝ: ነገሩን እጅግ አሳሳቢና አጣዳፊ አድርጎታል።

## ጥቃታቸውን የሚወጡትን፡ ጉበዞቹን ሕዝቦችማ አየናቸው! እኛሳ!?

ኅበዞቹማ! ማለትም፡ ስማቸው፡ በአርአያነት፡ ቀደም ብሎ የተጠቀሰው፡ የአንዳንድ የኅረቤትና የሩቅ አገሮች ሕዝቦች፡ ሃይማኖታቸውንና ምግባራቸውን፥ ቋንቋቸውንና ሥርዓታቸውን፥ አለባበሳቸውንና ሌላውን ባህላቸውን ኹሉ፡ እንዴት አድርገው ተከላክለውና ተጠባብቀው፥ አንከባክበውም እንዳቆዩ፥ ዛሬም እየኖሩበት እንደሚገኙ፡ ከላይ በተሰጠው ሐተታ ላይ ተመልክተነዋል።

እኛ ግን፡ በዚህ ረገድ፡ ከምን ዓይነቱ ውድቀት ላይ እንደደረስን፥ ወደፊትም፡ ወደየት የውርደት አግጣጫ እያመራን እንደኾን፡ በቀላሉ ልንረዳ እንደቻልን እገምታለሁ። ልንጠብቅ የሚገባን እኮ፡ የምግብና የመጠጥ ባህላችንን ብቻ ሳይኾን፡ ሌሎቹንም መልካሞቹን ኹሉ መኾን እንዳለበት፡ ኢትዮጵያዊነታችን በየጊዜው ያሳስበናል።

በዚህ በኩል፡ እንደቀድሞው ኹሉ፡ ዛሬም፡ ታላቁን የኃላፊነት ድርሻቸውን፡ ከወንዶች በበለጠ እንጂ ባላነሰ መጠን ሊወጡ የሚችሉት፡ ሴቶች ልጆቻችን፥ እህቶቻችንና እናቶቻችን ናቸው። ለጥፋቱም ኾነ ለልማቱ፡ ቀደምት መሣሪያዎች ኾነው የተገኙት፡ እነርሱ እንደኾኑ፡ በመጀመሪያዎቹ አጥፊዎች፡ በአዳምና በሔዋን፥ እንዲሁም፡ በመጨረሻዎቹ አልሚዎች፡ በኢየሱስ ክርስቶስና በድንግል ማርያም ተረጋግጦ ታይቷል። ሔዋን፡ ለክፋትና ለሐሰት፥ ለኃጢአትና ለሞት ምክንያተ ስሕተት ስትኾን፥ ድንግል ማርያም ደግሞ፡ ለደግነትና ለእውነት፥ ለምሕረትና ለሕይወት፡ ምክንያተ ድኅነት መኾኗንም፡ ኢትዮጵያውያት ልጆቻችን፥ እህቶቻችንና እናቶቻችን ያውቁታል። ስለዚህ፡ አርአያቸው አድርገው ሊከተሏት የሚገባቸው፡ ቅድስት ድንግል ማርያምን ብቻ እንጂ፡ ሔዋንን ባለመኾኑ፡ ከእግዚአብሔር የተቀበልናቸውንና በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሱትን፡ የኢትዮጵያዊነት ሃይማኖታችንንና ምግባራችንን፥ ሥርዓታችንንና ባህላችንን አጽንተን በመጠበቅ ረገድ ኢትዮጵያውያት ሴቶች፡ አዛውንቱም፥ ወጣቶቹም፡ ያለባቸው ባለአደራነትና ተጠያቂነት፡ ከፈጣሪያቸው መኾኑን ተገንዝበው፡ ግዳጃቸውን፡ ከወንዶቹ ጎን በመሰለፍ፡ በመሥዋዕትነት ሳይቀር ሊፈጽሙ ይገባቸዋል።

\+ + + + + + +




አለቃ ለማ ኃይሉ ወልደ ታሪክ።

## ለአንባቢው የቀረበ  የሙገሳ ቃል

የበኩልዎን ግዳጅ፡ ባግባብ ለፈጸሙት፤
መልእክቱን በማንበብ፡ ጀግና ለተባሉት፤
የጥንቱ በረከት፡ ይኸው ይቀበሉት፦
ከዘላለሙ እርሻ፡ ሰብልዎን ለማምረት፥
የራስዎን ተግባር፡ ፈጽመው መገኘት፤
የቀረውን ኹሉ፡ ለእርሻው ባለቤት፡
ትተው መከተል ነው፡ የእግዚአብሔርን እውነት።

\+ + +



አቶ መንግሥቱ ለማ፤

(የኹለቱም ዝክረ ነገር፡
በገጽ ፩፻፫-፩፻፲ ይገኛል።)

ኢትዮጵያ፡



# በኢትዮጵያ፡

# የእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎት

## መመሪያ ሥርዓት

### መቅድም

እኛ ኢትዮጵያውያን፡ በሃይማኖትና በቃል ኪዳን ጸሎቶቻችን፥ እንዲሁም፡ ለሰማዩ አባታችንና ለዘለዓለማዊቷ እናታችን በምናቀርባቸው የምስጋና ቃሎቻችን ውስጥ የተገለጹትን፡ የእምነት መመሪያዎቻችንን ተከትለን፡ ይኸው፡ የኢትዮጵያዊነት ሕይወታችንን በየግላችን እየኖርን እንገኛለን።

ከዚህ የተነሣ፡ እግዚአብሔር፡ በቸርነቱ ብዛት፡ እያንዳንዳችን፡ በኢየሱስ ክርስቶስ በተገኘው ጸጋ፡ የዘለዓለማዊ ክብሩና የባሕርይ ገናንነቱ ተካፋዮች እንድንኾን ባደረገባት መንግሥቱ ውስጥ፡ መሰል የሌላትንና አምላካዊት የኾነችውን፡ የዜግነት መብት፡ በነፍስና በሥጋ፥ በመንፈስም አጎናጽፎናል። ይኸውም፡ ለኢየሱስ ክርስቶስ፡ ቀዳሚ አርአያና ለኢትዮጵያዊነት ደግሞ፡ መደበኛው ግንድ እንደኾነው፡ እንደመልከ ጼዴቅ ሰውነት ኹሉ፡ እኛም፡ በነፍስ ወከፍ፡ እየራሳችንን በንስሓ እያደስን፡ ቅዱሱን ቁርባን የምንቀበል በመኾናችን፡ የአንድነትና የሦስትነት ባሕርያት ላላቸው፡ ለሦስቱ የእግዚአብሔር መንግሥት ዘርፎች፡ ማለትም፡ ለቤተ ሕዝብ፥ ለቤተ ምልክናና ለቤተ ክህነት ባለቤነትነት የበቃንበት፡ ያ፡ በመንፈስ ቅዱስ የተቀዳጀነው፡ የእግዚአብሔር ልጆች የመኾን ክብር ነው።

እንግዲህ፡ በኪዳነ ልቦና ተመሥርቶና በኪዳነ አሪት ጸንቶ፡ በኪዳነ መንፈስ ቅዱስ የተፈጸመውን፡ ይህን የመሰለውን መለኮታዊ በረከት ለመቀበል የታደልን፡ እኛ የኢትዮጵያ ልጆች፡ ይህንኑ፡ ከእግዚአብሔር ያገኘነውን ዘለዓለማዊ ጸጋ፡ በየግላችንና ለየግላችን ብቻ ሳይኾን፡ በኅብረትና ሌሎች ወገኖቻችንም፡ ለዚሁ የንስሐ ሕይወት እንዲበቁ በማድረግ፡ እውን በኾነ ሕያው አገልግሎት፡ በምግባር ተርጉመን፡ ለፍሬ ማብቃት እንደሚገባን ተገነዘብን። ደግሞም፡ ለግል፥ ለቤተሰብና ለኅብረት ኑሮአችን፡ መመሪያ እንዲኾነን፡ ከፈጣሪያችን የተሰጠን፡ ይህ አምላካዊ ሥርዓት፡ በተለይ፡ በእኛ በኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ እስከሁን ጸንቶና ተጠብቆ የኖረ በመኾኑ፡ ወደፊትም፡ ከትውልድ ወደትውልድ እየተላለፈ የሚኖር እንጂ፡ በማንም ፍጡር ሊሻር የማይቻል፥ የማይገባም መኾኑን፡ በጠለቀ ሃይማኖታዊ መንፈስ ተረዳን።

## ኢትዮጵያ:

በዚህ መልክ: ከጥንት አባቶቻችንና እናቶቻችን ሲያያዝ መጥቶ: እነሆ ዛሬ እኛ የተረከብነውንና ኢትዮጵያዊ ግዴጃችን የኾነውን: ይህንኑ ተልእኳችንን: አጠናክረን ለመቀጠል እንችል ዘንድ: በዚሁ በያዝነው የእውነተኛ ኢትዮጵያዊነታችን አቋም: እስከመጨረሻው ጸንተን፥ በመንፈስ ቅዱስም: አንድ ልብ ኾነን፥ የእግዚአብሔርን ቃል: መሠረታችንና መመሪያችን፥ መነሻችንና መድረሻችን አድርገን: በቁርጥ በመነሣት: ተባብረን መሥራት እንዳለብን አምነን ተስማማን::

### መግቢያ

ለዚህ ስምምነታችን: መሠረትና አዕማድ፥ መመሪያና ፋና ሊኾኑን: የእግዚአብሔር ቃላት መካከል: ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገራቸው: ከዚህ የሚከተሉት ይገኛሉ:: እነዚህም:-

፩ኛ:- ቀደም ብሎ: በመጀመሪያ: በብሉዩ ኪዳን: *"እኔ ራሴ: ሕጌን በልቡናቸው አኖራለሁ፤ በልባቸውም እጽፈዋለሁ:: ስለዚህ: ሰው: ባልንጀራውን: 'እግዚአብሔርን እወቅ' ብሎ አያስተምርም፤ ኹሉ ያውቁኛልና!"*

፪ኛ:- ኋላም: በመጨረሻ: በአዲሱ ኪዳን: *"ከእናንተ: ኹለቱ: በምድር ላይ: በሚለምኑት ነገር ኹሉ ቢስማሙ: በሰማያት ካለው ካባቴ ዘንድ ይደረግላቸዋል:: ኹለት ወይም ሦስት: በስሜ በሚሰበሰቡበት: በዚያ በመካከላቸው እኾናለሁና!"* ሲል ያሰማቸውና በትንቢተ ኤርምያስ: ምዕራፍ ፴፩፥ ቁጥር ፴፫-፴፬፥ ቀጥሎም: በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ ፲፰፥ ቁጥር ፲፱-፳ ተጽፈው የሚነበቡት ናቸው::

እግዚአብሔር: እንዲህ አድርጎ: እርሱን እናውቀው ዘንድ: በየልቦናችን የጻፈውን ሕጉንና ያስተማረንን ትምህርቱን፥ በቃሉም ያሰማንን ተስፋውን አምነንና ተከትለን: በየግል ሰውነታችን ስንኖረው የቆየውን የአገልግሎት ሕይወታችንን: አሁን ደግሞ: እርሱ ራሱ: ኢየሱስ ክርስቶስና ቅድስት እናቱ: ድንግል ማርያም: ዙፋናቸው: በመንፈስ ቅዱስ ተዘርግቶ: በሰብሳቢነታቸውና በመሪነታቸው ተቀምጠው በሚያካኺዱት: በዚህ የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎታችን አማካይነት: በጋራ እንዲቀጥል እናደርግ ዘንድ: መለኮታዊ ጥሪው እነሆ ቀረበልን::

እኛም: ጥሪውን ተቀብለን: ቀደም ብሎ: በየልቦናችን ተቀርጾና ከዚህ በታች በፊደላት ገዝፎ በተጻፈው መመሪያ መሠረት: በግል: ከእያንዳንዳችን፥ በጋራ ደግሞ: ከኹላችን የሚጠበቀውን: የኢትዮጵያዊነት ተግባር ለመፈጸም: ተዘጋጅተን እንገኛለን:: ይህንንም: በመለኮታዊቷ መንግሥት ዙፋን ፊት: በእውነትና በመንፈስ ቆመን: ለዚህ ያበቃንን ጌታ፥ ቅድስት እናቱንም በማመስገንና እንደገና የምስክርነት ቃላችንን በይፋ በመስጠት እናረጋግጣለን::

# አንቀጽ አንድ

## ስያሜ

የአገልግሎቱ ስም: "በኢትዮጵያ: የእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎት" ነው:: በዚህ መመሪያ ውስጥ: ባጭር ቃል: "አገልግሎት" ተብሎ ይጠቀሳል:: እያንዳንዱም ቅርንጫፍ: በሚገኝበት አድራሻ የሚታወቅ ይኾናል::

# አንቀጽ ኹለት

## አቋም

የአገልግሎቱ አቋም: ከዚህ በኋላ: "ቀኖናዊ መርህ" ወይም "ሃይማኖታዊ መመሪያ" እየተባለ በሚጠቀሰው: በኢትዮጵያ የቅዱሱ ኪዳን ተዋህዶ ሃይማኖት ላይ የተመሠረተ ነው:: የአገልግሎቱ መመሪያዎች÷ ምግባሮችና ሥርዓቶች ኹሉ: ያሳንዳች መዛባት: በሙሉ የሚመነጩት: ከዚህ ቀኖናዊ መርህ ብቻ ይኾናል:: ይህ ቀኖናዊ መርህ: በኢትዮጵያውያን ልቦና ተመዝግበውና በልማድ ታውቀው÷ በቃል ሲነገሩና በምግባር ሲፈጸሙ በኖሩት÷ ዛሬ ግን በጽሑፍ ሠፍረውና የዚህ መመሪያ አካል ኾነው: ከነመዝሙሮቻቸው በተያያዙት:-

፩ኛ:- የኢትዮጵያውያን የቃል ኪዳን ጸሎት÷
፪ኛ:- የኢትዮጵያውያን የሃይማኖት ጸሎት÷
፫ኛ:- ኢትዮጵያውያን: ለጌታ የሚያቀርቡት የምስጋና ጸሎት÷
፬ኛ:- ኢትዮጵያውያን ለድንግል ማርያም የሚያቀርቡት

የሰላምታ ጸሎት በተባሉት: በዚህ መጽሐፍ: በገጽ ፩፻፹፰-፩፻፺፩ ላይ በሚገኙት ቃላት ተብራርቷል::

የእነዚህ አራት ጸሎታት ትርጓሜና ሐተታ: በዚህ መመሪያ ውስጥ አባሪ ኾነው ከተያያዙት: የኢትዮጵያውያን መዝሙሮች ጋር÷ በተለይ: በዚህና "ኢትዮጵያዊው÷ በማንነቱ ፍለጋ!" በተባለው: በንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ ተዘጋጅቶ: በሚያዝያ ፳፯ ቀን÷ ፲፱፻፺፩ ዓ. ም.: በአዲስ አበባ÷ ኢትዮጵያ በታተሙት ኹለት መጻሕፍት ውስጥ በሰፊው ተተንትኗል:: እነዚህም መጻሕፍት: በአገልግሎቱ አባሎች እጅ ኾነው: የዘወትር አስታዋሽነታቸውን ግልጋሎት ይሰጣሉ::

# አንቀጽ ሦስት

## ዓላማ

የአገልግሎቱ ዓላማ: በዚህ መመሪያ ውስጥ: ባጭር ቃል: "ሕያው ውርስ" ተብሎ የሚጠራውንና በአንቀጽ ኹለት: "ቀኖናዊ መርህ" የተባለውን: ቅዱሱን ኪዳን:

፩ኛ:- እያንዳንዱ አባል: በሃይማኖታዊነቱም ኾነ በምግባራዊነቱ: ራሱ ሕይወት አድርጎት መኖሩን: በሚያስተማምን ኹኔታ ማረጋገጥ፤

፪ኛ:- ራሱን በንስሐ አድሶ ለሚቀርብ: "ኢትዮጵያዊ ነኝ" ለሚለው: ወንድ ኾነ ሴት ለኾነ ወገንና ለዚህ ኢትዮጵያዊነት ሊበቃ በሚፈቅድ: በማናቸውም ግለሰብ ሕያው ሰውነት: ይኸው ቅዱሱ ኪዳን: በተቻለ መጠን: በግል: በእያንዳንዱ አባል÷ በጋራ ደግሞ: በአገልግሎቱ አማካይነት: ተገቢ በኾነው ዘዴና መንገድ: በጤናማነት እንዲጠበቅ÷ በዚሁ የትንሣኤ ባሕርዩም እንዲቀጥል÷ በፍጥረተ ዓለሙ ዘንድ እንዲታወቅና በዘለዓለማዊ ህልውናው: ለትውልደ ትውልድ እንዲተላለፍ ማድረግ ነው::

ኢትዮጵያ፡

## አንቀጽ አራት

### የዓላማው ጊዜያዊ አፈጻጸም

የአገልግሎቱ ዓላማ፡ በግል በእያንዳንዱ አባል፥ በጋራም በአገልግሎቱ ቤተ ሕዝብና የእርሱ ዘርፎች በኩኑት፡ በቤተ ክህነቱና በቤተ ምልክናው አማካይነት፡ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ምግባራት፡ በጊዜያዊ መልኩ፡ በሥራ ላይ ውሎ ይፈጸማል።-

፩ኛ:- እያንዳንዱን ኢትዮጵያዊ፡ በአጠቃላይም፡ "ኢትዮጵያዊ ነኝ" የሚለውን ወገንና ሌላውን ግለሰብ:-

(ሀ) በግንባር ተገናኝቶ በማነጋገር፥
(ለ) በቃልና በጽሑፍ በማስተማር፥
(ሐ) ድርሰቶችን አሳትሞ በማሠራጨት፥
(መ) በነፋስ ድምፅና በነፋስ ሥዕል፥ በጎዋ መልእክትና በደብዳቤ አማካይነት በማስተላለፍ፥
(ሠ) በንግግርና በሥዕል ጥብጣብ ቀርጸ በማዳረስ፥
(ረ) ስብሰባን፥ ጉባዔንና የጥናት ሸንጎን በማዘጋጀት፥
(ሰ) "ኪዳናችን" በተባለው የአገልግሎቱ ጦማረ ሕዝብና በሌላ በማናቸውም የመገናኛ ዘዴ በመጠቀም፡

ሕያዉን ውርስ በሚመለከትና ራስን በንስሓ፡ እንዴት ለእውነተኛው ኢትዮጵያዊነት ማብቃት እንደሚቻል፡ ሙሉ እውቀትንና መረጃን፥ መመሪያንና የምክር እርዳታን እንዲያገኙ ማድረግ፤

፪ኛ:- ከዚህ መመሪያ ሥርዓት ጋር በተያያዘው፡ "ቃለ ዓዋዲ" በተባለው፡ የኢትዮጵያ፡ የነጋሪት ቀላጤ፡ ስለሰበካ ጉባዔ አስተዳደር፡ በጥቅምት ፲፭ ቀን፥ ፲፱፻፷፭ ዓ.ም. ታትሞ በወጣው ደንብ መሠረት ተቋቁመው፡ ኢትዮጵያውያን ካህናትን ለሚያስተዳድሩና ምእመናንን ለሚያገለግሉ ሰበካ ጉባዔዎች፥ እንዲሁም፡ የሰበካ ጉባዔዎች ባልተቋቋሙባቸው ሥፍራዎች ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ሌሎች ወገኖች ጭምር፡ ከማኅበሩ ቤተ ሕዝብ ሠርፀው፡ የአገልግሎቱ ዘርፎች በኩኑት፡ በቤተ ክህነቱና በቤተ ምልክናው አማካይነት፡ ዓቅም የሚፈቅደውን፡ ማናቸውንም አስፈላጊና ተገቢ የኾነ፡ መንፈሳዊና ሥጋዊ አገልግሎትንና እርዳታን ማበርከት፤

፫ኛ:- ሕያዉን ውርስ፡ ከትውልድ ወደትውልድ እና ከአንዱ ወደሌላው ለማስተላለፍ፥ በበለጠም ለማሳወቅ፡ እስካሁን በመሣሪያነት ያበረከቱት አገልግሎት ይቀጥል ዘንድ፡ ኢትዮጵያውያን መምህራንን፥ ካህናትን፥ መተርጉማንን፥ ደራስያንን፥ ሠዓልያንንና ከሕያዉ ውርሳችን ጋር የተዛመደ ሙያና ጥበብ ያላቸውን ግለሰቦች ኹሉ ፈልጎ ማግኘት፥ ለአገልግሎት መመደብ እና/ወይም ማሠልጠን፤

፬ኛ:- ኢትዮጵያውያን ሕፃናትና ትልልቆች ጭምር: የማንነታቸው መገለጫ የኾነው: የቅዱሱ ኪዳን ሕዝብነታቸው: ለመቼውም ጊዜ: በአእምሮአቸውና በየልቦናቸው ተቀርጾ ይኖር ዘንድ: ከሕያዉ ውርስ የሠረፁትንና የኢትዮጵያ ብቸኛ ሀብቶች የኾኑትን የእውቀትና የሙያ፥ የሥነ ምግባርና የባህል ቅርሶች የያዘውን ሥርዓተ ትምህርት ተከትለው የሚያስተምሩ የትምህርት ተቋማትን: አግባብ በኾኑ ቦታዎች መመሥረት፤

፭ኛ:- ለኢትዮጵያውያንና ለሌሎችም: የሥራ ዕድልን በመፍጠር: የአገሪቱ ምድር በምታፈራቸው ሰብሎችና ንጥረ ነገሮች: እየተሠሩ የሚወጡትን የምርት ውጤቶች: በዓይነትና በመጠን ከፍ ለማድረግ ይቻል ዘንድ: ከሕያዉ ውርስ ባህል ጋር የሚስማሙትን ልዩ ልዩ ያገርቤት ፅንሰ አሳቦችንና ጥበቦችን፥ የሥነ እውቀትና የተግባረ እድ ሙያዎችን: አግባብ ባለው መንገድና ዘዴ አጥንቶ መለየት፥ ማዳበርና በሥራ ላይ ማዋል፤

፮ኛ:- ሕያዉን ውርስ በሚመለከት: የጥናት፥ የምርምር እና/ወይም የትርጉም ሥራ በማካኼድ: የአገልግሎቱ ዓላማዎች: በተግባር ላይ ውለው: ሙሉ ተፈጻሚነትን እንዲያገኙ የሚያደርግ: አንድ አጠቃላይ የኾነ የመካነ አእምሮ ድርጅት ማቋቋም፤

፯ኛ:- ለዓላማዎቹ መሳካት: ተጻራሪ አቋም ከሌላቸው ሌሎች ግለሰቦች፥ ማኅበሮችና ድርጅቶች ጋር መተባበር::

# አንቀጽ አምስት

## አባልነት

### ንዑስ አንቀጽ ፩

### አባልነት

በአገልግሎቱ ውስጥ ሙሉ አባል ለመኾን: ማናቸውም ግለሰብ: ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ይዘቶች አሟልቶና ፈጽሞ እንዲገኝ ያስፈልጋል::

፩ኛ: "ኢትዮጵያዊ ነኝ" ብሎ: ራሱን በንስሐ አድሶና በቅዱስ ቁርባን አጽድቶ የሚቀርብ፥

፪ኛ: የኢትዮጵያዊነቱ መታወቂያ በኾነው: በቀኖናዊው መርሀ ውስጥ በተብራራው: በኢትዮጵያ የቅዱሱ ኪዳን ተዋህዶ ሃይማኖት ጸንቶ የሚገኝ፥

፫ኛ: ቀኖናዊዉን መርሀ: በእውነትና በታማኝነት መቀበሉን፥ ይህንኑም ጠብቆ፥ አጽንቶና አሳውቆ የሚኖር መኾኑን: የቃል ኪዳን ምስክርነትን በይፋ በመስጠት የሚያረጋግጥ፥

፬ኛ: ቀኖናዊው መርሀ የሚጠይቀውን የኑሮ ሥርዓት ተከትሎ: ራሱን: የዚያ ሥርዓት ሕያው መገለጫ በማድረግ: ሕይወቱን የሚመራ፥

፰ኛ፡ ቀኖናዊው መርህ በደነገጋቸው ሥርዓቶች መሠረት፡ በቤተሰቡ ውስጥ ከሚተዳደረው፡ ከእያንዳንዱ አባል ጀምሮ፡ ተገቢውን መመሪያና ትምህርት በመስጠት፡ የኢትዮጵያዊን ማንነትና የኢትዮጵያዊነትን ምንነት፡ ከትውልድ ወደትውልድ ለማስተላለፍ ያለበትን ተግባርና ኃላፊነት ተገንዝቦ፡ ይህንኑ ግዳጁን በሥራ ላይ የሚያውል÷

፱ኛ፡ የአገልግሎቱን ዓላማዎችና በዚህ መምሪያ የተደነገጉትን ሥርዓቶች፡ ራሱ አክብሮ የሚፈጽምና በቆራጥነት የሚያስፈጽም÷

፲ኛ፡ ዕድሜው፡ አሥራ ስምንት ዓመታት፡ ወይም ከዚያ በላይ የኾነ ሰው፡ ጾታና ሙያ÷ የመኖሪያ ቦታም ሳይወስነው፡ በአገልግሎቱ የሥራ ዘርፎች ውስጥ የሚመደቡትን አገልጋዮች ለመምረጥ እና/ወይም፡ ራሱ ለመመረጥ የሚያበቃውን የሙሉ አባልነት መብትን ማግኘት ይችላል።

ነገር ግን፡ ማናቸውም አባል፡ በዚህ መመሪያ ሥርዓት ውስጥ፡ በየአንቀጹ ለተጠቀሱት፡ ለአገልግሎቱ ሙሴነት÷ እንዲሁም፡ ለሦስቱ የአገልግሎት ቤቶች፡ ማለትም፡ ለቤተ ሕዝቡ÷ ለቤተ ክህነቱና ለቤተ ምልክናው ሊቀ መንበርነት ለሚያበቃው ምርጫ እጩ መኾን የሚችለው፡ ሰላሣ ዓመታት፡ ወይም ከዚያ በላይ ከኾነ የዕድሜ ደረጃ የደረሰ መኾኑ ሲረጋገጥ ብቻ ይኾናል።

## ንዑስ አንቀጽ ፪

## የአባልነት ሥርዓት

አንድ ሰው፡ አባል ለመኾን፡ በቅድሚያ፡ ቢያንስ ቢያንስ፡ ኹለት ነባር አባሎች፡ በቃል ወይም በጽሑፍ፡ ለአገልግሎቱ ሙሴ በሚያቀርቡት ማስታወሻ፡ እጩ ኾኖ መቅረብ ይኖርበታል፤ ይህንኑ፡ ሙሴው ደግሞ፡ ወደአገልግሎቱ ምርፋቅ ካስተላለፈው በኋላ፡ በዚያ ምርፋቅ ስብሰባ ላይ የተገኙት አባሎች፡ እጩውን በአንድ ድምፅ ተስማምተው፡ ሲቀበሉት፡ አባል ይኾናል። ይህም ውሳኔ፡ ለመላው አባሎች በይፋ ይገለጣል።

## ንዑስ አንቀጽ ፫

## ከአባልነት ስለመገለልና ስለመታገድ

ማናቸውም አባል፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነቱን ካልካደ፡ ወይም በራሱ ፍላጎትና ጥያቄ ካልኾነ በስተቀር፡ ከአባልነቱ አይገለልም፡ አይታገድም።

አንድ አባል፡ ኾነ ብሎ፡ በአገልግሎቱ መመሪያ ውስጥ የሠፈሩትን ሥርዓቶች፡ በተደጋጋሚ ቢተላለፍ፡ ወይም የአገልግሎቱን መልካም ስምና በጎ ዓላማ የሚጻረር ጠባይ ቢያሳይ፡ ወይም ይኸው ግለሰብ፡ ከአባልነቱ፡ የመገለል ወይም የመለየት ጥያቄና ፍላጎት ኖሮት፡ ይህንኑ፡ በቃል ወይም በጽሑፍ ገልጾ፡ ለሙሴው ማስታወሻ ቢያቀርብ፡ ሙሴው፡ ይህንኑ ጉዳይ፡ ወዲያው፡ ለምርፋቁ፡ በመጀመሪያው ስብሰባ ላይ ያቀርበዋል።

በዚህ ኹኔታ የሚገኘውን አባል፡ ሙሴውና በእርሱ የተመረጡ አባሎች፡ እስከሦስት ጊዜያት ድረስ፡ በሽምግልና መልክ ይጠይቁታል፤ ያነጋግሩታል፤ ይመክሩታል። ነገር ግን፡ ይኸው አባል፡ የቀረበለትን ጥያቄና ምክር የማይቀበል ኾኖ በሚገኝበት ጊዜ፡ በራሱ ፍላጎትና ፈቃድ፡ ከአባልነቱ እንደታገደ፡ ወይም ጨርሶ እንደተወገደ ይቆጠራል።

ይኹን እንጂ፡ አንድ አባል፡ በዚህ መልክ፡ ከአባልነቱ መገለሉ፡ ወይም መታገዱ፡ ወይም ጨርሶ መወገዱ የሚረጋገጠው፡ ጉዳዩ፡ በመጀመሪያ ደረጃ፡ ከመላው የምርፋቁ አባሎች መካከል፥ ቀጥሎም፡ በመጨረሻው ደረጃ በሚደረገው፡ በሚቀጥለው የአገልግሎቱ ጠቅላላ ጉባዔ ላይ፡ ከመላው አባሎች መካከል፡ እጅግ ቢያንስ፡ ኹለት ሦስተኛዎቹ በተገኙበት ቀርቦ ሲወሰን ብቻ ነው። ይህም፡ ፩ኛ፡ በማቴዎስ ወንጌል፡ ምዕ. ፲፰፥ ቁ. ፲፭-፳ የተጻፈውን፡ የጌታን ቃል በማብራራት፥ ፪ኛ፡ በመጀመሪያውም ኾነ በኹለተኛው ደረጃ፡ በጉዳዩ ላይ፡ የመጨረሻ ውሳኔ ከመሰጠቱ፡ አሥራ አምስት ቀኖች በፊት፡ የስብሰባውን ጊዜና ቦታ በማመልከት፡ ለተጠያቂነት ያበቃውን ምክንያት የያዘው መግለጫ፡ በቃል ወይም በጽሑፍ፡ ለሚመለከተው አባል ከደረሰው በኋላ ይኾናል።

ይህን ጉዳይ፡ ከመልካም ፍጻሜ ለማድረስ ሲባል፡ የአባሎች ልዩ ስብሰባ እንዲደረግ የሚያስፈልግ ኾኖ ቢገኝ፡ ይህን የመሰለው አሠራር፡ አገልግሎቱ ለቆመለት ዓላማ፡ ተገቢነት ያለው በመኾኑ፡ ማናቸውም የሚመለከተው ወገን፡ ስብሰባው እንዲጠራ፡ በቀጥታ፡ ለሙሴው ማሳሰብ፥ ሙሴውም፡ ከምርፋቁ ጋር ተመካክሮ፡ ጉባዔውን ሊሰበስብ ይችላል።

በዚህ መልክ፡ ከአባልነት የተለየው ግለሰብ፡ በማናቸውም ጊዜ፡ በንስሓ ቢመለስ፡ የነበረበትን የአባልነት ክብር የመቀዳጀት መብቱ፡ ምንጊዜም የተጠበቀለት መኾኑ፡ ከአባልነቱ፡ በራሱ ፈቃድ በሚለይበት እና/ወይም በአገልግሎቱ ጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔ መሠረት በሚወገድበት ዕለት፡ በገሃድ ይነገረዋል።

# አንቀጽ ስድስት

## ስብሰባዎች

አገልግሎቱ፡ ዓላማቸው አንድ የኾነ፥ ነገር ግን ይዘታቸው የተለያየ፡ የስብሰባ ሥርዓቶች አሉት። እነዚህም፡ ከዚህ የሚከተሉት ናቸው፡-

### ንዑስ አንቀጽ ፩

### ሰሙናዊ ስብሰባ

በዚህ ሰሙናዊ ስብሰባ፡ አባሎች ኹሉ፡ በየሳምንቱ እሑድ፡ በዕለተ ሰንበተ ክርስቲያን፡ ከንጋቱ ፲፪ ሰዓት በፊት፡ ከመላው ቤተሰባቸው ጋር፡ በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ተገኝተውና የቅዳሴ ሥርዓተ ጸሎታቸውን ፈጽመው፡ ቅዱስ ቁርባንን ይቀበላሉ።

ይህም፡ ኢየሱስ ክርስቶስና እናቱ ድንግል ማርያም፡ በመንበራቸው ተቀምጠው፡ የቃል ኪዳን ልጆቻቸው የኾኑት ኢትዮጵያውያን፡ ሴቶቹም፥ ወንዶቹም፡ በቅዱሱ ገበታ ዙርያ፡ በፊታቸው ተሰባስበው፡ ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን የሚቀበሉበት፡ አማናዊው የእግዚአብሔር መንግሥት ጉባዔ ነው። በዚህ ቅዱስ ጉባዔ፡ ሌሎቹ የአገልግሎቱ ስብሰባዎች ኹሉ ይቀደሳሉ፤ መሠረታቸውና ቀዳሚያቸውም ስለኾነ፡ ይህ ሰሙናዊ ስብሰባ፡ በአባሎች ዘንድ፡ በፍጹም ልዕልና ይከበራል።

ከቅዳሴው ሥርዓት በኋላ፡ በቤተ ክርስቲያን የተገኙት አባሎች፡ ከኢትዮጵያዊነት የዘር አባታቸው፡ ከመልከ ጼዴቅ፡ በቃል ኪዳን የወረሱትን፡ የተቀደሰውን የጠበል ጠዲቅ ሥርዓታቸውን ያከናውናሉ። ቀጥሎ፡ የትምህርት ውይይታቸውን ያካኺዳሉ። በመጨረሻ፡ የእርስ በርስ ንግግር ተለዋውጠው፡ የተወሰነው ጊዜያቸው ሲያበቃ፡ በፍቅር ተሰነባብተው ይለያያሉ።

## ንዑስ አንቀጽ ፪

## ወርኃዊ ስብሰባ

የየወሩ አሥራ ስድስተኛ ቀን፡ ማለት የኪዳነ ምሕረት በዓል፡ ከሰምንቱ ሰኞ እስከረቡዕ ሲውል፡ በወዲህኛው የዕለተ እሑድ፡ ሰንበተ ክርስቲያን፥ ከሐሙስ እስከቅዳሜ ሲውል ደግሞ፡ በሚቀጥለው የዕለተ እሑድ ሰንበተ ክርስቲያን፡ ሥርዓተ ቅዳሴያቸው ከተፈጸመ በኋላ፡ ከጧቱ ፬ እስከ ፯ ሰዓት ድረስ፡ የአባሎች ወርኃዊ ስብሰባ ይደረጋል።

የዚህ ስብሰባ ዓላማ፡ አባሎች፡ ከነቤተሰቦቻቸው፡ በበለጠ ተቀራርበው፡ ማኅበራዊ ግንኙነታቸውን እንዲያጎለምሱ፥ በመካከላቸው ያለውን የኅብረተሰብ አንድነት እንዲያጠናክሩ፥ ለአባሎችና አባሎች ላልኾኑ ጭምር ለሚያስፈልገው በጎ ምግባር፡ የእርስበርስና የኅብረት መረዳዳትን እንዲያጎለብቱ፥ እንዲሁም፡ እያንዳንዳቸው፡ በነፍስ ወከፍ፥ በአጠቃላይ ደግሞ፡ ኹሉም፡ አገልግሎቱ ለተቋቋመበት ዓላማ፡ ያላቸውን ግንዛቤ እንዲያሳድጉ፡ ማድረግ ይኾናል።

በእኒህ ስብሰባዎች ላይ፡ ንግግሮችና ውይይቶች፥ ባህላዊና ትምህርታዊ መዝናኛዎች፡ እንዲሁም ሌሎች ማኅበራዊ ዝግጅቶችና የአዳዲስ አባሎች ትውውቅ፥ ደግሞም፡ የአገልግሎቱን ተግባሮች በሚመለከት፡ የማስታወቂያዎችና የመግለጫዎች ሥርጭት እንደአስፈላጊነታቸው ሊቀርቡ ይቻላል።

## ንዑስ አንቀጽ ፫

## የጠቅላላው ጉባዔ፡ ዓመታዊ ስብሰባ

በየዓመቱ መጨረሻ ቀዳሚት ሰንበት እና በተከታይዋ ሰንበተ ክርስቲያን እሑድ፡ መላው አባሎች የሚገኙበት፡ የአገልግሎቱ ዓመታዊ ስብሰባ ይደረጋል።

የዚህ ስብሰባ ዋና ዓላማዎች፡-

፩ኛ፡ ቤተ ምልክናውንና ቤተ ክህነቱን የሚያስገኘውን፡ የቤተ ሕዝቡን ጠቅላላ ጉባዔ ተወካዮች፡ በየሦስት ዓመታቱ ለመምረጥ፥

፪ኛ፡ ሙሴው፡ አገልግሎቱ ስለሚገኝበት ኹኔታ፡ የሚያቀርበውን ጠቅላላ መግለጫ ለመስማት፥

፫ኛ፡ መላው አባሎች ሊያውቋቸው፡ ወይም ለእነርሱ ሊቀርቡ የሚገቡ ሌሎች ጉዳዮች ካሉ፡ እነዚያን ለመስማት፡ ወይም በእነዚያ ላይ ውሳኔ ለመስጠት ይኾናል።

ለጠቅላላው ጉባዔ የሚመረጡት ተወካዮች፡ ቁጥራቸው፡ እንደአባሎቹ ብዛት እየታየ ይወሰናል። ነገር ግን፡ ምንጊዜም፡ ከመላው አባሎች ቁጥር፡ ከአራት አንድ እጅ አያንስም።

## ንዑስ አንቀጽ ፬

## ልዩ ስብሰባ

ሙሴው ወይም ምርፋቁ፡ አስፈላጊ መስሎ በታየው፡ በማናቸውም ጊዜ፡ የአባሎች ልዩ ስብሰባ፡ ወይም የአገልግሎቱ ጠቅላላ ጉባዔ እንዲደረግ መጥራት ይችላል። ደግሞ፡ ከአባሎቹ መካከል፡ አንድ ሦስተኛው ያህል፡ በቃል ወይም በጽሑፍ የጠየቁ እንደኾነ፡ ሙሴው፡ ከምርፋቁ ጋር ተወያይቶ፡ ልዩው ስብሰባ እንዲደረግ ይጠራል።

ማናቸውም ልዩ ስብሰባ እንዲደረግ የሚተላለፈው ጥሪ፡ ለዓመታዊው ስብሰባ ጥሪ በሚፈጸመው መልክ ይኾናል። "ለስብሰባው ቀርቦ ይታያል" ተብሎ፡ በቃል ከተነገረው፡ ወይም በጥሪው ማስታወቂያ ውስጥ ከተጠቀሰው በቀር፡ አባሎቹ በሚያደርጉት በማናቸውም ልዩ ስብሰባ ላይ፡ እንዳችም ሌላ የሥራ ጉዳይ ቀርቦ አይታይም።

## ንዑስ አንቀጽ ፭

## ምልዓተ ጉባዔ

በአገልግሎቱ የሥራ ጉዳይ ላይ ተነጋግሮ ለመወሰን፡ የኃላፊነትና የተጠያቂነት ሥልጣን ያለውን ምልዓተ ጉባዔ ለማግኘት፡ ምንጊዜም፡ ድምፅ የመስጠት መብት ያላቸው አባሎች፡ አብዛኛዎቹ በአካል የሚሳተፉበት ስብሰባ እንዲኖር ያስፈልጋል። በዚህ ጊዜ፡ በአገልግሎቱ ጠቅላላ ጉባዔና በምርፋቁ፥ እንዲሁም፡ ለተለያዩ ጉዳዮች ተመርጠው በሚደረጉ፡ የየሕዋሳቱ ስብሰባዎች ላይ፡ ሙሴው ወይም የየስብሰባው ሊቀ መንበርና አብዛኛዎቹ የጉባዔው፡ ወይም የምርፋቁ፡ ወይም የየሕዋሱ አባሎች ከተገኙ፡ ምልዓተ ጉባዔ እንዳለ ተቆጥሮ፡ የአገልግሎቱን ሥራ ለማካኼድ ይቻላል።

ሙሴው በማይገኝበት ጊዜ፡ ግልገል ሙሴው፥ ወይም፡ የየቤቱ ሊቀ መንበርና የየሕዋሱ ሰብሳቢ በማይገኝበት ጊዜ ደግሞ፡ ምክትሉ፡ ስብሰባዎችን፡ በሊቀ መንበርነት ይመራል። ምልዓተ ጉባዔ በማይገኝበት ጊዜ፡ ቁጥራቸው አናሳ የኾነው አባሎች፡ ስብሰባውን፡ ከአሥር ቀኖች ላልበለጠ ለሌላ ዕለት ቀጥረው መለያየት ይችላሉ።

ምልዓተ ጉባዔ መኖሩ ከተረጋገጠ በኋላ፡ ለየስብሰባው የቀረበው ጉዳይ ወይም ምርጫ፡ በተባበረ አንድ ድምፅ እንዲወሰን፡ የተቻለው ይደረጋል። ይህ ያልተቻለ እንደኾነ፡ ጉዳዩ ወይም ምርጫው፡ ለዕጣ ይቀርባል። የዕጣ አወጣጡ ሥርዓት፡ በሐዋርያት ሥራ፡ ምዕ. ፩፥ ቁጥር ፲፩-፳፮ ላይ በተጻፈው መሠረት፡ ተገቢው ጸሎት ተከናውኖ ይፈጸማል።

## ንዑስ አንቀጽ ፮

## የስብሰባ ጥሪና በስብሰባ አለመገኘት

የስብሰባ ጥሪ፡ ቀንና ሰዓት፥ ቦታውና ምክንያቱ ጭምር፡ ለመላው አባሎች፡ በሙሴው፡ ወይም በግልገል ሙሴው አማካይነት፡ በመጨረሻው ሰሙናዊ ወይም ወርኃዊ ስብሰባ ላይ፡ በቃል ይነገራል። የስብሰባ ጥሪ፡ በቃል ወይም በጽሑፍ ሊኾን ይችላል። በጽሑፍ እንዲኾን ያስፈለገ እንደኾነ፡ ጥሪው፡ ከላይ የተጠቀሱትን ዝርዝሮች ከያዘ መግለጫ ጋር፡ ለስብሰባው ከተወሰነው ቀን በፊት፡ ቢያንስ፡ ከአምስት፥ ቢበዛም፡ ከሃያ ቀኖች ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ፡ ለእያንዳንዱ አባል እንዲደርሰው ይላካል።

በስብሰባ ላይ ተገኝቶ ድምፅ የመስጠት መብት ያለው፡ አንድ አባል፡ በተጠራበት ስብሰባ ላይ የመገኘት ኃላፊነት አለበት። ምናልባት፡ በስብሰባው ላይ ለመገኘት የማይችልበት ምክንያት ቢያጋጥመው፡ ይህንኑ፡ በቅድሚያ፡ ለሙሴው ወይም ለሚመለከተው ሰብሳቢ ማስታወቅ ይኖርበታል።

ማናቸውም አባል፡ በስብሰባው ላይ ያልተገኘበትን ምክንያት በመግለጽ፡ ለሙሴው ወይም ለሚመለከተው ሰብሳቢ፡ መልእክት ሳይልክ፡ በሦስት ተከታታይ ስብሰባዎች ላይ ሳይገኝ ቢቀር፡ ሙሴው፡ ለዚያ የአገልግሎት ወንበር፡ ሌላ አባል፡ በጊዜያዊነት ተክቶ፡ በመምሪያው መሠረት ተገቢው እንዲፈጸም ያደርጋል።

## ንዑስ አንቀጽ ፯

## የስብሰባ ሥራ፡ ቅደም ተከተል

የአገልግሎቱ ጠቅላላ ጉባዔና የመደበኛ ሸንጎዎች፥ የምርፋቁና የሌሎቹ ሕዋሳት ስብሰባዎች ኹሉ፡ ተግባራቸውን የሚያከኺዱበት ቅደም ተከተል እንደሚከተለው ይኾናል፦

፩ኛ፡ ስብሰባውን በጸሎት መክፈት፤
፪ኛ፡ የስብሰባው ጥሪ ለተሳታፊዎቹ መድረሱን ማረጋገጥ፤
፫ኛ፡ አባሎች መገኘታቸውን፡ ስማቸውን በመጥራት ማወቅ፤
፬ኛ፡ ቃለ ጉባዔን ማንበብ፤
፭ኛ፡ መልእክቶችን መቀበል፤
፮ኛ፡ አገልጋዮችን መሠየምና የአባልነትን ጥያቄ መመርመር፤
፯ኛ፡ የዋና አገልጋዮችን የሥራ ፍሬዎች፡ መስማት፤
፰ኛ፡ የየሕዋሳቱን የሥራ ውጤቶች ማዳመጥ፤
፱ኛ፡ ውዝፍ የሥራ ጉዳዮችን ማጠናቀቅ፤
፲ኛ፡ አዳዲስ የሥራ ጉዳዮችን መመልከት፤

፲፩ኛ፡ ማስታወቂያዎችን መንገር፤
፲፪ኛ፡ ስብሰባውን በጸሎት መዝጋት።

ይህ የሥራ ቅደም ተከተል፡ በማናቸውም ስብሰባ ላይ በተገኙት አባሎች፡ ስምምነት ሊሻሻል የሚቻል ሲኾን፡ ማናቸውም የሥራ ጉዳይ፡ በቅድሚያ እንዲታይ የመወሰኑ ሥልጣን ግን፡ የስብሰባው ሊቀ መንበር ብቻ ይኾናል።

## አንቀጽ ሰባት

### የአገልግሎት አቋም

አገልግሎቱ፡ ዓላማዎቹ ከግብ የሚደርሱበትን ተግባሮቹን ለማከናወን፡ የእግዚአብሔር መንግሥት የኾነችውን፡ የኢትዮጵያን አቋም ተከትሎ፡ ከዚህ በሚከተለው መልክ፡ ሥራዎቹን ያካኺዳል፤ ይፈጽማልም።

#### ንዑስ አንቀጽ ፩

#### የጠቅላላው ጉባዔ አንድነትና የአገልግሎት ቤቶች ሦስትነት

በአገልግሎቱ ዓመታዊ ስብሰባ ላይ፡ በመላው አባሎች የሚመረጠው፡ የአገልግሎቱ ጠቅላላ ጉባዔ፡ ቤተ ሕዝቡን፥ ቤተ ምልክናውንና ቤተ ክህነቱን አዋህዶ የያዘው፡ አንድ ዓቢይ አካል ነው። አገልግሎቱ፡ ለጠቅላላው ጉባዔ፡ የአቋም ግንድ በኾነው፡ በቤተ ሕዝቡ፥ እንዲሁም፡ ከእርሱ በሚሠርፁት፡ በቤተ ምልክናውና በቤተ ክህነቱ አማካይነት፡ የአገልግሎቱን አውታር፡ በአጠቃላይና በየዘርፉ ዘርግቶ፡ ተግባሩን ያካኺዳል፤ ይፈጽማልም።

#### ንዑስ አንቀጽ ፪

#### የሦስቱ የአገልግሎት ቤቶች፡ የተዋህዶ ምሥጢር

የእግዚአብሔር መንግሥት ክፍሎች የኾኑት፡ እነዚህ በተዋህዶ የጸኑት፡ ሦስት ቤቶች፡ እንደሥሉስ ቅዱስና እንደሰው አካል፡ የአንድነትና የሦስትነት ምሥጢር ያላቸው፡ አንድም፥ ሦስትም ኾነው፡ በኢትዮጵያዊው ሰውነትና በአንዲቱ ኢትዮጵያ ይሠራሉ። ይህም ማለት፡ አንዱ እግዚአብሔር አምላክ፡ በአብ፥ በወልድ፥ በመንፈስ ቅዱስ፡ እንዲህ፡ በሦስት ስም፥ በሦስት አካልና በሦስት ግብር ታውቆ፥ ተገልጦና መልቶ እንደሚሠራ፥ ደግሞም፡ አንዱ ሰብአዊ ፍጡር፡ ነፍስ፥ ሥጋና መንፈስ በተባሉ፡ በሦስት ስሞች፥ በሦስት አካላትና በሦስት ግብሮች ተጠርቶ፥ ገዝፎና ረቅቆ እንደሚኖር ኹሉ፡ እንዲሁ፡ እያንዳንዳቸው፡ የእግዚአብሔር መንግሥት የኾኑት ኢትዮጵያውያን ባስገኙት፡ በዚህ አገልግሎት፡ ቤተ ሕዝቡ፡ እንደአብ ወይም እንደነፍስ አካል፥ ቤተ ምልክናው፡ እንደወልድ ወይም እንደሥጋ አካል፥ ቤተ ክህነቱ፡ እንደመንፈስ ቅዱስ ወይም እንደመንፈስ አካል ኾነው ተግባራቸውን ያካኺዳሉ።

### ንዑስ አንቀጽ ፫

### የሦስቱ የአገልግሎት ቤቶች የሥራ ድርሻ

ከላይ፡ በንዑስ አንቀጽ ፪ የተገለጸውን ምሥጢር መሠረት በማድረግ፡ ቤተ ሕዝቡ፡ በውስጥ፡ የአባሎቹን፥ በውጭ ደግሞ፡ የሕዝቡን ጠቅላላ ፍላጎትና ግዳጅ፥ ቤተ ምልክናውም፡ በውስጥ፡ የአባሎቹን፥ በውጭ ደግሞ፡ የኅብረተሰቡን ሥጋዊ ፍላጎትና ግዳጅ፥ ቤተ ክህነቱም፡ በውስጥ፡ የአባሎቹን፥ በውጭ ደግሞ፡ የምዕመናኑን መንፈሳዊ ፍላጎትና ግዳጅ ለማሟላትና ለመፈጸም የሚያስችለውን፡ ተገቢውን ተግባርና አገልግሎት፡ በየበኩላቸው ያከናውናሉ።

## አንቀጽ ስምንት

## የአገልጋዮች ምርጫና ሢመት

መላውን አገልግሎት፥ ጠቅላላውን ጉባዔ፥ ሦስቱን የአገልግሎት ቤቶችና ምርፋቁን፥ ሌሎቹንም የአገልግሎቱን ሸንጎዎችና ስብሰባዎች፡ በመንፈስ ቅዱስ የሚሰበስቡትና የሚመሩት፡ ራሳቸው፡ ኢየሱስ ክርስቶስና ድንግል ማርያም የመኾናቸውን ሃይማኖታዊ ምሥጢር፡ በእውነትና በመንፈስ፡ አውቀውና ተረድተው፡ ኃላፊነታቸውን በፍጹም ፈቃደኛነት በመቀበል፡ የአገልግሎቱን ዓላማዎች፡ በተግባር ላይ የሚያውሉለትን አገልጋዮች፡ አገልግሎቱ፡ ከዚህ በሚከተለው ሥርዓት መርጦ፡ በየመንበራቸው ይመድባል።

### ንዑስ አንቀጽ ፩

### የአገልግሎት ሥዩማንና አባሎች አመራረጥ

### ሀ. ሙሴ

የኢየሱስ ክርስቶስና የእናቱ ድንግል ማርያም፡ ተቀዳሚ ተጠሪ ኾኖ፡ አገልግሎቱን፡ በባለአደራነትና በበላይነት የሚሰበስበውና የሚመራው፥ የሚያስተዳድረውና የሚቆጣጠረው፥ ሌላውንም የአገልግሎት ኀላፊነቱንና ተግባሩን የሚፈጽመው ዋና አገልጋይ፡ ሙሴ ተብሎ ይጠየማል። የሙሴው ምርጫ፡ መላው አባሎቹ በተገኙበት፡ በጠቅላላው ጉባዔ ይፈጸማል። ያንንም ስብሰባ፡ በሊቀ መንበርነት እንዲመራ፡ የጠቅላላው ጉባዔ አባሎች፡ ከመካከላቸው፡ በዕድሜ አረጋዊነት እና/ወይም በአባልነት ተራ፡ ቅድሚያ ያለውን አባል፡ ሰብሳቢ ይኾን ዘንድ፡ በአንድ ድምፅ ይወስናሉ። የእርሱ፡ ለዚህ ጊዜያዊ ኃላፊነት መመደብ፡ ለሙሴነት ምርጫ፡ እጩ ከመኾን አይከለክለውም።

## ለ. ሊቃነ መናብርት

ከሙሴው ቀጥለው ረዳቶች ተጠሪዎች በመኾን: አገልግሎቱን በቀንደኛነት የሚያገለግሉት: የቤተ ሕዝቡ፥ የቤተ ክህነቱና የቤተ ምልክናው ሊቃነ መናብርት: ከቤተ ሕዝቡ ጠቅላላ ጉባኤ ተወካዮች መካከል: በሙሴው አቅራቢነትና ሊቀ መንበርነት: በጠቅላላው ጉባኤ ይመረጣሉ:: የእነርሱም ሢመት: በጠቅላላው ጉባኤ ከጸደቀ በኋላ: እያንዳንዳቸው: ምክትሎቻቸውን፥ እንዲሁም: የቤተ ምልክናውና የቤተ ክህነቱ ሊቃነ መናብርት: በአገልግሎት የሚረዷቸውን ሹማምንት: ከጠቅላላው ጉባኤ ሕዝባውያን፥ ካህናትና ምሉካን ተወካዮች መካከል መርጠው: ለሙሴው ያቀርባሉ:: እርሱ: ምርጫቸውን: ሲቀበለው: አባሎቹ: የተመደበላቸውን የኃላፊነት ሥራ ይጀምራሉ::

በዚህ የአገልግሎት ጥሪና ድልድል ውስጥ የሌሉት: የቀሩት የጠቅላላው ጉባኤ ተወካዮች: የቤተ ሕዝቡ መደበኞች ባልደረቦች ኾነው: የሕግ አውጭነት ተግባራቸውን ያካኺዳሉ::

የቤተ ሕዝቡ ሊቀ መንበር: በዚህ ኃላፊነቱ ምክንያት: ምንጊዜም: የግልገል ሙሴነቱን የአገልግሎት ቦታ የሚይዝ እርሱ ይኾናል::

ሦስቱም ሊቃነ መናብርት: በየሊቀ መንበርነት ኀላፊነታቸው: የምርፋቁ አባሎች ናቸው::

## ንዑስ አንቀጽ ፪

## የአገልግሎት ሹማምንቱ ብቅዓትና የሥራ ዘመን

ከላይ በንዑስ አንቀጽ ፩ የተጠቀሱት ባለአደራ አገልጋዮች: እያንዳንዳቸው ለሚይዙት የኃላፊነት መንበር በሚያበቋቸው: በሦስቱም የኢትዮጵያዊነት የሥልጣን ጸጋዎችና ሙያዎች: ማለትም: በሕዝባዊነት፥ በክህነትና በምሉክነት የተሟሉ ኾነው መገኘታቸውን፥ እነርሱም: የአገልግሎቱን ኃላፊነት: በፍጹም ፈቃደኝነት ለመቀበል መዘጋጀታቸውን: ጠቅላላው ጉባኤ: በጊዜው ኃላፊዎች አማካይነት: በቅድሚያ ያረጋግጣል::

የእነዚህ አገልጋዮች: የሥራ ዘመን: ሦስት ዓመታት ይኾናል:: ይህ የአገልግሎት ዘመን በሚያበቃበት ጊዜ: ኹሉም: ወይም ጥቂቶቹ: ወይም አንዳቸው: አገልግሎታቸውን ሊቀጥሉ የማይችሉበት በቂ ምክንያት ካልተገኘ: ወይም በየራሳቸው ፈቃድ ሥራቸውን መልቀቅ ካልፈለጉ በስተቀር: ቦታቸውን እንደያዙ: የተለመደ አገልግሎታቸውን ይቀጥላሉ::

## ንዑስ አንቀጽ ፫

## የተለቀቁ የአገልግሎት ወንበሮች

በሙሴው መንበር፥ እንዲሁም: በቤተ ሕዝቡ፥ በቤተ ክህነቱና በቤተ ምልክናው፥ በምርፋቁና በሌሎቹም የአገልግሎቱ ሕዋሳት ውስጥ: በሞት፥ በሥራ መልቀቅ ወይም በሌላ ምክንያት: የማናቸውም የአገልግሎት አባል ወንበር የተለቀቀ እንደኾነ: በሙሴው: ግልገል ሙሴው ይተካል፤ በሌሎቹ ቦታዎች ግን: ሙሴው: ያለመዘግየት: ጊዜያዊዉን ተተኪ ይመድብበታል::

ኢትዮጵያ፡

ይህም የሚኾነው፡ ምርፋቁ፡ በመደበኛ ስብሰባው፡ ወይም ለዚሁ ጉዳይ ብሎ በሚያደርገው ልዩ ስብሰባ ተነጋግሮ፡ የጊዜያዊዉን አገልጋይ ተተኪነት እስኪያጸድቀው፡ ወይም ተገቢ የኾነ ሌላ አገልጋይ እስኪተካበት ድረስ ነው። በዚህ መልክ የተሠየመው አባል፡ ምርጫው፡ በጠቅላላው ጉባዔ እስከሚጸድቅበት፡ እስከሚቀጥለው ዓመታዊ ስብሰባ፡ ወይም፡ በአንቀጽ ስድስት፥ ንዑስ አንቀጽ ፬ መሠረት፡ ልዩ ስብሰባ ተደርጎ፡ ተተኪው ሰው እስኪመረጥ ድረስ፡ ወንበሩን ይዞ ሲያገለግል ይቆያል፡

## አንቀጽ ዘጠኝ

### የምርጫ ሱባዔ

ምርጫዎች ኹሉ የሚካኼዱት፡ መላው አባሎች፡ የመንፈስ ቅዱስ መሪነት፥ ረድዔትና በረከት እንዳይለያቸው፡ ቀደም ብለው የሚያደርጉት፡ የሱባዔ ሥርዓት ካበቃ በኋላ ይኾናል። ይኸውም፡ እያንዳንዱ የአገልግሎቱ ምርጫ፡ በዚህ መልክ በሚከናወንበት ጊዜ፡ ምርጫው፡ በመንፈስ ቅዱስ እንደተፈጸመ ታምኖበት፡ ለተመራጩ ወይም ለተመራጮቹ፡ "ሥዩመ እግዚአብሔር" የሚለውን የጸጋ ማዕርግ የሚያጎናጽፍ በመኾኑ ነው።

## አንቀጽ አሥር

### የዓላማው ቋሚ አፈጻጸምና የሥራ አመራር

በአጠቃላይና በዝርዝር፡ ሥጋዊና መንፈሳዊ የኾነው የአገልግሎቱ ተግባር የሚከናወነው፡ ከላይ በአንቀጽ ሰባት የተመለከተውን፡ የአገልግሎት አቋም በመከተል፡ ቀጥሎ በተብራራው መሠረት፡ የአገልግሎቱ ሙሴ በተጠሪነት በሚመራው፡ ጠቅላላ ጉባዔ፥ እንዲሁም፡ በቤተ ሕዝቡ፥ በቤተ ምልክናውና በቤተ ክህነቱ አማካይነት ይኾናል።

#### ንዑስ አንቀጽ ፩

#### የሙሴው መንበር

በሙሴው የአገልግሎት ኃላፊነት ሊፈጸሙ ከሚገባቸው ተግባሮች መካከል፡ ከዚህ የሚከተሉት ይገኛሉ።

፩ኛ፡ በመላው አባሎችና እንዲሁም፡ ቤተ ምልክናውንና ቤተ ክህነቱን በሚያዋህደው፡ በቤተ ሕዝቡ ጠቅላላ ጉባዔ ስም፡ አገልግሎቱን ወክሎ፡ ማናቸውንም የአገልግሎቱን ጉዳይ ይፈጽማል፤

፪ኛ፡ የአገልግሎቱን ጠቅላላ ጉባዔና ምርፋቁን፥ መላው አባሎች የሚገኙባቸውንም ሌሎች ስብሰባዎች ይሰበስባል፤ ይመራል፤

፫ኛ፡ ዋናው የአገልግሎቱ ሥራ ፈጻሚ እንደመኾኑ መጠን፡ በአገልግሎቱ ጠቅላላ ጉባዔ የጸደቁት የአስተዳደርና የሥራ ጉዳዮች፥ መርሐ ግብሮችና ዕቅዶች፡ በተግባር ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤